

## ማቆሚያና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ ዕንባ!

ከክንፈ ሚካኤል አበበ /አበበ ቀስቶ/ ከቃሊቲ ወህኒ ቤት 4

## ስለአፄ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ አባትነት

ዓለማየሁ ገላጋይ 3

## አለውክልና ግብር የለም

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም 3






# ፍትህ

ቅፅ 5 ቁጥር 183 አርብ ሚያዝያ 5 2004 ዓ.ም | www.fetehe.com Addis Ababa-Ethiopia | ዋጋ 7.00 ብር


## የፍትህ መንገድ - ከአሲምባ እስከ ቀራኒዮ 5




## የነፃው ፕሬስ ጉዞ እየተደመደመ ነውን?

2

## እስክንድር ነጋ አለም አቀፍ ተሸላሚ ሆነ

ታዋቂው የፖለቲካ ተንታኝ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የ2012 የፔን ኢንተርናሽናል ተሸላሚ ሆኖ መመረጡን ምንጮቻችን ለፍትህ ገለፁ፡፡

እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የነጻ ጋዜጣ መስራች ከመሆኑም በተጨማሪ ከባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል ጋር በመሆን የበርካታ ጋዜጣ ባለቤቶች እንደነበር ይታወቃል፡፡

የፖለቲካ ተንታኝ እና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ መንግስት ለተደጋጋሚ ጊዜ የታሰረ እና የተደበደበ ሲሆን በምርጫ 1997 ማግስት የተከሰተውን አለመግባባት ተከትሎ ከባለቤቱ ጋር በቃሊቲ ማረሚያ ቤት 20 የእስር ወራትን አሳልፏል፡፡

ጋዜጠኛ እስክንድር ከእስር ከተፈታ በኋላ ጋዜጣ ለማሳተም ፍቃድ ጠይቆ በመንግስት የተከለከለ ቢሆንም በሀገር ውስጥ በተለያዩ ጋዜጦች እና ድረ ገፆች ላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ አንባቢያን የሚከታሉት ትንተናዎችን ያቀርብ እንደነበረ ይታወቃል፡፡ አለም አቀፉ ድርጅት በሆነው ፔን ኢንተርናሽናል የአሜሪካ ሴንተር (Pen International) ጋዜጠኛ እና የፖለቲካ ተንታኝ የሆነውን እስክንድር ነጋን የ“2012 Pen Barbra Gold Smith freedom to Wright Award” ተሸላሚ አድርጎ መርጦታል፡፡ ሽልማቱንም በሜይ 1 ቀን ኒዎርክ ላይ በሚደረገው ዓመታዊው የፔን ጋላ ላይ የእስክንድር ተወካይ ተገኝተው እንደሚቀበሉ ምንጮቻችን ገልፀዋል፡፡

ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ የኢትዮጵያ መንግስት በሽብር ተግባር ተሳትፈሃል በሚል ጥርጣሬ በቃሊቲ ማረሚያ ቤት ከመስከረም ወር ጀምሮ ታስሮ እንደሚገኝ ይታወቃል፡፡

## የአባይ ግድብ ቀያሽ የት እንደገቡ ሳይታወቅ 25 ቀን አለፈው

- «በጣም ተረብሸናል» ቤተሰቦቻቸው 13

## እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜተር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ



የተከበሩ የዓለም ሎሬት ሜተር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ በ1924 ዓ.ም. በአንኮበር ከተማ የተወለዱት እውቁ ሰዓሊ ሜተር አርቲስት አፈወርቅ በ80 ዓመታቸው ማክሰኞ ሚያዝያ 2 ምሽት ላይ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

በእድሜ ዘመናቸው ከ80 በላይ ሽልማቶችን ያገኙት ሰዓሊው ከዓለም ተወጣጥተው ስማቸው፣ በሀገራቸው ባንዲራና ታሪካቸው ጨረቃ ላይ ከተቀመጠላቸው 200 ሰዎች አንዱ ነበሩ፡፡

ወርልድ ፎረም ፌዴሬሽን ከሰኔ 22 እስከ ሰኔ 27/2001 ዓ.ም. በዋሽንግተን ዲሲ ባዘጋጀው ዓለም አቀፋዊ ዐውደ ርዕይ ላይ የስነ-ጥበብ ስራዎቻቸውን በማቅረብ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እጅግ ታላቅ አርቲስት (ታላቁ ሰው) በመባል ከተመረጡ አንድ ሺህ ሰዎች መካከል


ወደ ገፅ 15 ዞሯል


## መኢአድ ከቤንች ማጂ ዞን የተፈናቀሉ የአማራ ብሔር ተወላጆችን በተመለከተ መንግስትን ነቀፈ

- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ስለጉዳዩ መረጃ የለውም 15

## የፕ/ር መስፍን ወልደማርያም «አዳጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ» መጽሐፍ ታተመ 15

## የአራዳ ክ/ከተማ ባለስልጣን ከግድያ ለማምለጥ ከሁለተኛ ፎቅ ላይ ዘለሉ 15

## ኢትዮጵያ የተባበሩ መንግስታት የደህንነት ሰራተኛን በሽብርተኝነት ከሰሰች 15

## እነእስክንድር ነጋ ለብይን ግንቦት ሶስት ተቀጠሩ 15

# የነፃው ፕሬስ ጉዞ እየተደመደመ ነውን?



ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

በድህረ-ቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃት ማግስት ወደስልጣን የመጣው ኢህአዴግ ራሱን ከቀደመው ሶሻሊስታዊ ስርዓት የተለየ አድርጎ ለማቅረብ እና የምዕራባውያንን ቅቡልነት ለማግኘት በመሻት የነፃ ፕሬስን ህልው መሆን ፈቀደ:: ይህን ፖለቲካዊ ማሻሻያ ተከትሎ ከሁለት መቶ በላይ ጋዜጦች እና ከ87 በላይ መጽሔቶች የነፃ ፕሬሱ ጀማሪዎች ሆኑ:: ለተወሰኑ ጊዜያት ሁኔታዎች መልካም ቢመስሉም በጋዜጠኞች ተደጋጋሚ እስር እና ተዛማጅ ቅጣቶች መፈተን የጀመረው የፕሬሱ ጉዞ በኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ማግስት በተፈጠሩት በውስጣዊ እና ውጪያዊ ጫናዎች ቁጥሩ እየቀነሰ መጣ:: የ1997ቱን የፖለቲካ ቀውስ ተከትሎ ወደ አስራ አምስት የሚጠጉ አዘጋጆችና ሪፖርተሮች በሀገሪቱ ህግ ከባድ በሚባሉት ሀገር መክዳትን በመሰሉ ክሶች እስር ቤት ገቡ:: ከሃያ ወራት በኋላ እነዚህ ጋዜጠኞች ከእስር ቢፈቱም ብዙዎቹ ሲሰደዱ ሀገር ውስጥ የቀሩት ‹‹ማሳተም አትችሉም›› በመባላቸው በሀገሪቱ ውስጥ ያለው የጋዜጣ ቁጥር እጅግ ተመናመነ:: ባለፉት ጥቂት ዓመታት ወደ ገበያ ከመጡት የፖለቲካ ጋዜጦች መሀከልም ሁለቱ ብዙም ሳይቆዩ ህልውናቸው አከተመ:: ዊኪሊክስ እንዳወጣው ዘገባ በ‹‹ህዝብ አስተያየት›› ስም ከፍተኛ የገዢው ፓርቲ አመራሮች ብዕር ስምን ሽፋን በማድረግ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ ያወጧቸው የፍረጃ ውንጀላዎች በቅርቡ በተዘጉት ጋዜጦችም ሆነ ለተሰደዱት አዘጋጆች በምክንያትነት ይጠቀሳል:: የኢትዮጵያ የፕሬስ የሁለት አስርታት አጭር ታሪክ ላይ የሚናገሩ አጥኚዎች የሀገሪቱ ነፃ ፕሬስ መንታ መንገድ ላይ እንደቆመ ይሟገታሉ:: በዚህ የሙግት ንፃሬ የፕሬሱን ከየት ወዴትነት ለማየት መሞከር ወቅታዊ ጭብጥ ይመስላል::

## መንታ እዳዎች

የኢትዮጵያን የነፃ ፕሬስ ኮረኮንቻማ ጉዞን ለመገምገም በጉዳዩ አጥኚዎች የሚጠቀሱ ሁለት ተመጋጋቢ ሁነቶች አሉ:: ሚዲያ በምዕራባውያኑ የፖለቲካ ስርዓት ውስጥ ያለውን ሚና እና የተግብሮት ሂደት ማንፀሪያ አድርጎ የኢትዮጵያ አቻውን ለመመልከት መሞከር ስሁት ድምዳሜ ላይ ይጥላል:: ዶ/ር ኒኮል ስትሪምላዩ እንደምትለው ከ1984 ዓ.ም. ወዲህ ያለውን ፕሬስ በአግባቡ ለመረዳት ፕሬሱ እና ፕሬሱ የሚሰራበትን አውድ የወሰኑ ሁለት ነገሮችን አጣምሮ መመርመር ያስፈልጋል፡- የተማሪዎች ንቅናቄ እና የቅድመ-83 የህወሓት የኮሚኒኬሽን ባህል::

በሀገሪቱ ያለው የጋዜጣ ጅማሮ ምንም እንኳን ውልደቱ በ19ኛው ክ/ዘመን መጨረሻ ቢጀምርም ተፅእኖ ሊያሳርፍ በሚያስችል መልኩ እድገቱ የታየው በ1950ዎቹ አጋማሽ ነው:: የወቅቱ ተማሪዎች ስርዓቱ ላይ ያላቸውን ቁጣ የሚገልፁት በዋናነት ራሳቸው በሚያዘጋጁቸው የተማሪ ልሳኖች ነበር:: የተማሪዎቹን ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ ባህል በማረቅ ቀዳሚ የሆኑት በጊዜው አፄ ኃ/ሥላሴ የነፃ ትምህርት እድል የሰጧቸው አፍሪካውያን ተማሪዎች ነበሩ:: ዶ/ር ራንዲ ባልሼቪክ “Haile Silasie’s students the intellectual and social background to revolution” በሚለው መፅሐፋቸው እንደሚሉት ‹‹ሂስ›› እና ‹‹ግለሰባዊ ስድቦችን›› በሚገባ መለየት ላልቻሉት የጊዜው ተማሪዎች የነዚህ አፍሪካውያን ወጣቶች ተሳትፎ ተማሪዎቹን በድፍረት እንዲናገሩ በማስቻል ግዙፍ አስተዋፅኦ ነበረው:: የተማሪዎቹ ንቅናቄ አቅም እየጎለበተ ሲሄድ ከአጼው ጋር የገቡበት ንትርክም ወደ ፅንፈኝነት እያዘነበለ ሄደ:: በዚህ የንቅናቄ ዘመን ወደ መድረኩ የመጡት ‹‹የብሔር›› ወይስ ‹‹የመደብ›› ቅራኔ ነው ቀዳሚው እና መሰል ጥያቄዎች ዙሪያ የነበሩት የክርክር አካሄዶች እጅግ አደገኛ የሚባሉ ነበሩ:: የሌላውን ወገን ሀሳብ ከመሞገት ይልቅ የተከራካሪውን ስብዕና (እንደ ብሄርና ሃይማኖት የመሰሉትን በመጥቀስ) በማዋረድ እና በማንኳሰስ ላይ ያተኮሩ ሙግቶች ተካሄዱ:: በድህረ-ደርግ ቀዳሚ ዓመታት የነበረውን የፕሬስ ባህል ከወሰኑት ይህን መሰል ጉዳዮች በተጨማሪ ሌላው የተማሪዎቹ ንቅናቄ ተራዘሚ ተፅዕኖ የወጣቶቹ አዕማድ አፍራሽነት /Iconoclasm/ ነበረ:: የዘመኑ ወጣቶች ነባሩን ማህበር-ባህላዊም ሆነ ፖለቲካዊ ስርዓት የቆመባቸውን አዕማዶች በማፈራረስ ላይ አትኩረዋል:: በ1984 የነፃ ፕሬስ ህልው መሆን ሲታወጅ የፖለቲካ ስርዓቱንም ሆነ የሚዲያውን ጅማሮ ያበሰሩት ብዙዎቹ ከዚህ ሌሎችን በመረምረም እና ፅንፈኛ አቋምን በማራመድ ከተበከለው የተማሪዎቹ ንቅናቄ የኮሚኒኬሽን ባህል ውርስ የተላቀቁ አልነበሩም:: እንደ እስክንድር ነጋ እና በፍቃዱ ሞረዳ ዓይነቶቹ የነፃው ፕሬስ ጀማሪዎች የ‹‹ያ-ትውልድ›› አባላት ባይሆኑም፤ በወቅቱ ከነበሩት ከ200 በላይ ጋዜጣ አዘጋጆች መሀከል ብዙዎቹ የዚያ ትውልድ አባላት መሆናቸው በ1980ዎቹ አጋማሽ በተፈጠረው የፕሬሱ እና የገዢው ልሂቅ መተናነቅ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳደረገ ዶ/ር ኒኮል “The press and the political restructuring of Ethiopia” በሚለው ጥናታዊ ፅሁፏ ታወሳለች::

በፕሬሱ እና በኢህአዴግ መሀከል ላለው አሉታዊ ግንኙነት ተጠቃሹ ሌላው ምክንያት የህወሓት የጫካ ዘመን የሚዲያ አመለካከት ነው:: ህወሓት ከመመስረቱ በፊት የትግራዎያን ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ማህበርን /TUSA/ ያቋቋሙት የትግራይ ወጣቶች ‹‹‹እተክ›› /ታጠቅ/ እና ድምፂ ብሔረ ትግራይ የሚባሉ ጋዜጦች ነበሯቸው:: ወጣቶቹ ወደ ትግል ከገቡ ወዲህ፡- እተክ /ታጠቅ/፣ ንቅሓ፣ ተጋደል እና ወይን የተባሉ ጋዜጦች ማሳተም ቻሉ:: ከዚህ በተጨማሪ ‹‹ስቶርም›› የተሰኘ ስርጭቱን በዲያስፖራ ክፍል ያደረገ ህትመትም በህወሓት ይዘጋጅ ነበር:: የ“Peasent Revolution in Ethiopia” መጽሐፍ ፀሐፊ ዶ/ር ጆን ያንግ እንደሚሉት ከፓርቲው የሬዲዮ ጣቢያ በተጨማሪ እነዚህ ህትመቶች ዋነኛ ግብ አድርገው የሚነሱት ደርግ በትግራይ ህዝብ ላይ አድርሶታል የሚባሉትን ጉዳቶች በመዘርዘር ላይ ነው:: ዶ/ር ኒኮል በበኩላቸውየፓርቲው የሚዲያ ባህል ፖለቲካዊ ድጋፍ ለማግኘት ያለመ ከመሆኑ አንፃር የትግራይ ህዝብ የተከሰቱ እና ያልተፈጠሩ ደርግ-ፈጠር ጉዳቶችን ከማሰብ ለአፍታም እንዳይላቀቅ ለማድረግ ከመፈለግ እንደሚነሳ ይጠቅሳሉ:: ሌላኛው የፓርቲውን የሚዲያ ምልከታ የወሰነው ድርጅቱ “ኢምፔሪሲዝም (Empiricism)” ሲል የሚጠራው የሁኔታዎች አረዳድ ዘዬ ነው:: በዚህ ምልከታ መሰረት በሚዲያ የሚተላለፉት ዘገባዎች ኀልዮታዊ ልባስ ከመያዛቸው ይልቅ ፓርቲው ፈፅሜዋለሁ የሚላቸውን ‹‹በጎ ነገሮች›› በመተረክ ይወሰናል:: የእኒህ ሁለት የፓርቲው የሚዲያ ባህል መገለጫዎች አሁን ባለው የፕሬስ አካሄድ ላይ ያላቸው ተፅዕኖ ግልፅ ነው:: ገዢው ፓርቲ የሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች ኢህአዴግ ባይኖር ሀገሪቱ ሊገጥማት ስለሚችሉት ክፉ እድሎች ከመተረክ አይቦዝኑም:: ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወደ ስልጣን ቢመጡ ምን ያህል ጉዳቶች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ስርዓቱ በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች ሲተረክ፤ በግልባጩ በነፃው ፕሬስ ላይ በሚተላለፉ ተገዳዳሪ ዘገባዎች ይህን ፓርቲው እንዲፈጠር የሚፈልገውን ሀገራዊ መንፈስ መግራታቸው ፓርቲው ፕሬሱን እንዲያፍን እንደገፋው የኦክስፎርዷ መምህር ትናገራለች:: ሌላኛው የማፈኛ መግፍኤ ‹‹ልማትን›› በተመለከተ ፓርቲው ከ‹‹ኢምፔሪሲዝም›› አረዳዱ የሚናጠቀው አካሄዱ ነው:: የስርዓቱን ጉድለቶች ባለመንካት ‹‹ወዳጃዊ›› ግንኙነት ለመፍጠር በሚሞክሩት፣ ምሁራን ‹‹ግሬይዞን›› ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሚሏቸው ሚዲያዎች እና የስርዓቱ አንደበቶች፤ ገዢው ፓርቲ ከውኛቸዋለሁ በሚሏቸው መንገድ መሰል ‹‹ልማቶች›› ላይ ሲያተኩሩ፣ በሌላ ጫፍ ይህን የፓርቲውን የልማት አተረጓጎም ስህተት ለማሳየት የሚወጡ ዘገባዎች በፓርቲው በኩል በመልካም እንዳይታዩ ያደርጓቸዋል:: እነዚህ ሁነቶች የገዢው ፓርቲ ልሂቃን ከተማሪዎች ንቅናቄ ከወረሱት ‹‹የአንድ እውነት ባለቤትነት›› ጋር ሲዛመዱ ሀገሪቱን ካለነፃ ሚዲያ ለመምራት እንዲያልሙ ያስገደዳቸው ይመስላል::

በሌሎች ሀገራት እንደሚስተዋለው የኢትዮጵያ የነፃ ፕሬስ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት እንዲፈጠር የራሱን አበርክቶት እንዳያደርግ ሁኔታዎቹ የተመቹ አልሆኑም:: ሞንሮኢ ፕራይስ፣ ኢብራሂም አልማራሺ እና ኒኮል ስትሪምላይ የተባሉ አጥኚዎች ለዚህ ክስተት ሁለት ምክንያቶችን ያቀርባሉ:: የመጀመሪያው ገዢው ፓርቲ ፕሬሱን ለማቅረብ አለመሞከሩ ነው:: ፓርቲው በፕሬሱ ላይ ከሚወጡ ዘገባዎች እና ትንታኔዎች በመነሳት ለውይይትም ሆነ ሀገራዊ ለሆኑ ጉዳዮች ፕሬሱን ለማሳተፍ አለመሞከሩ በተፃራሪው ፕሬሱ በሌላ ፅንፍ ላይ እንዲቆም መግፋቱ ቀዳሚ ጉድለት እንደሆነ እነሞንሮኢ ይከራከራሉ:: ኢህአዴግ በዚህ ፕሬሱን ወደ ጎን በመግፋት ላይ መሰማራቱ ብቻውን በሚቆጣጠራቸው ሚዲያዎች ላይ እንዲወሰን ማድረጉን አጥኚዎቹ በሁለተኝነት ያነሱታል:: እንደ እነሞንሮኢ ሙግት ይህ የፓርቲው አካሄድ በሀገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃንም ሆነ በመንግስት እና በፕሬስ መሀከል ያለውን ግንኙነት ወደ ፅንፈኝነት ወስዶታል:: ለሶስቱ የጉዳዩ ፀሐፊዎች ለዚህ ዓይነት ክስተት መፈጠር አስተዋፅኦ ያደረገው የገዢው ፓርቲ የ‹‹ልማታዊ መንግስት›› ኃልዮት መረጣ ነው:: “Media in the peace building process: Ethiopia and Iraq” በሚለው የሁለቱ ሀገራት ንፅፅራዊ ጥናታዊ ፅሁፋቸው እንደሚያነሱት በደቡብ ኮሪያ እና በታይዋን ያለው የሚዲያ ነፃነት በገደቦች የተሞላ ነው:: በነፃው ፕሬስ ላይ ምንም ዓይነት ሂሶች ሲስተናገዱ መንግስታቱ ታሳቢ የሚያደርጉት ምን ያህሎቹ ዘገባዎች በገዢው ፓርቲ ላይ እና በ‹‹ልማታዊ›› ዕቅዶች ላይ ተሰሩ የሚሉትን ነው:: ዘገባዎቹ በእነዚህ ሁለት ‹‹ዓይነኬ›› ጭብጦች ላይ ካተኮሩ ፕሬሱ ለጭፍለቃ ይጋለጣል:: የገዢው ፓርቲ የልማታዊ መንግስት ዕሳቤ ከኒህ አገራት እንደመቀዳቱ የኢትዮጵያም ፕሬስ ተመሳሳይ ዕጣ እየገጠመው እንደመጣ ይስተዋላል:: እንደ አጥኚዎቹ ትንታኔ አቶ መለስ ‹‹ልማትን›› መሰረት ካደረጉ መሰረታዊ ጉዮች ውጪ፤ የመሬት ጥያቄን፣ ፌደራሊዝሙን እና ህገ-መንግስቱን ማዕከል የሚያደርጉ ጋዜጦችን እና ዘጋቢዎችን በፀረ-ልማታዊነት በመፈረጅ ከአደባባዩ ያርቋቸዋል:: የፀሐፊዎቹን ግምገማ በሚያስረዳ መልኩ አሁን አሁን የአባይ ግድብን እና የመሬት ቅርምትን አስመልክቶ የሚወጡ የሌላ ጫፍ ትንታኔዎችን ስርዓቱ መታገስ አለመቻሉ የአደባባይ እውነት ሆኗል::

## ልማታዊ ጋዜጠኝነት ሲሉ

የልማታዊ መንግስት ፅንሰ ሀሳብ በአፍሪካ ፈር መያዝ የጀመረው እ.ኤ.አ በ1960 እና 70ዎቹ አካባቢ አንስቶ እንደነበር ተባባሪ ፕ/ሩ ተርጂ ስኪጅርዳል:: “developmental journalism revived: The case of Ethiopia” በሚለው ፅሁፋቸው ይገልፃሉ:: በወቅቱ የተለያዩ የአገር መሪዎች የልማታዊ ጋዜጠኝነት ሞዴልን በራሳቸው አገር ዘውግ /Context/ እንዲመች አድርገው መጠቀም የጀመሩ ሲሆን በቀጣዮቹ ጊዜያት ‹‹ልማታዊ ጋዜጠኛ›› እና ‹‹ልማታዊ ዘገባ›› የሚሉት ቃላት ከአፍሪካ ሚዲያ ፖሊሲ ቀስ በቀስ መጥፋታቸውን ይገልፃሉ::

በኤስያ ልማታዊ ጋዜጠኛ የሚለው ቃል በፖለቲካ ምህዳሩ መጠቀም ከመጀመሩ በፊትም ቢሆን በወቅቱ ጋዜጠኞች ተመሳሳይ የሆነ አቀራረብ ያራምዱ እንደነበር ስቴፈን ገናራትኔ እና “Social responsibility theory revisited” በሚለው ፅሁፋቸው ላይ ይጠቅሳሉ::

እንደ ነሀሲም ክርክር በ1970 እና 1980ዎቹ አካባቢ የልማታዊ ጋዜጠኝነት ፅንሰ ሀሳብ ደግሞ መነሳሳት ሲጀምር የተለያዩ የአፍሪካ መንግስታት በሚመቻቸው መልኩ በፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ በመክተት በተለይ የመንግስትን ሚዲያ ለማጠናከር ተጠቅመውበታል:: ከነዚህ መካከል ክዋሜ ንክሩማ አብዮታዊ ጋዜጠኛ የሚል ቅፅል ስም ለጋዜጠኛው ሲሰጡት የቀድሞ የታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኔሬሬ ደግሞ የኡጃማ ጋዜጠኛ ብለው ጠርተውታል:: ለተጠቀሱት ፀሐፊዎች እነዚህ የአፍሪካ መንግስታት በፖለቲካ የውስጥ ፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ የልማታዊ ጋዜጠኝነትን ፅንሰ ሀሳብ በዚህ መንገድ መጠቀማቸው በተለየ መልኩ የሚያሳየው ጋዜጠኝነት ከማህበረሰባዊ ተጠያቂነቱ ይልቅ ፖለቲካዊ ቀጥተኛ ቁጥጥር እንዳለበት ነው:: ይህ ተለምዷዊ ትስስሮሽ የቀዝቃዛውን ጦርነት ማብቃት ተከትሎ በተመሰረቱት የግል ሚዲያዎች ላይ አፈና እንዲፈፅሙ አስችሏቸዋል:: አጥኚዎቹ በዚህ ማሳያ አድርገው የሚጠቅሱት የናይጄሪያው አምባገነኑ የቡሃሪ መንግስት ልማታዊ ጋዜጠኝነት የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ በመንግስት ፖሊሲ ደረጃ የቀረፀ ቢሆንም ከዚህ በተለየ መንገድ መጓዝ የመረጡ የግል ሚዲያዎች ላይ ከፍተኛ ቁጥጥር ማድረግን ነው::

በልማታዊ ጋዜጠኝነት ዙሪያ የሚነሱ ችግሮችን በአጠቃላይ በሶስት ከፍልን ልናያቸው እንደምንችል በዘርፉ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን ይገልፃሉ:: የመጀመሪያ የቃሉ አሻሚ ትርጉም የፈጠራቸው ክፍተቶች ናቸው:: የልማታዊ ጋዜጠኝነት ፅንሰ ሀሳብ አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም ባለመያዙ የተለያዩ አገራት መሪዎች እንደተመቻቸው እንዲተረጉሙት እና እንዲጠቀሙት አስችሏቸዋል:: ሁለተኛው የልማታዊ ጋዜጠኝነት ትርጉም ክፍተት የተለያዩ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለሞችን በውስጡ እንዲይዝ እና ሌሎች የተለዩ ምልከታዎችን ለመጨፍለቅ ሁኔታዎችን ምቹ አድርጓል:: ሶስተኛው እና የመጨረሻው የፅንሰ ሀሳቡ ክፍተት በማሳያነት የሚቀርበው ልማታዊ ጋዜጠኝነት ትርጉም ከትክክለኛው የጋዜጠኝነት መርህ ይልቅ ፖለቲካ ወገንተኝነት ይጉላበታል የሚለው መከራከሪያ ነው:: ይህም ሚዲያው ማህበረሰቡን ማገልገል አለበት የሚለውን መርህ ገሸሽ አድርጐ የመንግስትን ፖለቲካዊ አጀንዳ በማራገብ ላይ እንዲጠመድ ገፍቶታል::

በኢትዮጵያ የልማታዊ ጋዜጠኝነት ፅንሰ ሀሳብን ለማብራራት በፖሊሲ ደረጃ የቀረበው ዶክመንት መሰረቱን ያደረገው የአገሪቷን የኢኮኖሚ ድህነት መቅረፍ ማዕከል ባደረገ መልኩ ነው:: መንግስት በሚቀጥሉት 20 እና ሰላሳ አመታት ዜጐችን መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገራት ተርታ አሰልፋለሁ የሚል እምነት በመያዙ በአገሪቷ ውስጥ የተሰለፉ ሚዲያውንም ጨምሮ ማናቸውም ኃይላት ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው በዝርዝር አስፍሯል::

መንግስት ይህንን ፖሊሲ ተግባራዊ ለማድረግ ማነቆ ይሆኑብኛል ብሎ በፖሊሲ ዶክመንቱ ላይ ካስቀመጣቸው ምክንያቶች አንዱ የግሉ ሚዲያ ነው:: ለጉዳዩ ተከታታዮች መንግስት የግሉን ሚዲያ በጥርጣሬ ዓይን እንዲያይ ያደረጉት ስጋቶች በተለይ ሁለቱ ዋነኞቹ ናቸው:: የመጀመሪያው ነፃ ሚዲያ ትርፍን ብቻ ማዕከል ያደረጉ ስለሚሆን የሚወጡት ዘገባዎች ጥራት አይኖራቸውም የሚለው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም የዚህ ሚዲያ ባልደረቦች ከመንግስት ልማታዊ እንቅስቃሴ ይልቅ በባህሪያቸው አሉታዊ ወደ ሆነው ዘገባ በማተኮር ሊያሳጡት ይችላሉ የሚሉት ናቸው:: ይህ ማለት ግን መንግስት በአገሪቷ ውስጥ ያሉ ዜጐች በሚዲያው እንዲሳተፉ አይፈልግም ማለት እንዳልሆነ የሚጠቁሙት እነዚህ ተንታኞች ፖሊሲው ጋዜጠኞቹ ልማታዊ እስኪሆኑ ድረስ በመንግስትም ድጋፍ ቢሆን መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ተጠቅሷል::

የሚዲያ ዶክመንቱ ልማታዊ ጋዜጠኛ የሚለውን ፅንሰ ሀሳብ ማህበረሰቡን እየተካሄዱ ያሉትን ልማታዊ እንቅስቃሴዎች እንዲረዳ፣ እንዲቀበል ብሎም በተጀመሩት እንቅስቃሴዎች ላይ እራሱ በንቃት በመሳተፍ ለለውጥ የሚተጋን ዜጋ የሚፈጥር አድርጎ ያስበዋል:: ዶክመንቱ እንደሚለው ይህ የልማት ጋዜጠኝነት ጥረት የመጨረሻ ግቡ የሚያደርገው ማህበረሰቡን ከኋላቀርና በፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ከድህነት አላቀው የበለፀገች አገር መመስረት ይሆናል:: ስለዚህ ይላል የፖሊሲው ዶክመንት ልማታዊ ጋዜጠኛ በዘገባው ሊያተኩርባቸው የሚገባው በጐ በጐውን ተግባራት ሲሆን የመንግስቱን አሉታዊ ጐን ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን ማቅረብ የሚደገፍ እንዳልሆነ ያብራራል::

መንግስት በመልካም ጐኑ ልማታዊ ጋዜጠኛ በአገሪቷ ከሚኖረው በጐ አስተዋፅኦ አንፃር በዚህ መልኩ መቃናት አለበት ብሎ ቢያምንም በቀጣይ ሊገኙብኝ ይችላል ብሎ የሚያስበውን ተግዳሮቶችም ጨምሮ አቅርቧል:: ይህም ልማታዊ ጋዜጠኝነት ላይሳካ ይችላል ብሎ ያቀረበው ምክንያት አንዱ የፖለቲካው ክበብ ምቹነት ነው:: መንግስት የሚከተለው የፖለቲካ ስርዓት ለልማት የማይመች ከሆነ ልማታዊ ጋዜጠኛው የሚዘግበው ነገር ስለማይኖር በዚህ ረገድ ላይሳካ ይችላል የሚለው ሲሆን በሁለተኝነት የሰፈረው የስጋት ምንጭ ደግሞ የፖለቲካ ስርዓቱ አለመመቸት ጋዜጠኛውን የገዢው ፓርቲ ፕሮጋንዳ መጠቀሚያ ያደርገዋል የሚለው ነው::

እነዚህ ሁለቱ የመንግስት ስጋቶችን አስመልክቶ የተለያዩ ፀሐፊያን ተቀራራቢ የሆነ ትንታኔ ሲሰጡ ይስተዋላል:: መንግስት ከፖሊስ ደክመንቱ ላይ ያስቀመጣቸው የልማታዊ ጋዜጠኛ ትርጉም እና ምንነት የተለያዩ አንድምታዎች አሏቸው:: አንደኛው ጋዜጠኛው ልማታዊ ታሪኮች ላይ ብቻ እንዲያተኩር መደረጉ ነፃነቱን ያሳጣዋል የሚለው ነው:: ጋዜጠኛው የተመረጡ ታሪኮች፣ በተመረጡ የመግባቢያ ቋንቋ እና ከተመሳሳይ ምንጭ ብቻ እንዲቀዳ መደረጉ ጋዜጠኛውን ከሙያው ስነ ምግባር ውጭ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪ የፖለቲካ መጠቀሚያ እንዲሆን ያስችለዋል:: ሌላኛው ስጋት ጋዜጠኛው ከላይ በሚቀርብለት መመሪያ ብቻ ስራውን እንዲሰራ መደረጉ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚነሱ ብሶቶች እና ሮሮዎች ድምፅ አልባ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል የሚለው መከራከሪያ ነው:: ‹‹ይህ የመንግስት አካሄድ አስቀድሞም አሁን ካለው የልማታዊ ጋዜጠኝነት ህልዮት ሞዴል ጋር በእጅጉ ይጣረሳል ይላሉ››::

## ከገንዘብ ቅጣት-ሞት?

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ኢህአዴግ ፕሬሱን ከአደባባይ ለማራቅ አዘውትሮ ከሚጠቀምባቸው ስልታዊ ጫናዎች በተጨማሪ ያፀደቃቸው ሁለት ህጎች ፕሬሱን ለማፈን የህግ ሽፋን ሰጥተውታል:: የመጀመሪያው ተሻሽሏል ተብሎ የፀደቀው የፕሬስ አዋጅ ነው:: ይህን አዋጅ አስመልክቶ በጊዜው ከነበሩት መሀከል ዘጠኝ የሚሆኑት የጋዜጣ አዘጋጆች የነፃውን ፕሬስ እንቅስቃሴ በመግታት ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚኖረውን ሚና ከማቀጨጭ በዘለለ የዜጐችን መረጃ ማግኘት ህገ-መንግስታዊ መብትን ይጨፈልቃል ሲሉ ተቃውሚቸውን ቢገልፁም አዋጁ ስራ ላይ ውሏል:: እንደ ብዙ የጉዳዩ ተንታኞች የአዋጁ አደገኛነት የሚገለፀው ቅጣቶችን በተመለከተ ያስቀመጣቸው ማዕቀፎች ናቸው:: ዶ/ር ቴሬሴ ሮስ የተባሉ ፀሐፊ እንደሚከራከሩት ለአነስተኛ ስም ማጥፋት እስከ መቶ ሺህ ብር የደረሰ ቅጣት በጋዜጠኞች ላይ መጣሉ ገዢው ፓርቲ ነፃውን

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# አለውክልና ግብር የለም



ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም

ስለግብር ስናገር ወደ አርባ ዓመት ሊሆነኝ ነው፤ ዛሬ ሁሉም ስለግብር ይናገራል፤ እንዲያውም ወሬው ሁሉ ስለግብር፤ ስለቫት እየሆነ ነው፤ ዱሮ እኔ የምጮኸው በገበሬው ላይ ስለተጫነው ግብር ነበር፤ የዛሬው ጩኸት በነጋዴው ላይ ስለተጫነው ግብርና ወደበላተኛው ስለሚተላለፈው ግብር ነው።

በፈረንጆች አንድ የታወቀ አባባል አለ፡- አለውክልና ግብር የለም --ተረት ሳይሆን ከፖለቲካ ፈላስፋዎቻቸው የመነጨ ቁም-ነገር ነው፤ ለአንድ አገር መንግሥት ገንዘብ እንደሚያስፈልገው ሳይታለም የተፈታ ነው፤ የአገርን ዳር-ድንበር ለማስከበር ወታደር ያስፈልጋል፤ የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ ለማስጠበቅ የፖሊስ ኃይል ያስፈልጋል፤ የሕግ አስተዳደሩን የሚያካሂዱ ዳኞችና የሕግ ሰዎች ያስፈልጋሉ፤ አስተዳደሩን በየደረጃው የሚያስኬዱት ብዙ ሰዎች ያስፈልጋሉ፤ ለትምህርት ቤቶች መምህራንና መጻሕፍት፣ ሌሎችም ነገሮች ያስፈልጋሉ፤ ለሀኪም ቤቶች ሀኪሞች፣ እቴዋዎች፣ ሌሎችም ባለሙያዎችና መሣሪያዎች ያስፈልጋሉ፤ ከነዚህ ሁሉ ጋር የውሃ፣ የመብራትና የመንገድ ነገሮች ሁሉ ሰዎች ያስፈልጓቸዋል፤ እነዚህ ሁሉ ሰዎች እንደሌላው ሰው ሁሉ መብላትና መጠጣት ብቻ ሳይሆን የተደላደለ ኑሮ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፤ ይህ ሁሉ ‹‹ያስፈልጋል›› ሳይታለም የተፈታ ነው።

አንድ ያስፈልጋል ያላልሁት በጣም የሚያስፈልግ ነገር አለ፤ ግን የአገዛዞች ሹማምንት ሁሉ ከጉዳይ የማይቆጥሩት የመኖሪያ ቤት ጉዳይ ነው፤ የመኖሪያ ቤት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ሹማምንቱ ዱሮም አሁንም ለራሳቸው እያንዳንዳቸው ለአምስት ቤተሰብ የሚበቃ ቤት በመስራታቸው ይረጋገጣል፤ ይሁን እንጂ በዝቅተኛ ኑሮ ላይ ለሚገኘው ሕዝብ በአቅሙ መኖሪያ ቤት ለመገንባት የሞከረ አገዛዝ የለም፤ ደርግ መሬቱን ነፃ በማድረግ ትንሽ ተቃርቦ ነበር፤ እንደሚመስለኝ ዋናው ምክንያት ትንንሽ ቤቶችን በመሥራት ብዙ የሚገሸለጥ አለመኖሩ ነው፤ አንድ ምስክርነት ልስጥ፤ በ1967 ግድም ቀበሌዎች እንደተመሰረቱ በየዋህነት ለሕዝቡ ጥቅም የሚያገለግሉ መስሎኝ የልማት ኮሚቴ የሚባለው ውስጥ ገባሁ፤ በባለሥልጣኖች እንደተለመደው ኮሚቴው የቀበሌው ችግሮች የሚላቸውን በመላ-ምት መዘርዘር ሲጀምር፣ ልክ እንዳልሆነ ተገንዝበን በእኛ ስብሰባ የቀበሌውን ሕዝብ ችግር በቅደም-ተከተል ልናውቀው አንችልም፤ ስለዚህ ራሱ ችግሩን ይናገር በማለት ተወሰነ፤ ሕዝቡን አንደኛ ችግር፣ ሁለተኛ ችግር፣… እያለ እስከአምስተኛ ችግር ድረስ እንዲገልጽ መጠይቅ ሠርተን ሰዎች በየቤቱ እየተዘዋወሩ እንዲሞላ ተደረገ፤ ውጤቱ ማንም የጠበቀው አልነበረም፤ አንደኛ ችግር ቤት፣ ሁለተኛ ችግር ሰገራ ቤት!

ከዚህ ተነስተን በጥሩ ሁኔታ በእንጨትና በጭቃ የሚሰሩ ቤቶች እቅድ አወጣን፤ ወጪውን ሁሉ አሰላን፤ ለነጠላ ሰዎች በአምስት ብር፣ ለባልና ሚስት በሃያ አምስት ብር የሚከራዩና በአስር ዓመታት ዋጋውን የሚመልስ አድርገን ለቀበሌው ስናቀርበው የቀበሌው ሱቅ ለሚባለው ገንዘቡን ሲሰጡ ለእኛ ከለከሉ፤ ቀረ! እኔም ከቀበሌ ጋር በየዋህነት የጀመርሁትን ግንኙነት አቋረጥሁ፤ ዛሬም ቢሆን ‹‹የመንግሥት ሌቦች›› ከፈቀዱ በዝቅተኛ ኑሮ ላለው ሕዝብ መጠነኛ ቤት በመጠነኛ ኪራይ ለመሥራት ይቻላል፤ ኮንደሚኒየም የሚባለውን አለማንሣቴ ረስቼ እንዳይመስላችሁ!

ጥያቄዎች የሚነሡት ገንዘቡ እንዴት ይሰብሰብ? እንዴት ይደልደል? የት የትና እንዴት ይከፋፈል? በሚሉትና ሌሎችም ጥያቄዎች ላይ ነው፤ የፈረንጆቹ አለውክልና ግብር የለም የሚለው ቁም-ነገር ሥራ ላይ የሚውለው እዚህ ላይ ነው፤ ማህበረሰቡ ወይም ህዝቡ ችግሩን ያውቃል፤ የችግሩን ቅደም-ተከተል ያውቃል፤ ስለዚህም እንኳ ገንዘብና ጉልበቱንም ቢሆን ለመገበር ዝግጁ ነው፤ ማናቸውም የሹማምንት ውሳኔ ላይ የችግሩ ባለቤት የሆነው ሕዝቡ በእውነት ተወክሎአል ወይ? በስራውስ ላይ እውነተኛ ተሳትፎ ነበረው ወይ? የመንግሥት ሌቦች የፈለጉትን፣ በፈለጉበት ጊዜና በፈለጉበት ቦታ እየሠሩ ደሀውን ከደሀነት እናድንሃለን ቢሉ ደሀው ከቁልቁለቱ መንገድ አይወጣም፤ ደሀው ግብሩን ይከፍላል፤ ከግብር በተገኘው ገንዘብ የሚጠቀመው ግን ሌላው ነው።

የተመረጡ ‹‹ደሀዎች›› በቴሌቪዥን ጨዋታ ቢያሳዩም ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው፤ የቴሌቪዥን ጨዋታው ወደአልጀዚራም መተላለፉ አስደናቂ አይደለም፤ ደሀነትን ለማጥፋት ሊወጣ የሚገባው ገንዘብ ለአንድ እበላ-ባይ ጋዜጠኛ ኑሮ ማዳበሪያ መሆኑ ያሳዝናል።

ሕጋዊ ግብር ሲባል የከፋዩ የገቢ መጠንና የኑሮ ሁኔታ መታየት አለበት፤ ለምሳሌ አንድ ሰው በዓመት አራት መቶ ብር ቢያገኝና የቤተሰቡ ቁጥር አምስት ቢሆን ከዚህ ሰው ላይ ምንም ያህል ገንዘብ በግብር ስም መውሰድ ወደወንጀል ይጠጋል፤ ልብስንና ሌላውን እንርሳና ለምግብ ብቻ ብናስብ ቤተሰቡ በሙሉ የሚያገኘው በቀን አንድ ብር ከአስር ሳንቲም ነው፤ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እኩል ከተካፈለ በቀን የሃያ ሁለት ሣንቲም ምግብ ያገኛል፤ ይህም ቁርስን ትቶ ለምሳ አስር ሣንቲም፣ ለራት አሥር ሣንቲም ይሆናል ማለት ነው፤ ይህንን ቤተሰብ ግብር ማስከፈል ወንጀል አይሆንም?

ደሀውን ገበሬ አስቡት፤ ምናልባት በኩርማን ሄክታር መሬት ላይ ሶስት ኩንታል ጤፍ ያመርት ይሆናል፤ ለምግብ ሳያስቀር ሶስቱንም ኩንታል እያንዳንዱን በስምንት መቶ ብር ሂሳብ ቢሸጠው ለእያንዳንዱ አባል የሚደርሰው አንድ ብር ከሠላሳ ሣንቲም ነው፤ ማሽላና ዘንጋዳ፣ ወይም በቆሎ የዘራው ያንን ያህል አያገኝም፤ ለጅምላ ሞት የሚያበቃ ችጋር አለመከሰቱ እርዳታ እያሉ ጥገኛነትን የሚያስፋፋ አገሮች በሚሰጡት እርዳታ ነው።

በአለፉት ሃያ ዓመታት ውስጥ ትልቅ እርምጃ (ወደፊት ይሁን ወደኋላ ባይታወቅም) የታየው ከህዝብ ገንዘብ የመሰብሰቢያው ዘዴ ነው፤ አልፎ አልፎ ከሚደረግ የደርግ ‹‹የእናት አገር ጥሪ›› በጣም የረቀቀና ፋታ የማይሰጥ ነው፤ ማንም አያመልጥም፤ በረሀብ እየተዝለፈለፉ ተማሪ ቤት የሚሄዱ ተማሪዎችም መዋጮ እንዲከፍሉ ይገደዳሉ፤ ልዩ ልብስ ገዝተው እንዲለብሱ ይገደዳሉ፤ ሕጋዊው ግብር ጭነቱ በዛ ሲባል ከሕግ ውጭ ያለው መገበሪያ እየተስፋፋ ነው።

ችጋር ወደሞት አፋፍ ላይ የሚያደርስ የደሀነት አዘቅት ነው፤ የሞት አፋፍ ላይ የቆመውን ግብር ማስከፈል ወይም መዋጮ መጠየቅ ደሀነትን ያስፋፋል እንጂ አይቀንሰውም፤ አለውክልና ግብር የለም የሚባለውንም ቁም-ነገር ይጥሳል።

# ስለአፄ ቴዎድሮስ የሥልጣኔ አባትነት

ዓለማየሁ ገላጋይ

በዕውቀቱ ስዩም ባለፈው ሳምንት በትህትናም በእውቀትም ‹‹ጨዋ›› የሆነ የአቋም ማጣጥፍ አስነበበን። ‹‹ዳግማዊት ጃፓን፣ ዳግማዊ ቴዎድሮስ›› የተሰኘው ይሄ መጣጥፍ በተሽኮርማሚነት አጠራጣሪ ሐተታ በመደርደር የእኔን ሐተታ ለመጠራጠር ሞክሯል። ‹‹የሁለት ሥልጡን ሕዝቦች ወግ›› በተሰኘ የቅድመ-ሣምንት ፅሁፌ ከእኛ አፄ ቴዎድሮስን፣ ከጃፓን አፄ ሙትስሒቶን፣ ከዘመን 1960 ዓ.ም. አነሳስቼ መቋጫዬን የከሸፈ ስልጣኔ የፈጠረውን ቁጭት አድርጌ ነበር። በዕውቀቱ ስዩም ጃፓን ከኢትዮጵያ፣ አፄ ቴዎድሮስ ከአፄ ሙትስሒቶ መነፃፀራቸው የጉሮሮ ቅርቃር ሆኖ እንዳልተዋጠለት በሚጠቁም መልኩ አንዳንድ ሐሳቦችን ጣል አድርጓል። ሐሳቦቹ ሲጠቃለሉ፡-

1. በጥንታዊት ጃፓንና በጥንታዊት ኢትዮጵያ መካከል ተመሳስሎ አለመኖሩ እንደውም መቃረኑ

2. ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ለውጥ ጠል መሆናቸው

3. ጥንታዊ ጃፓናውያን ለውጥ የሚያስጠላ ክፉ እድል ያልገጠማቸው መሆኑ

4. ዳግማዊ ቴዎድሮስ እንዳብዛኞቹ ዘመነ መሳፍንት ገገርዎች የአውሮፓን ስልጣኔ ለማስገባት ከመፈለግ ውጭ የስልጣኔ አባት የሚያሰኝ አዲስ ነገር አለማድረጋቸው

5. በተለይ ዳግማዊ ቴዎድሮስን የሞራል ስልጣኔ-ምሳሌ ማድረግ አብዝቶ ስህተት ላይ መውደቅ መሆኑንና ሌሎችንም ነጥቦች አንስቷል።

ዘርፍ ዘርፉንና ነገር ማቀጣጠያ ጭራሮውን አራግፈን ስናየው የበዕውቀቱ አንኳር ሀሳብ ይሄው ነው። እዚህ ላይ በዕውቀቱ እንደመስታወት ሰባሪ አንዴ በመወርወር ያንከሻከሸው ብዙ እውነት አለና ስንጥርጣሪው ሁሉ (ዋጋ ቢኖረውም) እየለቀሙ ና-ተከፈል ማለት ለጊዜም፣ ለጉልበትም፣ ለወረቀትም ፀር ነው። በዕውቀቱ ‹‹በጨዋዎች›› ዕውቀት የእልህ ዘገር የነቀነቀበት የጥንታዊት ጃፓንና የጥንታዊት ኢትዮጵያ አለመመሳሰል ማስረጃዎቹ እውነታን የሚያጣርሱና በሙያም የሚያውቃቸውን እንኳን በይሆነኝ የካዱ ናቸው። ለምሳሌ ይሄንን የማህበረሰብ ሥነልቡና (Social psychology) እውነታ እንዴት እንደጣሰ እንመልከት።

‹‹በጥንታዊት ኢትዮጵያና በንታዊት ጃፓን መካከል ከነበሩት ልዩነቶች አንዱ ስለለውጥ የነበራቸው አስተያየት ነው። ቀዳሚውን ማክበር አዲሱን መጠራጠር የኢትዮጵያውያን ጠባይ ነበር። ካዲሱ ብልሃት አሮጌውን ግራ መጋባት መምረጥ ከማያውቁት መልአክ የሚያውቁትን ሰይጣን የሙጥኝ ማለት ብሔራዊ መለዮ ነበር።››

ይሄንን ከእውነታ ጋር የተጣረሰ የማህበረሰብ ማንፀሪያ አንድ ለሥነ-ልቡና እውቀት ‹‹ጨዋ›› የሆነ ሰው በተናገረው ይቅርታ ባደረግንለት ነበር። ነገር ግን የሥነ-ልቡና ትምህርት ምሩቁ በዕውቀቱ ሆነ። በሥነ-ልቡና ትምህርት ጅማሬ ላይ ስለማህበረሰብ ደህንነት በሚያትተው ክፍል ውስጥ ማህበረሰብ በሙሉ አንዱ ካንዱ ሳይለይ ለውጥ-ጠልና አሮጌውን ሙጥኝ ባይ መሆኑ ተገልጧል። ኢትዮጵያ፣ ጃፓን፣ አውሮፓ… የሚል ፍረጃ ደንቅሮ በለውጥ ፈላጊና አል-ፈላጊነት የመመደብ የበዕውቀቱ ፍላጐት ከምን እንደመነጨ ግልፅ አይደለም። ይሁንና ‹‹ቀዳሚውን ማክበር አዲሱን መጠራጠር የኢትዮጵያውያን ጠባይ›› ብቻ ሳይሆን የመላው የሰው ልጅ ባህርይ ነው። በዕውቀቱ ‹‹ጥንታዊ ጃፓን ግን ለውጥን የሚያስጠላ ክፉ እድል የገማት አይመስልም›› በሚል የደረሰበት ድምዳሜ በሳይንስ ብቻ ሳይሆን በታሪክም ያልተደገፈ ሀሳብ ወለድ ነው። ለምሳሌ፡-

በ1614 ዓ.ም. ነጋሪት የተጐሰመበት የፊውዳላዊት ጃፓን አስቸኳይ አዋጅ በግልፅ ከሚያግዳቸው ነገሮች ውስጥ የክርስትና እምነት ማራመድ ዋነኛው ነበር። ይሄ እጋዳ እስከ 1889 ዓ.ም ድረስ ፀንቶ ቆይቷል። ከወጪ ሰዎች ጋር የንግድም ሆነ የሐሳብ ግንኙነት ማድረግ ሌላኛው በአዋጁ ከታገዱት ውስጥ ይቀሳል። ይሄን-ይሄን ስንመለከት ጃፓን እንደውም ከአለም ህዝቦች ሁሉ በተለየ ለውጥን በአዋጅ ያገደች፣ ድንበሯን የጠረቀመች ብቸኛዋ አገር ነች። በዕውቁ ጥንታዊ ኢትዮጵያንና ጥንታዊ ጃፓንን ነጣጥሎ ለማሰብ ብቻ ይሄንን እውነታ ገድፎ ፅፏል። ከዚህ ግድፈቱ ተነስቶም ባለሁለት ነጥብ አቋም ይዟል። ቃል በቃል ላስቀምጠው።

1. አንድ የአስተሳሰብ መስመር የሚለካው በጠቃሚነቱ እንጂ በአገር በቀልነቱ ወይም በማይረጋገጥ እውነቱ አይደለም።

2. አዲሱ የነባሩ ጠላት አይደለም። ‹‹የጐመን ምንቸት ውጣ የገንፎ ምንቸት ግባ›› የሚል የለውጥ መዝሙር አይሰራም።

እዚህ ላይ የበዕውቀቱ የአቋም መግለጫ ከምን እንደመነጨ ብቻ ሳይሆን ምን ለማለት እንደፈለገም ግልፅ አይደለም። አንድ አዲስ አስተሳሰብ ሲመጣ የአገር በቀል አስተሳሰቡ የሚጠቀመው የሰው ልጅ በተፈጥሮ ለውጥ-ጠል በመሆኑ ሳይቃረነው እንዲላመደውና እንዲያራምደው ማስቻሉ ላይ ነው። ጥንታዊቷን ጃፓንና አፄዋን ሙትስሒቶን አንስተን ያወዳደስነው ምዕራባዊውን ስልጣኔ በጃፓናዊው ነባር ስልጣኔ ቀስተውና አደጋግፈው ያለቅራኔ ፈጣን እድገት ማምጣት በመቻላቸው ነው "Japanesque" ይሰኛል። የበዕውቀቱ የአቋም መግለጫ ነጥብ 1 ግን የሶሻሊስቱ የለውጥ ዘመን የታየውን ስህተት ለመድገም ያቆበቆበ ወይም ከስህተቱ ያልተማረ ነው። ሩሲያዊ፣ ቤትናማዊ፣ አፍጋኒስታናዊ ወይም ቻይናዊ ባዕድ አስተሳሰብን በአገር በቀል አስተሳሰብ ፋንታ የመተካት ዕኑ ፍላጐት።

የበዕውቀቱ አቋም መግለጫ ነጥብ 2 ህብርና እውነታ የሌለው ነው። ‹‹አዲሱ የነባሩ ጠላት አይደለም›› ይላል። ካልሆነ ለምን ለውጥ አስፈለገ? ለውጥ (Change) በባህሪው የቅራኔና የጠላትነት ውጤት መሆኑን በዕውቀቱ ዘንግቶታል ወይም ሆን ብሎ ገድፎታል። አለበለዚያም ለውጥ የሚለውን እሳቤ የያዘው ከእግር ኳስ የተጫዋቾች ለውጥ ነው። እዚያም ተለዋጩ በለዋጩ አሰልጣኝ ላይ መነጫነጩ ይቀራል ብላችሁ?

በበዕውቀቱ ስዩም ፅሁፍ ውስጥ የእራስን አሳንሶ የመመልከት አባዜ ጉልቶ ይስተዋላል። ለምሳሌ ዶክተር እጓለ ገብረዮሐንስ ያቀረቡት ምርምር ያለ ሂስ መቀበል ጉዳት እንዳለው ጠቅሶ የበርትራንድ ረስልን ዘበታዊ ንግግር አገላብጦ ሳይመረምር ይውጣል። ጃፓናውያንን ለውጥ ተቀባይ አድርጐ ኢትዮጵያውያንን የአሮጌ ግራ መጋባት ቁራኛ ያደርጋል…

በእኔ አመለካከት ጥንታዊዎቹ ጃፓኖችና ጥንታዊዎቹ ኢትዮጵያውያኖች የለውጥ ጠል ባህሪያቸውና ለስልጣኔ የተነሱበት አግባብ ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን አንድ ነው። ለምሳሌ ጃፓኖች አንድ የሚታወቁበት ባህርይ አላቸው። ከእምነት አንፃር መጤውን ሃይማኖት ላለመቀበል የቻሉትን ሁሉ ማድረግ። ካልቻሉና ተፅዕኖ ከበዛባቸው እንዳለ ከመቀበል ይልቅ ከአገር በቀሉ ነባር እምነት ጋር አዋህዶ አንድ ላይ ማስኬድ። ለምሳሌ እስካሁን ድረስ ጃፓን ውስጥ አዳጋች የሆነው የሺንቶንና ከቡዲሒዝም እምነቶች መነጣጠል ነው። "History of Religion" የተሰኘ መጽሐፍ ይሄንን ርዕሰ ጉዳይ አንስቶ እንዲህ ይላል። "Buddhist images and other objects were removed from Shinto temples. But it was not possible to complety separate the two religions because they had merged together so thoroughly." (የቡድሒዝም ምስሎችንና ሌሎች ንዋየ ቅዱሳን ከሺንቶ ቤተመቅደስ የማስወገድ ተግባር ተከናውኗል። ነገር ግን ሁለቱን እምነቶች መነጣጠል ፈፅሞ የማይቻል ሆኗል። ምክንያቱ ደግሞ በጥብቅ የተዋሃዱ በመሆናቸው ነው።)

ወደኛም አገር ስንመጣ ተመሳሳይ የእምነት ባህርይ እናገኛለን። Reidulf Knut Molvaer የተባለ ተመራማሪ "Tradition and change in Ethiopia" በተሰኘ መፅሐፉ ይሄንኑ የነባርና የአዲስ እምነት መዋሃድ አንድ ምዕራፍ ሰጥቶ ተንትኖታል። "Syncretism in Christianity and paganism" በሚል ርዕስ

ይሄ የጃፓንና የኢትዮጵያ ተመሳስሎ በአንድ አይነት የስልጣኔ ብሒል እንዲሄዱ የሚጠቁም ጭምር ነው። ላለመቀበል የቻሉትን ሁሉ ያደርጋሉ ካልተቻለ የቀረው አማራጭ አዋህዶ መቀጠል ነው። የአውሮፓውን ስልጣኔ ለማስገባት ሲሞከር በእምነቱ በኩል የታየው እውነታ በዚህም ረገድ ተፈፃሚ ሊሆን ይገባው ነበር። የዚህ ሁሉ ማጠቃለያ ደግሞ በዚህ ዘመን የሚታየው ማንነትን አፈራርሶ በመቃብሩ ላይ ቻይናዊ ስልጣኔን የመገንባት ፍጭርጭሮሽ መሰረት እንደሌለው ማስገንዘብ ነው።

በዕውቀቱ ስዩም ሳያውቅ በስህተት፣ እያወቀ በድፍረት ከያዛቸው አቋሞች የከፋው ከአፄ ቴዎድሮስ ጋር ተያይዞ ደረስኩበት ያለው ድምዳሜ ነው። ቃል በቃል እንዲህ ይላል።

‹‹በእኔ አስተያየት፤ በዘመነ መሳፍንት የነበሩ አብዛኛዎቹ ገገርዎች ያውሮፓ ስልጣኔን ማስገባት ይፈልጉ ስለነበር ዳግማዊ ቴዎድሮስ በዚህ በኩል ልዩ ሊሆኑ አይችሉም።››

ታሪክ በመቅመል አፄ ቴዎድሮስን አሳንሶ የማሳየት ፍላጐት የቅጂ መብቱ የልዑል መኮንን እንዳልካቸው እንጂ የበዕውቀቱ ስዩም አይደለም። ልዑሉ ‹‹ጣይቱ ብጡል›› በሚል በ1958 ዓ.ም. በፃፉት ተውኔት ላይ አፄ ቴዎድሮስን ተኮናኝ ነፍስ አድርገው ስለዋቸዋል። ይሄንን የልዑሉን ድፍረት ባዕዱ Molvaer ሳይቀር ታዝቦ መኮንን እንዳልካቸው በፊትም ሆነ በኋላም ያልተሞከረ የማሳነስ ስራ ነው ብሎታል። እንግዲህ ከልዑሉ ወዲህ ደግሞ ብላቴናው በዕውቀቱ ሳምንት በሞላው ፅሁፉ አፄውን የማሳነስ አቋም ያዘ። በመሰረቱ ታሪክ እያጣቀሱ የማተለቅ ፍላጎትን የመወጣት አዝማሚያ እንዳለ ሁሉ የማሳነስ ጥማት ቢከሰት አስደናቂነት የለውም። እንደውም ቢያንስ-ቢያንስ ሀሳብ እርስ-በርሱ ተሟርዶ የሰላ ግንዛቤ እንዲፈጠር ያደርጋልና ጉዳትነት የለውም።

በዕውቀቱ የትኛው የዘመነ-መሣፍንት ገዢ በአፄ ቴዎድሮስ መጠንና አይነት ስልጣኔን ለማስገባት እንደፈለገ በግልፅ አልጠቆመም። ስልጣኔን የማስገባት ፍላጐት ጠበንጃና መድፍ በማስመጣት ተተርጉሞለት ከሆነ ታላቅ ስህተት ላይ እንደወደቀ ሊረዳው ይገባል። አፄ ቴዎድሮስ የስልጣኔ በር ከፋች ተደርገው እንዲታሰቡ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

# እናመሰግናለን

አዎን! የፍትህ አንባቢዎችን ከልብ እናመሰግናለን፡፡ በእርግጥ የምናመሰግነው ፍትህን ወደው እና ናፍቀው የሚያነቡትን ብቻ ሳይሆን ለመንቀፍ እና ህፀፅ ለማውጣት የሚያነቡትን አንባቢዎቻችንንም ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ነቃፊዎቻችን ሊነቅፉን የቻሉት ቢያንስ ጋዜጣችንን አንብበው ነውና፡፡ የሚያነብ ደግሞ (አመለካከቱ ምንም ይሁን ምን) ሊበረታታ እና ሊመሰገን ይገባዋል፡፡

የሆነ ሆኖ ፍትህ ከነገ በስቲያ ሚያዝያ 7 ቀን 2004 ዓ.ም. ድፍን አራት አመት ይሞላታል፡፡ የመጀመሪያዋ የፍትህ እትም ለንባብ የበቃችው በዕለተ ማክሰኞ ሚያዝያ 7 ቀን 2000 ዓ.ም እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እናም በአራት አመታት ውስጥ ምንም እንኳን ዳኛው /ፍርድ ሰጪው/ ህዝባችን ቢሆንም፣ ፍትህ ጥቂትም ቢሆን የራሷን አስተዋፅኦ ማድረጓን እኛም በልበ ሙሉነት ለመናገር እንችላለን፡፡

ፍትህ ስትመሰረት ዋነኛ አላማ አድርጋ የተነሳችው ‹‹ሀሳብን የመግለፅ መብት ያለገደብ›› በሚል መርህ ነው፡፡ ይህንን ግቧንም ከሞላ ጎደል ለማሳካት ችላለች፡፡ ወጣቱ ስለሀገሩ የፖለቲካ ጉዳይ ያለአንዳች ፍራቻ እና መሸማቀቅ በአደባባይ እንዲነጋገር ማበረታታት፣ ለህዝባችን አማራጭ፣ ነፃ፣ ታማኝ ሚዲያ መሆን፤ የውይይት መድረክ መፍጠር፣ ብሔራዊ እርቅ እንዲፈጠር አስተዋፅኦ ማድረግ፣ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ይመጣ ዘንድ አለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ማቅረብ፣ የፍትህ ስርዓቱ ነፃና ገለልተኛ ይሆን ዘንድ መደገፍ፣ የፖለቲካ ንቃተ ህሊናን ማጎልበት፣ በአጠቃላይ ድምጽ ለተነፈጉ፣ ፍትህን ለሚሹ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ድምፅ መሆን፣ ኢ-ህገመንግስታዊ እና ኢ-ፍትሃዊ ድርጊቶችን ለህዝብ ማጋለጥ፣ ትክክለኛ መረጃን በወቅቱ ማድረስ… የመሳሰሉት አላማዎቻችን ፍትህን ለመመስረት የተገደድንባቸው ናቸው፡፡ እንግዲህ ከእነዚህ አላማዎቻችን ምን ያህሉ እንደተሳኩ፣ ምን ያህሉ እንዳልተሳኩ ዳኝነቱ የህዝብ ነውና ዳኝነቱን ለህዝብ እንተዋለን፡፡


በፍትህ በኩል ግን ቀጣዩ አምስተኛ አመታችንን የምናከብረው ስህተቶቻችንን ቀርፈን፣ ድክመቶቻችንን አርመን እንዲሁም ከጥላቻ እና ከወገንተኝነት የፀዳ ጥንካሬያችንን አጎልብተን እንገኝ ዘንድ ከወዲሁ በለውጥ ጉዳና ላይ መሆናችንን ለአንባቢዎቻችን በማብሰር ነው፡፡ በተጨማሪም ምንም እንኳን ጋዜጣችን ትኩረቷን ፖለቲካው ላይ ያደረገች ቢሆንም ከዚህ ጎን ለጎን በቀጣይ ሌሎች ማህበራዊ አላማዎችንም ለማሳካት ጠንክራ ለመስራተ በዝግጅት ላይ ትገኛለች፡፡

የሆነ ሆኖ ፍትህ ዛሬም ድረስ ህልውናዋ ተጠብቆ እዚህ ልትደርስ የቻለችው በእናንተ ታማኝ አንባቢዎቻችን እገዛ እንደሆነ ስንናገር በኩራት ነው፡፡ ዛሬ የፍትህ የህትመት ኮፒ በአገራችን እየታተሙ ካሉ ጋዜጦች ትልቁ ሊሆን የቻለውም በአንባቢዎቻችን ቋሚ ተሳትፎ እንደሆነ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ እናም ፍትህ ተደራሽነቷ ከዚህ በእጅጉ ይልቅ ዘንድ፣ ጥንካሬዋም እንዲሁ ይበረታ ዘንድ የአንባቢዎቻችንን የተሳትፎ ድጋፍ በእጅጉ ትሻለችና እስከዛሬ አብራችሁን ለቆያችሁ አንባቢዎቻችን ነገም እልፍ እንደምትሆኑና ፍትህ የጀመረችውን እውነትን ያለምንም መደባባስ እና ፍርሃትን የማባረር ተልዕኮ ከግብ እንደምታደርሱት ከልብ እናምናለን፡፡ ለእስከዛሬው ድጋፋችሁም እነሆ ደግመን ደጋግመን እናመሰግናለን፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

## አስተያየት

# ማቆሚያና ገደብ ያጣው የምስኪኗ እናቴ ዕንባ!



**ከክንፈ ሚካኤል አበበ /አበበ ቀስቶ/ ከቃሊቲ ወህኒ ቤት**

የዘንድሮው የዓድዋ በዓል 116ኛ ዓመት ሲከበር በምኒልክ አደባባይ ለመገኘት እድሉን አላገኘሁም፡፡ ሆኖም ግን በቃሊቲ ወህኒ ቤት ውስጥ ሆኜ ዕለቱን ለማስታወስ ሲባል የተዘጋጀውን የኢቴቪን ልዩ ዝግጅት ለመከታተል እድሉን አግኝቻለሁ፡፡ እጅግ የተገረምኩት ደግሞ በዓድዋ ዘመቻ ላይ ታሪካዊ ጀግንነትና ገድል ከፈፀሙት መካከል አንዱ የሆኑት የእኔ የቅድመ አያቴ አኩሪ ታሪክና ተግባር ብኮራና ብደሰትም እርሳቸው ለሀገራቸው አንድነት፣ ለነፃነትና ለእኩልነት፣ ያደረጉት ተጋድሎ ዋጋ አጥቶ እኔ ልጃቸው ነፃነት አልባ ሆኜና ለነፃነት፣ ለፍትህና ለእኩልነት መቆርቆሬ ከወንጀል ተቆጥሮብኝ፣ የእኔ እያልኩት የእኔ ባልሆነው መንግስት ወህኒ መወርወሬ በእጅጉ አሳዝኖኛል፡፡ አሳፍሮኛል፡፡

ምን ይኼ ብቻ እንደ ቅድመ አያቴ ሁሉ ከአያቶቼ አንዱ ደግሞ በአምስቱ ዓመት የአርበኝነት ዘመን እምቢ ሀገሬንና ነፃነቴን ሲሉ፤ ከሌሎች መሰል አርበኞች ጋር በመሆን ለፋሽስት ኢጣሊያ መንግስት አልገዛ፣ አልሰግድና አልንበረከክ ማለታቸው ብቻ ከወንጀል ተቆጥሮ አዚናራ ተብሎ በሚጠራው የፋሽስቱ ወህኒ ቤት ተወርውረው ፍዳቸውን ለመቁጠር በቅተዋል፡፡ አያት-ቅድመ አያቶቼ ይህን ሁሉ ያደረጉት ከራሳቸው አልፈው ለእኔ ዛሬ በግፍ ለታሰርኩት የልጅ ልጃቸው ነፃነትና እኩልነት ከልብ በማሰብ የተነሳ መሆኑን ማንም ሰው ሊክደው የማይችለው የዘመን ሀቅ ነው፡፡ እድለቢሱ እኔ ግን ፋሽስት ኢጣሊያ ከተባረረ ከብዙ ዓመታትም በኋላ የአያት ቅድመ አያቶች ልፋትና ትግል ፍሬ አጥቶና መክኖ የአምባገነኑ የኢህአዴግ መንግስት የግፍ ሰለባ ሆኜ ወደ ዘብጥያ ተወርውሬ /ተጥዬ/ እገኛለሁ፡፡

ልክ እንደ እኔ ሁሉ እድለቢሷ እናቴም ብትሆን አባቷ፣ አያቷና ቅድመ አያቷ ለታገለሉት ነፃነትና እኩልነት ተቋዳሽ ለመሆን አልታደለችም፡፡ በተለይም የእኔ እናት በተከታታይ በአገራችን የነገሱትን አምባገነኖች የግፍና የጭካኔ ተግባር እንደ ሆሊውድ ፊልም ስትኮመኩም ለመኖርዋ ታሪክዋ ህያው ምስክር ነው፡፡

ይህች የእኔ እናት በ1953 ዓ.ም. የቀዳማዊ ኃ/ሥላሴን መንግስት በመቃወም ተካሂዶ በከሸፈው መፈንቅለ መንግስት ጦስ የተነሳ በዘመኑ በነበሩ ዳኞች በተሰጠ የግፍ ውሳኔ የቅርብ ዘመዶቿ የስቅላት ፍርድ በአደባባይ ሲፈፀምባቸውና የተረፉትም ሀገር ጥለው ሲሰደዱ በቅርበት አይታለች፡፡ ሰምታለች፡፡ ከዚያም በ1966 ዓ.ም. በሀገራችን በፈነዳው ግብታዊ አብዮት ወደ መንበረ ስልጣኑ ብቅ ያለውና ንጉሱን ከስልጣን ያስወገደው ወታደራዊው የደርግ መንግስት ዴሞክራሲያዊ ለውጥን እንደሚያመጣና በህዝብ ለተመረጠ መንግስት ስልጣኑን አስረክባለሁ በማለት የገባውን ቃል ኪዳን ሲያፈርስና ቃሉን ሲበላ ተመልክታለች፡፡

መቼ ይኼ ብቻ ይህች እናቴ በዘመነ ደርግ በ1969 ዓ.ም. አካባቢ እንኖርባት በነበረችው የገጠር ከተማ በዘመኑ የተቀናቃኝ ፓርቲ አባል በመሆኑ ብቻ ከሚሰራበት መ/ቤት በግፍ ተባርሮ በወቅቱ በቤት ውስጥ ያለ ስራ የተቀመጠውን እንጀራ አባታችንን ለመያዝ በመጣ ግብረ ኃይል ቤታችን በፍተሻ ሲተራመስና ሲታመስ የእንጀራ አባታችንም በወቅቱ ለነበረው ለወረዳው ፖሊስ አዛዥ እጁን ሰጥቶ በቁጥጥር ስር በመዋሉና በመታሰሩ ለተወሰኑ ጊዜያት ቀለብ የማመላለሱን ስራ ተያያዘችው፡፡ በእሱ ይብቃ ያላላት እናቴ በወቅቱ በአገራችን በሰፈነውና በነገሰው ገላጋይ ያጣ፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ገደብ ያጣ ንትርክና ትርምስ የተነሳ የእህቶቿ ልጆችና የቅርብ ዘመዶቿ በመታሰራቸው ከጣቢያ ጣቢያ፣ ከወህኒ ቤት-ወህኒ ቤት፣ እየተንከራተተች መጠየቅና ቀለብ ማመላለስ መደበኛ ስራዋ ሆኖ ከዚሁ ጋር ልጆቻቸውን በግፍ ተነጥቀው የልጆቻቸውን ሬሳ በመግዛትና በመቅበር መሪር የሀዘን እንባ ያፈሰሱ እናቶች ጋ ለቅሶ መድረስና ማስተዛዘንንም አቋርጣ አታውቅም ነበር፡፡

እንደ ዕድል ሆኖ ግፈኛው የደርግ ስርዓት ወድቆ የኢህአዴግ መንግስት ሲተካና እሱም እንደቀደምቶቹ እንደውም ከእሱ ብሶ በተሻለና በአማረ ቋንቋ የዴሞክራሲና የፍትህ ብቸኛው ጠበቃ እኔ ነኝ እያለ ምሎ ሲገዘትና በአደባባይ ሲለፍፍና ሲያውጅ ስትሰማ እውነት መስሏቸው ከተደሰቱት እናቶች መካከል አንዷ ነበረች ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፡፡

እንደውም ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ ግንቦት 19 ቀን 1986 ዓ.ም. ለቀይ ሽብር ሰማዕታት መታሰቢያነት ለሚቆመው ሐውልት የመሰረት ድንጋይ ሲያኖሩ ‹‹ከእንግዲህ ወዲያ እንደ ደርግ ዘመን የልጆቻችሁን ሬሳ በገንዘብ የምትገዙበት ስርዓት ተመልሶ አይመጣም፡፡ የልጆቻችሁም ሬሳ እንደ ውሻ ሬሳ ጉዳና ላይ አይጣልም›› ሲሉ ቃል መግባታቸው እውነት መስሏት ከልብ መደሰቷን አስታውሳለሁ፡፡ ሲፈጥራት ለደስታ አላደላትም መሰለኝ ይህ ደስታዋ ረጅም ጊዜ አልዘለቀም፡፡ ዴሞክራት ነኝ ባዩ የኢህአዴግ መንግስት የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የእኩልነት ጥያቄ ያነገቡ ንፁሃን ኢትዮጵያውያንን ዕድሜና ፆታ ሳይለይ በአግአዚና በፌደራል ጥይት ግንባር ግንባራቸውን እያለ ጉዳና ላይ ሲደፋቸውና ጉዳናው በንፁሐን ኢትዮጵያውያን ደም ሲረጥብና ሲቀላ በማየቷና በመስማቷ፣ አቶ መለስም ቃላቸውን በማጠፍና በመካድ የሟች ህፃናትን አስከሬን ከየሆስፒታሉ ገንዘብ እያስከፈሉ በመሸጥ ወላጆቻቸውን ሲያስነቡና ሲያስለቅሱ በመታዘቧ ፍፁም ከአዘኑትና የምር በማንባት ፈጣሪያቸውን ከአማረሩት ኢትዮጵያውያን እናቶች መካከል አንዷ ናት፡፡

አቶ መለስም የንፁሃን ኢትዮጵያውያንን ደም በከንቱና በግፍ በማፍሰስ በ17 ዓመቱ የትጥቅ ትግል ወቅት ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለፍትህ ሲታገሉ የወደቁትን ሰማዕታት ለማሰብ በመቀሌ፣ በባህር ዳርና በናዝሬት የቆሙትን የሰማዕታት ሐውልቶች በቁማቸው አፈረሷቸው፡፡ የሰማዕታትንም ደም ደመከልብ አደረጉት፡፡ እኛም የሰማዕታቱ ሐውልት በቁሙ ሲፈርስ በትዝብት አይተናል፡፡

የአቶ መለስ አስተዳደርና በ1997 ዓ.ም. የተካሄደውን የምርጫ ውጤት መጭበርበርን ተከትሎ በተነሳው የህዝብ ድምፅ ይከበር፣ የሚል ጥያቄና ህዝባዊ ቁጣ ሳቢያ ከነጋደኞቻቸው በወሰዱት እርምጃ የጉዳቱ ሰለባ ከሆኑት እጅጉ ብዙ ኢትዮጵያውያን መካከል አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡

በ1998 ዓ.ም. መጀመሪያ ላይ በፌደራል ፖሊስ አባላት ዘግናኝ የሆነ የግድያ ሙከራ ተካሂዶብኝ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ ሆኖ ተርፌአለሁ፡፡ የፌደራል ፖሊስ አባላት በምሽት በዱላና በሰደፍ ደብድበውኝ የለበስኩት ልብስ በደም ጨቅይቶና በራሴ ደም ርሼ ሳለሁ ጭነው ሲወስዱኝ ከነበረው የፌዴራል ፖሊስ ፒክአፕ መኪና ላይ ኮልፌ መብራት ኃይል ድልድይ ስር የሞትኩ መስሏቸው ወርውረውኝ ሲሄዱ ያዩ ኢትዮጵያውያኖች በአቅራቢያው በሚገኝ ዘመዴ ክሊኒክ አሳክመው በኋላም ለዚያችው እናቴ ደውለው ተደብድቦ ተጥሎ አግኝተነው ነው ኑና ውሰዱት ብለው ነግረዋት በተዓምር ከሞት የተረፍኩትንና በሞትና በህይወት መካከል ያለሁትን ልጇን አንስታ ወደ ቤት ለመውሰድ በቅታለች፡፡

ይህም ብቻ አይደለም አሁን ደግሞ በ11/01/2004 ዓ.ም. ሊይዙኝ ሲፈልጉ እዚያው ባለፈው ደብድበው ሞቷል ብለው የጣሉኝ ስፍራ ላይ ከዓመታት በኋላም እንደገና የኢህአዴግ ደህንነቶች በሚነዱት ፓጃሮ መኪና ገጭተው በመግደል በመኪና አደጋ የደረሰ ድንገተኛ አደጋ ለማስመሰል ሞክረው በእኔ ጥበብ ሳይሆን በእግዚአብሔር ብርታት ልተርፍ ችያለሁ፡፡

ይህች የእኔ እናት የኢህአዴግ የስልጣን ዘመን 20 ዓመታት ከሞላው በኋላም እንኳን እኔን ልጇን የዴሞክራሲ፣ የፍትህና የእኩልነት ጥያቄ አንግበሃል፣ ስለኢትዮጵያና ስለአንድነቷ አስበሃል፣ ለህዝብ ጥቅም ተቆርቁረሃል፣ በሚል በሽብርተኝነት ፈርጆ በደም የፀደቀ ነው የሚለው የራሱ ህገ መንግስት ከሚፈቅደውና ከሚያዘው ውጭ ዘብጥያ ስለወረወረባት ቀድሞ በደርግ ዘመን ታደርገው እንደነበረው ሁሉ አሁንም በእርጅና ዘመኗ የሚያዝንላትና የሚያሳርፋት አጥታ አንዴ ማዕከላዊ አንዴ ቃሊቲ እየተንከራተተች ቀለብ ማመላለሷን ቀጥላለች፡፡ ቴዲ አፍሮ ‹‹አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ›› ሲል በምፀት ያዜመው ይህን የሀገር ሃቅ አይደለምን? ይህች ያልታደለችው የእኔ እናት የሚሊዮን ሀዘንተኛ ኢትዮጵያውያን እናቶች ምርጥ ማሳያና ምርጥ ምሳሌ ናት፡፡

ምስኪኗ እናቴ ሚሊዮኖችን በግፍ ውሳኔያቸውና ፍርዳቸው አስነብተውና አስለቅሰው እንዳለፉት የንጉሱና የደርግ ዘመን ዳኞች ሁሉ የዛሬው የእነርሱ ተተኪ የሆኑት የአምባገነኑ የኢህአዴግ ፍ/ቤት ዳኞች በእኔ በልጇ ላይ የሚበይኑትን እና የሚያነቡትን ግፍና ጭካኔ የተሞላበትን የፍርድ ውሳኔያቸውን ለመስማት ወደዚሁ ፍ/ቤት ደከመኝና ሰለቸኝ ሳትል በመመላለስ ላይ ናት፡፡ እነሱም ይህን የግፍ ፍርዳቸውን አናሰማም እንደማይሏትና የጭካኔ ፍርዳቸውን በማንበብ እንደሚተባበሯት ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ እንደሷ ሁሉ እኔም ለመስማት ጓጉቻለሁ፡፡

ከዚህ በላይ የጠቀስኩት ሃቅ የሚያስረዳው በሀገራችን ለዘመናት በዙፋኑ ላይ የሰውና የልብስ ለውጥ እንጂ የአስተሳሰብ፣ የአመራርና የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለውጥ እንዳልመጣ ነው፡፡ እናም እባካችሁ መቼ ይሆን በምንፈልገውና በምናምነው የእኛ በሆነ ስርዓትና የአስተሳሰብ ጥበብ የምንመራው? የምታውቁ ንገሩኝ፡፡

ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት አያት ቅድመ አያቶቻችን ዛሬ በራሳችን ሰዎች ጭቆና ወድቀን ለምንማቅቀው እድለ ቢስ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ነፃነትና ለሀገር አንድነት ያደረጉት ትግልስ ፍሬ አፍርቶ የሀገራችንና የነፃነታችን ባለቤቶች የምንሆነው መቼ ነው?... መቼ ነው? … መቼ ነው?

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!

# ፍትህ ጋዜጣ

በማስተዋል ህትመት ማስታወቂያ ስራድርጅት
በየሳምንቱ የሚታተም

**የአሳታሚው አድራሻ**
አራዳ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12
የቤት ቁጥር አዲስ
ፒያሳ ራስ መኮንን
ድልድይ አጠገብ

**ሥራ አስኪያጅ**
ማስተዋል ብርሃኑ

**ዋና አዘጋጅ**
ተመስገን ደሳለኝ
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ ጀሞ
ሳይት የቤ.ቁ. 012

**አዘጋጆች**
ሙሉነህ አያሌው
ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

**ከፍተኛ ሪፖርተሮች**
መሐመድ ነስሩ
ኤልያስ ገብሩ

**ሪፖርተር**
ሰውዓለም ታዬ

**አምደኞች**
ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም
አለማየሁ ገላጋይ
ጌታቸው ታምራት
ዳንኤል ተፈራ
ቅጣው እጅጉ
ታዲዮስ ታንቱ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ሀብታሙ ታደሰ
ቤቴልሄም አመነሸዋ

**የሽያጭ ሰራተኞች**
ደለለኝ ሙሉጌታ
ታመነ ደገፋ

0911 928401
0911 712361
011 8951856
✉ 110744

E-mail:
fetih_gazeta@yahoo.com

www.fetehe.com

**አታሚ**
ብርሃንና ሰላም
ማተሚያ ድርጅት
ክ/ከተማ:- አራዳ
ቀበሌ:- 17
የቤት:- 984

# የፍትህ መንገድ-ከአሲምባ እስከ ቀራኒዮ



ተመስገን ደሳለኝ

አቤት! እንደምን ያለ ጉዞ ነው? አድካሚ፣ ፈታኝ፣ አስፈሪ፣ አደናቃፊ… ብቻ ዙሪያው በአደጋ የተሞላ ነው። ልክ እንደ ጦር ሜዳ። በእርግጥ ጦር ሜዳን በፊልም እና በቴሌቪዥን ካልሆነ ገፅ-ለገፅ አይቼ አላውቅም። ሆኖም በጣም አስፈሪ እና ከሞት ጋር ‹‹አኩኩሉ›› የመጫወት ያህል እንደሆነ ለማወቅ አይቸግረኝም።

ለዚህም ነው በጦር ሜዳ ‹‹ሞት እርካሽ ነው›› ሲባል ግነት እንዳይመስልህ የምልህ። ምንአልባት ከጎኑ ከሻጠው ኮዳ ውሃ ያስጎነጨህ ጓደኛህ ኮዳውን ከመመለስህ በፊት ሞቶ ወይም ሊሞት ሲያጣጥር ልታገኘው ትችላለህ። ለምን? በቃ! በጦር ሜዳ ሞት ከአይነ እርግብግቢት የፈጠነ ነዋ። የጦር ሜዳን መከራ ይበልጥ የሚያበዛው ደግሞ ላለመሞት የሚደረገው ግብግብህ ከጠላት ጋር ብቻ አለመሆኑ ነው። ከወገንም በኩል የሚነሳ የሞት መልዕክ አለና።

እናም ድንገት ወደ ውጊያ ከመግባትህ በፊት የተጠመደ ፈንጅ ታከሽፍ ዘንድ አለቃህ ይመርጥሃል። (ወዳጄ ‹‹ይመርጥሃል›› ስልህ ለሹመት እንዳይመስልህ፣ በፈንጂ ላይ ተረማምደህ ስጋና አጥንትህ ተበጣጥሶ ለሌሎች ወታደሮች መንገድ ትጠርግ ዘንድ ነው-የመረጠህ) አየህ! በጦር ሜዳ ሞት የቅርብ ጓደኛህ ብቻ ሳይሆን ጥላህም ነው። ጥላ ደግሞ ስትሄድ ይሄዳል፣ ስትቆም ይቆማል። ሞትም እንዲያ ቅርብ ነው።

ዛሬ የምተርክልህ የጉዞ ገድልም ከዚህ በማይተናነስ መልኩ በአደጋ የተሞላ ነው ስልህ እመነኝ አላጋነንኩትም። በፈንጅ የታጠረ ነው። ይህን ከጦር ሜዳው ፈንጅ ወረዳ የሚለየው እንደ ጦር ሜዳ ፈንጅ መቀበሩን የምታውቀው ጓደኛህ ተንከባሎበት ሲበጣጠስ አለማየትህ ብቻ ነው። እዚህ በግልፅ በመንግስት ሚዲያ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ራሳቸው ‹‹አሁን ቀዩን መስመር አልፈሃል››፣ ‹‹11ኛው ሰዓት ላይ ደርሰሀል››… ይሉሀልና። ያን ጊዜም ሁለት ስሜቶች ይፈጠሩብሃል ‹‹መራድ›› ወይም ‹‹በጽናት መቆም››። ግና የምትጓዘው ለሀገርና ለህዝብ እስከሆነ ድረስ ለምን ትርዳለህ? ጥያቄው ይህ ነው፣ መልሱም በእጅህ ነው።

ፍትህ ስትመሰረት ምንም አልነበረም። በመስራቾቿ እጅ ማለቴ ነው። ነገር ግን ከምንም በላይ አንድ ነገር ነበረን። አላማ የሚባል። ያ አላማ መኖሩ ነው፣ የፍትህን ጅማሮዋን ብቻ ሳይሆን መጨረሻውንም አውቀን እንድንገባ ያደረገን። እናም ስንጀምር መድረሻችንን እናውቀዋለን። መንገዳችንም በመሰናክል ናዳ የተሞላ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን። መጓዛችን አይቀሬ እንደሆነም እናውቃለን። ከቶም ምንም ነገር ከመድረሻችን ሊመልሰን እንደማይችል እናውቃለን። እስርም፣ ሞትም፣ ጫናም… ። ለነገሩ እነዚህ ሁሉ ከሀገር እና ህዝብ በታች ናቸው። እናም እልሀለሁ ጉዳዩ የሀገር እስከሆነ ድረስ፣ ተጠቃሚው ህዝብህ መከራውም ስለምትውዳት ሀገር እስከሆነ ድረስ የመረጥከውን መንገድ ይዘህ መጓዝ እንጂ የምትከፍለው ዋጋ ሊያሳስብህ አይገባም።

በእርግጥ የፍትህ ፈተና ይህ ብቻ አይደለም፣ ከዚህም ይሻገራል። ነባር የፍትህ አንባቢዎች እንደሚያስታውሱት ፍትህ ቀኗን ጠብቃ ለንባብ የማትበቃበት ጊዜ ነበር። ለአራት ሳምንት ያህል ያልታተመችበት ጊዜ ሁሉ አለ። በቂ የገንዘብ አቅም አልነበራትምና። በአናቱም ያች ሚጢጢዋ የፍትህ ቢሮ ከአንዴም ሁለቴ ተዘርፋለች። የሁለተኛው ዝርፊያ ለፖሊስ ቢመለከትም እስከዛሬም ድረስ ዘራፊዎቹን አየን ያለ የለም።

ሌላው ፈተና ደግሞ ከቤተሰብህ እና ከወዳጆችህ የሚመጣው ጫና ነው። ሆኖም እንዲህ አይነቱን ፈተና በቀላሉ ማለፍ ትችላለህ። ‹‹ይቅርብህ፣ ተው…›› ለሚሉህ እናትና አባትህ አሊያም ሌሎች የቤተሰብ አባላት ‹‹ከሀገር አትበልጡም›› ብለህ በመመለስ ማለቴ ነው። ይህም አልገባቸው ካለ እንዲህ ስትል ዘምርላቸው፡-

እናት አባት ቢሞት በሀገር ይለቀሳል
እህት ወንድም ቢሞት በሀገር ይለቀሳል
ሀገር የሞተ እንደው ወዴት ይደረሳል…
አዎን! ወዴትም አይደረስም።

እንዲሁም እንዲህ ብለህ አትፃፍ፣ መንግስት ሀይለኛ ነው፣ ፖለቲካ ኮረንቲ ነው፣ ገለመሌ ለሚሉ ወዳጅ ዘመድ ደግሞ ከህገ-መንግስቱ ውስጥ ሀሳብን ያለገደብ መግለፅ እንደምትችል የሚፈቅደውን አንቀፅ ድምፅህን ከፍ አድርገህ አንብብላቸው። ከፍ አድርገህ…

የሆነ ሆኖ ነገ ድፍን አራት አመት የሚሞላት ፍትህ እዚህ የደረሰችው በ‹‹መራድ›› እና በ‹‹መጽናት›› ወጀብ ከወዲህ ወዲያ እየተላጋች ነው። በእርግጥ እንዲህ ያለው አድካሚ እና ፈታኝ ጉዞ ነገም ይጠብቃታል። አደጋውን አስፈሪ የሚያደርገው ደግሞ ከቀን ወደ ቀን የመሰናክሉ አይነት መጨመሩና መደደሩ ነው።

ማን ነበር ህዝቡን ከረጅም ጉዞ በኋላ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያደረሰው? ሙሴ ይሆን? የለም የለም የሙሴ ጉዞ ለእኛ አርዕያ አይሆነንም። ሙሴ የታገለው ‹‹ህዝቤን ልቀቅ›› ብሎሃል እያለ ነውና። የእኛ እንዲህ የሚል መዕልክት አስተላለፊ ‹‹ኃይለኛ›› የለውም። ያለው ይህ የኔ ትውልድ (እኔና አንተ) ነው። እናም እኛው ራሳችን ነን ‹‹በቃን! ልቀቁን›› እያልን ያለነው ወይም የምንለው። ታዲያ ማን ይሆን ህዝቡን ከረጅም ጉዞ በኋላ ‹‹ከንአን›› ያደረሰው? የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ መስራቾች ናቸው ብትል አልዋሸህም። ነገሩም እንዲህ ነው፡-

ከዛሬ 80 አመት በፊት CCP የተባለው የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ፣ ከወቅቱ የቻይና ገዢ ፓርቲ “Kuomintang” ጋር ለህግና ለስርዓት ያስቸገሩትን በመላ ቻይና የነበሩ የጦር አበጋዞችን በትብብር ድራሻቸውን ለማጥፋት ይስማማል። በስምምነታቸው መሰረትም በየአጥቢያቸው ትናንሽ ንጉስ ሆነው አልገዛም ያሉትን የጦር አበጋዞች ከግራና ቀኝ አጥቅተው ያጠፋሉ። ከዚህም በኋላ ኮሚኒታግ ቃሉን አጥፎ የተቀጣ ፊቱን ወደ CCP ያዞራል። ይህን ግዜ የመንግስት ሀይል ከአቅማቸው በላይ እንደሆነ የገባቸው ማኦ ዜዱንግ እና ጓደኞቹ ከከተማ ወደ ገጠር ሸሹ። ዛሬ በቻይናዊያን እንደገድል የሚነገርለትን Long march (ረዥሙ ጉዞን) በዚህ አስገዳጅ ሁኔታ ነው CCP የተጓዘው። የጉዞውም እርቀት 11 ሺ ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ከዚህ በኋላም CCP ራሱን አጠናከረ። የጥንካሬያቸው ምንጭ ደግሞ ለአንድ አመት ያህል በፈጀው ጉዟአቸው የሚበሉት አጥተው መርዛማ ቅጠል እየበሉ ሳይቀር መጓዛቸው ብቻ ሳይሆን ከጉዞው በኋላ ያደረጉት ስር ነቀል ተሀድሶ ነው። ከዚህ በኋላ ነው CCP በድል እየገሰገሰ በሽንፈት ለቆት ወደሄደው ከተማ የተመለሰው። እነሆ ያ ፓርቲ ዛሬም በስልጣን ላይ አለ። ምን አልባት፣ ምንአልባት ግን በዛ አስቸጋሪ ጉዞ ቢበገር ኖሮ፣ ዛሬ CCPን እንኳ እኔና አንተ ምሳሌ ልናደርጋቸው ቀርቶ ቻይናውያንም አያውቁትም ነበር። ይህ ነው አይበገሬነት።

ሌላም በፈተና ከተሞላ ጉዞ በኋላ ታሪክ የሰራ ድርጅት አለ፤ ህወሓት። ህወሓት ለ17 አመት ያህል ተጉዟል። ያውም በመሳሪያ፣ በሰው ሀይል እና በስልጠና በእጅጉ ከሚበልጠው ከቀድሞ መንግስት ወታደሮች ጋር እየተዋጋ። እናም ብዙ የገደለ ሞትን ያሸንፋል እንዲሉ ህወሓትም ከዚህ ሁሉ ጉዞ በኋላ የመንግስቱን መንበር ያዘ። ነገር ግን የህወሓት ጉዞ እንደ CCP የተሳካነው ማለት አንችልም። ምክንያቱ ደግሞ ከህወሓት መስራቾች አብዛኞዎቹ ዛሬም በሌላ ረጅም፣ አሰልቺ እና ፈታኝ ጉዞ ላይ መሆናቸው ነው። …አረጋዊ በርሄ፣ ግደይ ዘራፅዮን፣ ስዬ አብርሃ፣ ገብሩ አስራት፣ አወአሎም ወልዱ፣ አረጋሽ አዳነ፣ አስገደ ገብረሥላሴ፣ አለምሰገድ ገ/አምላክ… ህወሓትን መስርተው የ17 አመቱን ጉዞ የመሩ ናቸው። ሆኖም ዛሬም በሌላ ጉዞ ላይ ይገኛሉ። ህወሓትን ይዘን የተጓዝነው ጉዞ የስህተት ጉዞ ነው በሚል ማለቴ ነው። እንደምራቂ ደግሞ የህወሓት የአማርኛ ተናጋሪ ክንፍ የሆነውን ብአዴንንም ብታየው ከላይ የነበረው አመራር አሁንም በአዲስ ጉዞ ላይ ነው። በእርግጥ የብአዴን ሰዎች እየተጓዙ ነው ስልህ የታምራት ላይኔንም ጉዞ ከዚህ እንዳታያይዘው። የእርሳቸው ለፅድቅ ነውና። መሰረቱም ምድራዊ ሳይሆን ሠማያዊ ነው። ምንጩም ፖለቲካ አይደለም፤ የእስር ቤት ‹‹ራዕይ›› እንጂ።

ፍትህ ስትመሰረት ረጅምና የፈተና ጉዞ እንደሚጠብቃት መስራቾቿ ያውቁ እንደነበር ተነጋግረናል። አውቀውም ነው የገቡበት ብዬሀለሁ። ሆኖም ፍትህ እንዲህ ሄዳ ሄዳ ብቻ የመሆን ዕዳ ላይ ትወድቃለች የሚል እሳቤ ግን አልነበራቸውም። የሆነው ግን እንዲያ ነው። የተለያዩ የሚታዩና የማይታዩ አደጋዎችን ተቋቁማ፣ አንዳንዴም እየተቸነከረች፣ አንዳንዴም እየተሸራረፈች ዳገቱን ለመጨረስ ግብ ግብ ተያይዛለች። ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በአንድ ወቅት በዚህችው ፍትህ ላይ በፃፉት ፅሁፍ ‹‹ዳገት ላይ ሰው ጠፋ›› ብለው ነበር። ፕሮፍ ልክ ናቸው። ዛሬ ሀገሬ ዳገቱን ጨርሶ ከገደሉ ስቦ የሚያወጣትን አላገኘችም። ምክንያቱ ደግሞ በብዙ የሚጠበቀው አንዳንዴም ገና ከታች፣ አንዳንዴም ከዳገቱ ወገብ እየቀረ ጣሯም መከራዋም ትውልድ ተሻጋሪ እየሆነ ነው። …እንዴት ያማል መሰለህ ትውልድ ተሻጋሪ መከራ? የእኔና የአንተ ትውልድ ባለፉት ተከታታይ ትውልዶች ያልተከፈለ ዕዳ ተሸክሟል። የሸክማችን ግዝፈት መነሾም ይኸው ይመስለኛል። እንደቅርስ መከራን ማውረስ…

የፍትህም ጉዞ ቢሆን ዳገቱን ለመውጣት በትግል ላይ ነው። በእርግጥ መከራው እና ድካሙ በአይነትም ሆነ በአሰቃቂነት የሚጨምረው ወደፊት በተጓዝክ ቁጥር ነው። ዳገቱን ለመጨረስ በተጓዝክ ቁጥር አደጋውም እየበዛ ይሄዳል። የታዘዘውም ያልታዘዘውም የአቅሙን መሰናክል ይፈጥርብሃል። በየቀኑ መቸንከር፣ በየቀኑም ከችንካር ወርዶ ወደፊት፣ ወደፊት፣ ወደፊት… እንዴት ፈታኝ መሰለህ? እንዴት ብርክ ፈጣሪ መሰለህ? እናም የፍትህ (የነፃ ፕሬስ) ጉዞ እንዲህ እንደዋዛ ‹‹ውሾቹ ይጮኻሉ፣ ግመሉ ጉዞውን ቀጥሎአል›› ብለህ የምታልፈው እንዳይመስልህ። እውነታው ተቃራኒው ነውና። የሚናከስ እንጂ የሚጮህ ነገር አትሰማም። ስለዚህም ድንገት ልትነከስ ትችላለህ። ድንገትም ጉዞህ በአደጋ ይከበባል። ያኔም አማራጭ ከፊት ይቀመጣል። ‹‹ውጣ አትበለው ግን እንዲወጣ አድርገው›› የሚለው ለዘመናት ያገለገለው ቀመርም በስራ ላይ ይውላል። እመነኝ ይህን ቀመር ከተቀበልክ ተሸውደሀል። ከወጣ ወጣህ ነውና። ማን ነበር ‹‹ሀገሩ የሌለ የትም የለ›› ያለው? ተስፋዬ ገ/አብ ይሆን? ለነገሩ ስዬ አብርሃም ‹‹መሬትህን አትልቀቅ›› ሲሉ የጻፉ ይመስለኛል።

በእርግጥ ፍትህ በአራት አመት ጉዞዋ በቂ ሊባል የሚችል ስራ ባትሰራም፣ ለሀገራችን የዴሞክራሲ ሂደት የአቅሟን ያህል አስተዋፆ ማድረጓ ሊካድ የሚችል አይደለም። ከተባዳዩ አንፃር ቁጥሩ እዚህ ግባ የሚባል ባይሆንም ለተበደሉ፣ እና ፍትህን ለተነፈጉ ድምፃቸው ሆናለች። ከዚህ በተጨማሪም በርካታ ህዝባዊ ችግሮችን፣ ሀገራዊ አጀንዳዎችን ግራና ቀኝ ፈትሻ አደባባይ አውላለች። ይህ ሲሆን መንገዱ አልጋ በአልጋ ሆኖ እንዳይመስልህ። ለነገሩ አንተ እዚችው ኢትዮጵያ ስላለህ ከአደጋ የፀዳ መንገድ ያለ ሊመስልህ እንደማይችል አውቃለሁ። እንዲያውም ይህ ሁኔታ የሚመሳሰለው ከኢህአዴግ ጉዞ ጋራ ነው።

አዎ! ህወሓትን እፍኝ የማይሞሉ ሰዎች እንደ መሰረቱት ታውቃለህ። ሞኛ ሞኙ ደርግም በቆረጡ ሰዎች (ሰባትም ሆኑ አስራ ሁለት) የታሪክ ሰሪ መንፈስ እንደሚሰፍንባቸው አላወቅምና እስከውድቀቱ ዋዜማ ድረስ ‹‹እፍኝ የማይሞሉ ወንበዴዎች…›› በሚል ፕሮፓጋንዳ ጉልበቱን ጨረሰ። (ይህ የእኔ ትንተና እንዳይመስልህ። ‹‹የትውልድ ሀላፊነትን የተቀበሉ ቆራጦች አዲስ ታሪክ ሰሪ መንፈስ ይጫናቸዋል›› የሚሉት ታሪክ አዋቂ ፈላስፎች ናቸውና።) እመነኝ የህወሓትም ብርታት ከዚህ እንጂ ከሱዳን ጠንቋይ የመጣ አይደለም። ማን ያውቃል የፍትህ ጉዞስ ነፃውን ፕሬስን የት እንደሚያደርሰው? እናም ያ ቀን ለቀጣዩ ትውልድ ሲል ያጥር ዘንድ እመኛለሁ። መመኘት ብቻም አይደለም እንዲህም እላለሁ አቤቱ ታሪክ ሰሪ መንፈስ ሆይ ወዴትነህ?


የሆነ ሆኖ ከመጋረጃው ጀርባ ባለችው ኢትዮጵያ እና በኢቲቪ በምትመለከታት ኢትዮጵያ ብዙ ርቀት አለ። የኢቲቪ ኢትዮጵያ በየአመቱ 11 በመቶ የምታድግ፣ ነፃ ፕሬስ እንደ አሸን የፈላባት፣ ብሔር ብሔረሰቦች በደስታ እና በተድላ ተፋቅረው ‹‹ያምቡሌ››ን የሚጨፍሩባት፣ ፍትህ ርትዕ የነገሰባት፣ እውነትን የሚያገለግል ጋዜጠኛ የሚከበርባት፣ የስራ እድል የተትረፈረፈባት… ወዘተተርፈ ነች። እንዳልኩህ ይች ኢትዮጵያ የኢቲቪ እንጂ እኔና አንተ የምናውቃት፣ ኢህአዴግ የሚያስተዳድራት አይደለችም።

እኔና አንተ የምናውቃት፣ ከነ-

ወደ ገፅ 6 ዞሯል

‹‹ስደት በጋዜጠኛው ዓይን››
የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ በገበያ ላይ

በአንጋፋው ጋዜጠኛ ነብዩ ኢያሱ የተዘጋጀው ‹‹ስደት በጋዜጠኛው ዓይን›› የተሰኘ መጽሐፍ ዋነኛ ዓላማ የስደትን እውነተኛ ገጽ ለማሳየት፣ የሰው ልጅ ሲገፋ፣ ሲበደል፣ ሲባረርና ሲወረወር ነሮ በመነሳት በደልን ለመቋቋምና ለፍትሕ ለመቆም የሚያደርገውን የህይወት ተጋድሎ ለማንፀባረቅ ነው። ከዚህ አኳያ ያጋጠሙን ችግሮችና ያደረግናቸው ስህተቶች በመመርመር ለዘለቄታው የህብረተሰባችን ጥንካሬ የአስተዋይ ዜጐች እርምጃ ምን መሆን እንዳለበት እንመካከራለን።
የመንግስትን መሰረነትና የህብረተሰባችንን ጥንካሬና ድክመት ለመመርመርና ለመወያየት ይህ መጽሐፍ እራሳችንን እንደ መስታወት የምናይበት፣ ትናንት፣ ዛሬንና ነገን የምንመለከትበት መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ ድክመቶቻችንን በማፍረጥረጥ እውነቱን ሲነግረን ያስደነግጠናል፣ አንዳንዶቻችንም ያስከፋናል፣ የወደፊቱን የተስፋ ጭላንጭልም ያሳያል።




ይህ የመሪዎቻችንና የያንዳንዳችን ለመተንበይ የሚያስቸግር ግራ የሚያጋባ ባህሪይ የምንመረምርበት ምርጥ መጽሐፍ ዛሬውኑ ያንብቡት!

በሁሉም መጽሐፍት መደብሮች ያገኙታል።
ዋና አከፋፋይ አምባሳደር መጽሐፍት መደብር
ስ.ቁ. 0911 67 64 57

# ፍልስፍና



# አገር ወዳድነት (ብሔራዊ ስሜት) እና አለማቀፋዊነት

### ውድ ዶ/ር አድለር

‹‹አገር ወዳድነት›› (ብሔራዊ ስሜት) የሚለውን ቃል በብዙ መንገድ ሲጠቀሙበት እያየሁ ግራ ተጋብቻለሁ፡፡ ሕዝቦች ከተባበሩት መንግስታት ወይም ከሌሎች አለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር ተባብሮ መስራትን በመንቀፍ እራሳቸውን ‹‹አገር ወዳዶች›› በማለት ይጠራሉ፡፡ ጉጠኞችም ከጭቆና ለመላቀቅ እና እራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እየታገሉ አሁንም ‹‹አገር ወዳድ›› ብላችሁ ጥሩን ይላሉ፡፡ በደቡብ አፍሪካ ውስጥ የነበረው የነጮች አገዛዝ፣ የጀርመን ናዚዎችና አክራሪዎችም እንዲሁ እራሳቸውን፣ የሚቆጥሩት ‹‹እንደ አገር ወዳድ›› ነው፡፡ ለመሆኑ ‹‹አገር ወዳድ›› ማለት ምን ማለት ነው? የትኛውንም አለምአቀፋዊ ትብብር መቃረን አገር ወዳድ ያሰኛል?

ኤፍ.አር

### ውድ ኤፍ.አር

ለዚህ ዘመን ጆሮ እንደ ‹‹አገር ወዳድነት›› ያለ ተደጋግሞ የሚሰማ ሌላ ቃል አለማለት ይቸግራል፡፡ አንድ ሰው አፍሪካና እሲያ ውስጥ ስለተነሳ ‹‹የአገር ወዳድነት›› ማዕበል እንዲሁም የአብዮትና የአብዮት ቅልበሳ መንስኤ ሆኖ በአንድ ጊዜ ሊሰማ ይችላል፡፡ የቻይና አገር ወዳዶች ንቅናቄ፣ የእንግሊዝ አገር ወዳዶች ንቅናቄ፣የአረብ አገሮች የአገር ወዳዶች ንቅናቄ፣ የሰርቢያ አገር ወዳዶች ንቅናቄ፣ የፈረንሳይ አገር ወዳዶች ንቅናቄ... ወዘተ፡፡ የዚህን ወሳኝ ቃል ግልፅ አለመሆን አንስተህ ሐሳብ እንደገባህ መግለፅህ ትክክለኛ ነገር ይመስለኛል፡፡ ግልፅ መሆን የሚችልበትን ፍቺ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡ በግል ሆነ በጋራ ላለን ህይወትም የአገር ወዳድነት ግንዛቤ ግልፅ መሆን ወሳኝ እና ዋነኛ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ብሔራዊ ስሜት የሚለውን ግንዛቤ ፈፅሞ አዲስ አስተሳሰብ እንደሆነ አድርጐ መቀበል በራሱ ግራ መጋባቱ ላይ እኩሌታ ድርሻ አለው፡፡ ይሁንና ግንዛቤው ሳይሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እንደ ፋሽን የተያዘው ወታደራዊ የፖለቲካ አማራጭ የተለያየ ሆኖ ሳለ በአንድ ቃል መገልገሉ ሁኔታ ነው የተምታታ ግንዛቤ የፈጠረው፡፡ የብሔራዊ ስሜት ወይም የአገር ወዳድነት ከማህበረሰብ ምስረታ እኩል እድሜ ያለው ጥንታዊ ግንዛቤ ነው? ብሔራዊ ስሜት የሚለው ቃል ካለው ልዩ ነገር ይልቅ የዘመኑ የአገር ወዳድነት ትግል ከጥንታዊው ፖለቲካዊ ውትድርና ጋር ያለው ተመሳስሎ የበለጠ አስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የሰው ልጅ ፖለቲካዊ ተፈጥሮ በተለያዩ መንገዶች እራሱን ሲገልፅ እንደኖረ ከታሪክ እንማራለን፡፡ ቤተሰብ፣ ጐሣ ወይም ነገድ፣ ጉልታዊ ፊውዳል፣ ኃይማኖታዊ ወገንተኝነት፣ የከተማ አስተዳደር፣ ሥርዎ መንግስት፣ ግዛት እና ብሔራዊ አስተዳደር፡፡ ታሪካዊ ሁነቶች የሰው ልጅ ፖለቲካዊ ፍላጐቱን በተለያየ መንገድ እንዲያስፈፅም ሲገፋፉት ኖረዋል፡፡ ይሁንና እነዚያ መሰረታዊ የሰው ልጅ ፍላጐቶች አልተለወጡም፡፡ ብሔራዊ ስሜት እንደሌሎቹ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ሁሉ ሰዎች የሚፈልጉትን ለማግኘት የሚሞክሩበት መንገድ ነው፡፡

በአጠቃላይ ብሔራዊ ስሜት ህገ መንግስት ያለው ወይም አለኝ ብሎ የሚያስብ የትኛውም የፖለቲካ ቡድን የሚያዋህድ ስሜት ነው፡ ፡ ከዚህ በተጨማሪም የትኞቹም በብሔራዊ ፍቅር ልባቸው የነደደ ሰዎች ከየትኛውም ነገር በፊት ቅድሚያ የሚሰጡትና የሚታመኑት ለአገራቸው ብቻ ይሆናል፡፡

በወቅታዊው ብሔራዊ ስሜት ላይ ተዘውትሮ ባይሆንም አልፎ አልፎ የሚስተዋል ባህሪም አለ፡፡ አንዲት አገር ሰፊ ልትሆን ትችላለች፡፡ ስለዚህ የተማከለ ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ አስተዳደር ይኖራታል፡፡ ህዝቦቿም የሚጋሩት ታሪካዊና ባህላዊ እሴት ይኖራቸዋል፡፡ ይሁንና አነሰም በዛም በጥሩም ሆነ በመጥፎ መልኩ የዘር መድልኦ እንዳለ የሚሰማቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት የባህላዊ አንድነት ስሜቱ በቀላል መንገድ በዘረኝነት የሚተካበት ሁኔታ አለ፡፡

ዘመናዊው ብሔራዊ ስሜት ብዙ ጊዜ ለፖለቲካ የተመቸ አስተሳሰብ ተደርጐ ይታያል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ምንጩ ከፈረንሳይ አብዮት ጋር ተያይዞ የነፃነት፣ የእኩልነትና የወንድማማችነት አስተሳሰቦች መነሻ ሆኖ ይቀርባል፡፡ ነገስታትን ሳይሆን ህዝቦችን ለዙፋን አብቅቷል ማለት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የአገሮቹን ማዕከላዊ ሥፍራና ሉአላዊነት ከአምባገነኖቹ ይልቅ ለህዝቦች አጕናፅፏል፡፡

ብዙ ጊዜ የብሔራዊ ስሜት እንቅስቃሴዎች ወደ ዴሞክራሲ ሲለወጡ ይታያል፡፡ ይሁንና ይሄ የሚሆነው ሁልጊዜም አይደለም፡፡ የአገራዊ ስሜት ያላቸው ቡድኖች ያንን ለአገር ያላቸውን ፍቅር እንደያዙ ሳይለቁ ሌላ አይነት አገዛዝ ሊመሰርቱ ይችላሉ፡፡ በአገራዊ ስሜት ውስጥ ዋናው ነገር በህዝብ የተወደደው አመለካከት አስተዳደር ላይ መቀመጡ እንጂ ያ በህዝብ የተወደደ አመለካከት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ መተግበሩ አይደለም፡፡

ብሔራዊ ስሜትን ከተለየ አቅጣጫ ተመልክተው የሚያሳስባቸው ሰዎችም አሉ፡፡ የእነዚህ ሰዎች ስጋት የሚመነጨው ብሔርተኝነት ከአለም አንድነትና አስተዳደር በተቃራኒ ስለሚቆም ነው፡፡ የአገር ወዳዶች ስሜት መሰረቱን የሚጥለው በአካባቢ ጉዳዮች ላይ በመሆኑ አለም አንድነቷ ሊጠናከር ቀርቶ ከአሁኑ የበለጠ ልትበጣጠቅ የምትችልበት ሁኔታ እንደሚኖር እነዚህ ሰዎች ስጋታቸውን ይገልፃሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች የችግሩን መኖር በተመለከተ አንገታቸውን ለመስጠት ወደኋላ አይሉም፡፡ ይሁንና እኔ ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል የሚል እምነት የለኝም፡፡ አንድ አገር የተቀሩት አገራት ሁሉ ጠላት ይሆናል፣ ማለት አይደለም፡፡ አንድ አገር ፍላጐት የሚሳካው ከጠላትነት ይልቅ በመተባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ሲኖረው ነው፡፡ መተባበር ደግሞ ወደ ህብረት ሊመራ የሚችል ነገር ነው፡፡ ህብረት ደግሞ በአገራዊ ስሜት ከመቃረን ፍፁም የራቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡

# የፍትህ መንገድ

... ከገፅ 5 የዞረ

ዛሬ... እያልን የምንሰጋባት፣ ዜጐቿ ‹‹ውጡ ይህ ሀገራችሁ አይደለም›› የሚባሉባት፣ ጋዜጠኞች አሸባሪ እየተባሉ እንደ በግ ተጎትተው የሚታሰሩባት ወይም ሀገር ለቀው የሚሰደዱባት፣ ህፃናት በረሃብ እንደቅጠል የሚረግፉበት፣ ስራ እጥ የነገሰበት፣ የፍትህ ስርዓቱ ለመንግስት ጠባቂ መልዕክ የሆነበት፣ ካድሬ ያሸውን የሚያደርግባት፣ የመደራጀትና የመሰለፍ መብት የተነፈገባት፣ ሰብዓዊ መብት የሚጣስባት፣ አቤት! የሚባልበት ዳኛ የሌለባት፣... ኢትዮጵያን ነው የምናውቃት፡፡

የፍትህ ጉዞንም በእሾህ የተከበበ ያደረገው ይህ ነው፡፡ ለዚህም ነው ደግመን ደጋግመን ‹‹ጉዞአችን ቀራኒዮ›› ድረስ ነው ያልነው፡፡ በእርግጥ ላለመሰናከል መበርታት እንደአለብን ብናውቅም ቀራኒዮ ከዚህ ምን ያህል እንደሚርቅ ግን ማናችንም አናውቅም፤ ዛሬ ምሽት እንድረስ ወይም ነገ አሊያም የሚቀጥለው አመት የሚያውቀው ገዢው ፓርቲ ብቻ ነው፡፡ ምንም አይነት እርምጃ የመውሰድ ምርጫው በገዥው ፓርቲ እጅ ነው፡፡ አዎን! ውሳኔው በእጁ ነው፡፡ ወይ ፍትህን አጥፍቶ የሚመጣውን በፀጋ መቀበል፤ አሊያም የፍትህን ጎምዛዛ ሂስ ውጦ መታረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ፍትህን መዝጋት አሊያም እንድትዘጋ በስውር መዳፍ መደፍጠጥ በኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ላይ የመጨረሻውን ሚስማር መምታት ነው፡፡ ሚስማር ደግሞ የሚፈነቅለው ነገር ሊኖር እንደሚችል ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡ እስከዛው ድረስ ግን እኛ እንፅፋለን፡፡ የምንፅፈው የሀገሪቱ ህገ-መንግስት መፃፍ ትችላላችሁ ሲል መብታችንን ስላረጋገጠልን ነው፡፡ እምንከተለውም ሆነ እምንቀበለው ህገ-መንግስቱን ብቻ እንጂ የአምባገነን ባለስልጣናትን ተግሳፅ አይደለም፡፡ አንተም ይህን ልታደርግ ይገባሃል፡፡ ሀሳብህን ያለገደብ መግለፅ ትችላለህ ተብለሀልና ይህንኑ መተግበር አለብህ፡፡ ያን ጊዜም ነው ነፃነትህ በእጅህ የምትሆነው፡፡ ያንጊዜም ነው ሀገር እና ህዝብን የምታገለግለው፡፡

አዎን ፍትህም የምታገለግለው ሀገርንና ህዝብን እንጂ መንግስትን ወይም ተቀናቃኞቹን ባለመሆኑ እስከ መጨረሻዋ ሰዓት ከመስመራችን አንድ ኢንች አንወጣም፡፡ ትላንት ጎዞአችን ቀራኒዮ ድረስ ነው ብዬሀለሁ፡፡ ዛሬም እደግመዋለው ‹‹ቀራኒዮ...ድረስ ነው››

የሆነ ሆኖ በዚህ ፅሁፍ ላይ ከከፍተኛ ባለስልጣኖች ጀምሮ እስከ ተራው ካድሬ ድረስ በሚቆጠሩ አምባገነኖች የተሰነዘሩ ዛቻ እና ማስፈራሪያዎችን፣ እንዲሁም ለቁጥር አዳጋች የሆኑ የሀሰት ክሶችን ብዘረዝር ቢያንስ ለታሪክ ይጠቅም ነበር፡፡ ሆኖም እንኳን አንድ አምድ፣ ሙሉ ጋዜጣውም አይበቃምና እናልፈዋለን፡፡ ነገር ግን እዚህች ጋ ስደርስ አንድ ነገር ትዝ ስላለኝ ላጫውትህ፡፡

በዚሁ ዓመት በወርሃ ታህሳስ ለአንድ ሳምንት ያህል በፍትህ አዘጋጆች ላይ የደህንነት አባላት ነን ያሉ ሰዎች 24 ሰዓት ሙሉ እየተከታተሉ ያስጨንቁ ነበር፡፡ ሁኔታውም ከቀን ወደ ቀን እየከረረ እና እየበረታ ሲሄድ ሁሉም አዘጋጆች አሲምባ ገቡ፡፡ አሲምባ ግን የት ነው? ትርጓሜውስ ምን ማለት ይሆን?

መቼም በያ ትውልድ ዘመን በነበሩ ወጣቶች ልብ ውስጥ ኢህአፓ የሚባል ፓርቲ ነግሶ እንደነበረ ታስታውሰዋለህ፡፡ ደህና! ኢህአፓም ሰራዊቱን ምዕራብ ትግራይ ውስጥ ኢሮብ የሚባል ቦታ በሚገኝ አንድ ተራራ ላይ እንዲሰፍሩ አደረገ፡፡ ያ ተራራም አሲምባ ይባላል፡፡ ትርጓሜውም ‹‹ቀዩ ተራራ›› ማለት ነው፡፡ እናም አሲምባ ለብዙ ወጣቶች ከሞት የማምለጫ ምሽግ ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ በእርግጥም እድል ቀንቶአቸው በርካታ የደርግ ኬላዎችን አልፈው አሲምባ መድረስ የቻሉ ወጣቶች ከሞት ተርፈዋል፡፡ አሲምባ ማለት በያ ትውልድ ይህ ነው፡፡

ወደ ፍትህ አሲምባ ደግሞ እንምጣ፡፡ ከላይ እንዳልኩህ በነዛ ሰባት የመከራ ቀናት፣ ክትትሉና ጫናው አደገኛ በመሆኑ ሁለቱ የጋዜጣው አዘጋጆች ‹‹በጋራ ለቆምንለት የፕሬስ ነፃነት፣ በጋራ ዋጋ እንከፍልለታለን›› አሉና በብቸኝነት እኖርበት የነበረችውን አንድ ክፍል ቤት ተዳበሉ፡፡ ከዚህ በኋላም ክትትሉና ማስፈራሪያው በጋራ ሆነ፤ የእኛም እንቅስቃሴ ተገደበ፣ እንደጋዜጠኛ ከወዲህ ወዲያ ተሯሩጦ መስራት የማይሞከር ሆነ፡፡ ውሎአችንም ከቤት ወደቢሮ፤ ከቢሮ ወደቤት ሆነ፡፡ ይህን ሁኔታ ቅርብ ሆነው የተከታተሉ ወዳጆቻችንም ያችን በጋራ የሙጢኝ ያልናትን የኔን ቤት ‹‹አሲምባ›› ሲሉ የበረሃ ስም ሰጧት፡፡ እነሆም በግልፅ የነበረው የደህንነት ከበባው ቢነሳም (ምንአልባት በስውር ሆኖ ሊሆን ይችላል) አሲምባ ግን ዛሬም የአዘጋጆቹ መኖሪያ ቤት መሆኗን ቀጥላለች፡፡

በእርግጥ አሲምባን መኖሪያ ቤት ከማለት ‹‹ምሽግ›› ማለቱ የሚቀል ይመስለኛል፡ ፡ ምክንያቱም በአሲምባ ህይወት ጉራማይሌ ነው፡፡ ከምቾት የተፋታ፣ ከደስታ የተጋባ ነውና፡፡ በምግብ በኩል በአሲምባ አብስሎ ለመብላት የሚያስችል ምንም አይነት ቁስ ስለሌለ ብዙውን ጊዜ ለእራት የሚሆነው ሙዝ በዳቦ ሲሆን፣ እንዳንዴም ጫናው ሲበረታ እንደተራቡ ማደር ይከተላል፡፡ (አሳዳጆቻችን ግን የሚያሳድዱን እራት በልተው ይሆን ወይም ሳይበሉ የሚያውቀው የመደባቸው አካል ብቻ ነው) ይህም ሆኖ በአሲምባ በጊዜ የሚተኛ የለም፡፡ ቶሎ ከተተኛ ከሌሊቱ ሰባት ሰዓት በኋላ ነው፡፡ አሊያም እስከ ንጋት 11 ሰዓት ይመሻል፡፡ ይህ ግን አሰልቺ አንዳይመስልህ፡፡ እንዲያውም በጣም ጣፋጭ ነው፡ ፡ እንዴትስ ጣፋጭ አይሆን? በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ዱላ ቀረሽ ክርክር እና ውይይት እየተደረገ የሚቆይ ምሽት? እናም በአሲምባ ሲነጋ መንጋቱን የምታውቀው ከጎዳናው ላይ በሚሰማው የታክሲ ረዳቶች ተሳፋሪዎቻቸውን በሚጣሩበት ድምፅ ነው፡፡ (ስለአሲምባ ሌላ ጊዜ በስፋት እናወጋለን፡ ፡ አሁን ኑሮአቸውን በአሲም ባደረጉ አዘጋጆች ስለምትዘጋጀው የ‹‹ፍትህ›› ገዳለ ገደል ጉዞን ቅኝት ወደመደምደሙ እንመለስ፡፡)

አዎ! እጃችሁን ከፍትህ አንሱ ፍትህን ማሸነፍም ሆነ መጨፍለቅ አይቻልምና፡፡ በነገራችን ላይ ፍትህ ስል አዘጋጆቹን እንዳይመስላችሁ፣ መንፈሱን ነው፡፡ የመናገር፣ የመተቸት፣ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ መንፈስን ማንም አይገድበውም፡፡ ማንም፡፡ የፍትህን መንፈስ (ይህን መንፈስ) ማሸነፍ ደርግን የማሸነፍ ያህል ቀላል አይደለም፡፡ ይህ ማስፈራሪያ አይደለም፡፡ ህዝብ አይሸነፍም ማለት እንጂ፡፡ መቼም ይሁን መቼ፣ የትም ይሁን የት ህዝብ ተሸንፎ አያውቅም፡፡ እናም ፍትህን አጥፍቶ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ ይኑር ማለት ትውልድን ከማጥፋት ወንጀል በምንም ሊለይ አይችልም፡፡ ሊያንስምም አይችልም፡፡ ስለዚህም በአገሪቱ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዳለን ሁሉ፣ የምንሰብከውም በህገ-መንግስቱ በተረጋገጠው መብታችን ብቻ እንደሆነ እና ይህንን መብትም ሌሎችም እንዲጠቀሙበት የማበረታት ሙሉ መብት እንዳለን አውቃችሁ ልታከብሩልን ይገባል፡፡

...የሆነ ሆኖ የፍትህ ቤተሰቦች እየከፈሉ ያለው ዋጋ ለሀገር መከፈል ካለበት አንፃር ከአየነው በጣም ጥቂቱን ነው፡፡ ምክንያቱም ለዚህች ሀገር በርካቶች የህይወት መስዋዕትነትን ከፍለው አልፈዋልና፡፡ በጎዳና ላይ በጥይት ያለቁት ወንድም እና እህቶቻችን ዛሬ እኛ እያቀነቀንን ላለው የዴሞክራሲ ስርዓት ነው፡፡ ከታሪካችን እንደተረዳነውም ካልን እልፍ አላፍት መስዋዕቶች ‹‹ሀገሬን...›› ሲሉ አልፈዋል፡፡ ለዳር ድንበር መተኪያ የሌለውን ህይወታቸውን ከፍለዋል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል አሉላ አባነጋን የመሳሰሉ የሀገር አንድነት አቀንቃኝ ጠላቶቻችን ተሸንፈው ከሀገራችን ሲወጡ ‹‹የረገጣችሁት አፈር ላይ የወንድሞቻችን ደም ፈሶአልና ከጫማችሁ አራግፉ›› ሲሉ ያስገደዱት፡፡

ወዳጄ! ይህን እየፃፍኩልህ ሳለ ፍትህን የከበባት አደጋ ከመቼውም ጊዜ የከፋ ሆኗል፡፡ ከዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከል እስከ አይጋ ፎረሙና አዲስ ዘመን የተሰኙ ‹‹ሎሌ›› ሚዲያዎች ከእነ ጭፍሮቻቸው የማሸማቀቅ፣ የመወንጀል፣ የማስፈራራት፣ የማስጨነቅ ዘመቻቸውን በተለያየ ግንባር ከፍተውብናል፡፡ እነዚህ ሚዲዎች ዛሬ እየፈጠሩ የሚለጥፉብንን የሀሰት ውንጀላዎች ነገ ደግሞ ማስረጃ አጠናከርንበት ሊሉ እንደሚችሉ ማንም ያውቃል፡፡ በፍትህ በኩል ግን ዛሬም እንደቀድሞ ለስደት የተዘጋጀ እግር እና አጎብዳጅ አንገት እንደሌለ ከሳሾቻችን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡


## ስብሐት ገ/እግዚአብሔር ሕይወትና ክህሎት

### መጽሐፍ ድጋሚ ታትሞ ገበያ ላይ ዋለ !

<<ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ... የስብሐትን ማንነት (በሰብዓዊነቱ፣ በተፈጥሮው፣ በአመለካከቱ፣ በአስተሳሰቡ) በመውደድና በማክበር ረገድ ጥሩ ትሕትና የተላበሰ መጽሐፍ ነው፡፡ እውነት ለመናገር እንደ ቀድሞ ሥነ-ጽሑፍ መምህርነቴ በአፌ ሙሉ ላድንቅ ብል ዓለማየሁ ገላጋይን ጥሩ አማርኛ አዋቂና ከቃላት አመራረጡ ጀምሮ እስከ ንድፈ ሀሳብ አደራደሩ... የመሰጠኝ መሆኑን መግለፅ እፈልጋለሁ፡፡ . .በምርመራውና አዲስ የአመለካከት ፈር በመቅደዱ ዓለማየሁን አሁንም የደራሲነት ጥረትና ቋንቋውን አደንቅለታለሁ፡፡>>

መስፍን ኃ/ማርያም

<<ድንቅ ስራ ነው፡፡ ይህ የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ የሥነ-ጽሑፍና ሃያሲያንን ትኩረት እንደሚስብ አያጠራጥርም፡፡ ጋዜጠኛ ዓለማየሁ ለብዙ መሰረታዊ ሂደቶች የሚሆን ጥናት አቅርቧል ማለት እችላለሁ፡፡>>

እዮብ ካሣ




<<በዚህ በዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ ላይ....መጠነ ሰፊ ውይይትና ክርክር የተደረገበት አጋጣሚ ተከስቷል፡፡ ዓለማየሁ ገላጋይ በዚህ መጽሐፍ... ያልተደፈሩ ርዕሶችን በማንሳት ችሎታው ያለውን የተለየ ነገር ከመግለፁም በላይ... ስለስብሐት ህይወትም ሆነ ስለሥራዎቹ በርካታ አዳዲስ ነገሮች ነግሮናል፡፡ በሚያምር የቋንቋ አገላለፅ ስለስብሐት የተለየ ህይወትና ክህሎት ከማናውቀው አቅጣጫ ተነስቶ በተጋፋጭነት አቋም ይተርካል፡፡ ተወደደም ተጠላም ለደረሰባቸው አዳዲስ ድምዳሜዎች ምክንያቱን አቅርቧል፡፡ በዚህ መጽሐፍ የተነሱትን ጉዳዮች ወደ ጐን በመግፋት የምናደንቃቸው ታላላቅ ሰዎች ሲነኩ ብቻ <<ዘራፍ!>> ማለት ከታሪክ ተጠያቂነት አያስተርፍም፡፡>>

ሰለሞን ጉቹ

ይህን በታዋቂ ሰዎች ዘንድ እንዲህ ምስክርነት የተሰጠለት አነጋጋሪና ድንቅ መጽሐፍ በአነስተኛ ቅጂዎች የታተመ ስለሆነ ሳያመልጥዎ ዛሬውኑ ፈጥነው የግልዎ ያድርጉት በሁሉም መጽሐፍት መደብሮች ያገኙታል፡፡

ዋና አከፋፋይ አምባሳደር መጽሐፍት መደብር ስ.ቁ. 0911 67 64 57

# የእናቴን ዘመዶች ተዉአቸው!



አናንያ ሶሪ
anania20006@yahoo.com

ሰው ነኝ፤ በአምላኬ አምሳል የተሰራሁ:: ለዚህም ፈጣሪ ምስጋና ይግባው! በዚሁ በምፅፍበት የአማርኛ ቋንቋ ስቀጥል፡- በእናቴ አማራ ነኝ:: ቋንቋውን አቀላጥፌ ባልችልም በአባቴ ደግሞ ኦሮሞ ነኝ:: ሁለቱ ግን ያለአንዳች ችግር በአባቴ ኦሮምኛም ሆነ በእናቴ አማርኛ ይግባባሉ:: ደግሞም የእናቴ አማርኛ ብዙ የአባቴ ኦሮምኛ ቃላትን በውስጡ ይዟል:: ለመማርም ዝግጁ ነበሩና ቋንቋ ለህብረታቸው ደንቃራ አልሆነም:: ቀድሞውኑም ለመቀራረቡ ደግሞ ንግድና ግብይት ጥሩ አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል:: እኔም የጊዜ ጉዳይ እንጂ ገና ብዙ የሀገሬን ቋንቋዎች እለምዳለሁ:: የነሱን አባትና እናት ብሎም አያት ቅድመ-አያቶች 'እርግጠኛ' ቋንቋዊ ማንነት ብሎም የዘር ግንድ አሊያም ሐረግ ለማወቅ ደግሞ ሉሲ እና አርዲ ይጠየቁበት:: ታዲያ ከዚህ ሁሉ በኋላ እኔ ማነኝ? ሰው ኢትዮጵያዊ ከመሆን በቀር! አዎ-ከሰውነቱ ባሻገር ኢትዮጵያዊ፤ ቀጥሎ የአማራ እና ኦሮሞ ወይም የኦሮሞ እና አማራ ውህድ የሆንኩ አዲስ ፍጥረት ነኝ:: በዚያ ላይ አዲስ አበቤ:: አሊያም ኢጆሌ ፊንፊኔ! ከፈለጋችሁ በአራዶቹ ቋንቋ አምቼ በሉኝ:: ይህ የእኔ የማንነት አረዳድ ቅደም-ተከተል ነው ፤ ቢያንስ አሁን ባለው የማንነት ፖለቲካ ማዕቀፍ ውስጥ ራሴን ሳየው! በተረፈ በሙያዬ፣ በምርጫዬ፣ በፍልስፍናዬ፣ በፖለቲካ አቋሜ፣ በኢኮኖሚ ደረጃዬ፣ በፆታዬ፣ በዕድሜዬ፣ በሃይማኖቴ፣ በቋንቋዎቼ፣ በባህሎቼ ስገለፅ የራሴ የሆኑ ተፈጥሯዊ፣ አመለካከታዊ፣ ሙያዊ እና ማህበራዊ የማንነት ገፅታዎች ያሉኝ ሰው ነኝ:: እንደከተማ ነዋሪነቴም ብዙ የሚያዋትቱኝ የሙያና የኢኮኖሚ ማንነቶቼ ናቸው:: ለሌሎቹ ግድ የለኝም ግን አላልኩም:: እንደየሁኔታው መቀያየር እየገዘፉና እያነሱ የሚሄዱ የተለያዩ ማንነቶች ባለቤት ነኝ:: ብዙዎቹም ሰዎች እንዲሁ ይመስሉኛል:: ለምሳሌ፡- በእምነት ቤቴ ክርስቲያንነቴ እንጂ የጋዜጣ ላይ ፀሐፊነቴ ጐልቶ አይወጣም፤ አያስፈልግምም:: በሙያዬ ላይ ደግሞ የእምነቴ ማንነት ወሳኝ አይደለም:: ገጠር ያሉ ዘመዶቼን ልጠይቅ ሄጄም ከተሜነቴ እንጂ ሃይማኖቴ እምብዛም ገዝፎ አይወጣም:: በአንፃሩ ግን የተለያዩ ማንነቶቼ ሁሉ በቀላሉ የሚፈራረቁና በየተራ ብቻ የሚስተናገዱም አይደሉ:: አንዳንድ ጊዜ ገዝፈው ለመውጣት እርስ-በርስም በአያሌው ይታገላሉ:: ሰው ሀሳብ የሚፈራረቅበት የትግል አውድማ አይደል! በመሆኑም እንበልና፡- ለኢኮኖሚ ደረጃዬ መሻሻል ስል ፖለቲካዊ አቋሜን እንድለውጥ የሚያስገድድ ተፈታታኝ ሁኔታ ቢፈጠር፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ማንነቴ ግብግብ ውስጥ ገቡ ማለት ነው:: በመሆኑም አሸናፊ ሆኖ የሚወጣውን ለመወሰን የፍልስፍና ወይም የሃይማኖት የሞራል ማንነቴ ደግሞ የዳኝነት ሚናውን ይወስዳል::

ዛሬ ግን የእናቴን ዘመዶች ተዉአቸው እንድል ያደረገኝ፤ የአጠቃላይ ማንነቴ አካል እና ገሚስ-ክፋይ የቋንቋ ዘመድ የሆኑት የጉራ-ፈርዳ ነዋሪ የነበሩ አማሮች በኢ-ሰብዓዊ እና ኢ-ፍትሃዊ መንገድ ከቀዬአቸው መፈናቀል ነው:: እነዚህ ሰው-ኢትዮጵያዊያን የእናቴ ዘመዶች ኑሮን ከብልሃቱ ሊያሳኩ በተፍጨረጨሩበት፣ ጥረው-ግረውም በወዛቸው ሀብት ባፈሩበት፣ ልጆች ወልደው ሊከብዱም በተመኙበት የኢትዮጵያውያን ወንድም እህቶቻቸው መሬት እንደባዕዳን የውጪ አገር ዜጋ ተቆጥረው በግፍ መባረራቸውን ብሎም በቀማኛ-ካድሬ ተደብድበውና ተዋርደው ንብረታቸውን ተዘርፈው ወደመሃል አገር አዲስ አበባ ተሰደዱ ማለትን በሰማሁ ጊዜ ልቤ ተሰበረ፤ ደሜ ተቆጣ፤ ግማሽ ጐኔም ታመመ:: እህ…ብዬ ወደ ፈጣሪም አለቀስኩ:: በእውነት በዚች አገር ምን እየተደረገ ነው?

<u>ጉራፈርዳ 'ይሄ ሰው ከአማራ ከቶ ሚለው ማነው?'</u>

ያን ምስኪን ገበሬ ሸመቁበት አሉ
ካገር ሊያሳድዱት ከገዳም ከደብሩ
እትብቱ ካለበት
መሸመቁ ሳያንስ
የወይኑን አፀድ እየነቃቀሉ
ስለወይን ፈንታ ቀጋ እየተከሉ
ካባቶቹ እርስት አሳደዱት አሉ፤
መሰደዱ ሳያንስ
ከእትብቱ ተነቅሎ ከቤቱ ከቀዬው
የምስኪኑን በደል ጩኸቱን ቀምተው
'የገበሬው ስደት ከየት እስከየት ነው?'
የሚል መጽሐፍ ፅፈው
ይሸጣሉ አሉ! ገበያ አውጥተው::
(የተቀማ ጩኸት -ኤፍሬም ስዩም)

በኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ቤንች ማጂ በሚባለው ዞን ውስጥ በጉራፈርዳ ወረዳ በእርሻ ሙያ ሲኖሩ የነበሩ ሰው ኢትዮጵያውያን አማሮች በግዳጅ እየተፈናቀሉ ሀብት ንብረት ካፈሩበት አገራቸው ተነቅለው ተሰደዋል:: ለዚህ ደግሞ የተሰጠ ግልፅ ምክንያት የለም:: ‹‹ወደመጡበት ክልል ይመለሱ›› ከሚለው በስተቀረ:: የተከለለላቸው ክልል ደግሞ የነዚህን ሰዎች ህልውና ለማቆየት ባለመቻሉ ነው ቀድሞውኑም የተከለለውን ክልል አልፈው መሄዳቸው:: እህል-ውሃቸው መርቷቸው ቤንቺ ማጂ የተገኙትም ሰርተው ጥረው ግረው ሀብት ማፍራት፣ ቤት ማቆም፣ ቤተሰብ መመስረት ሲጀምሩ ምንም ባላወቁት ሰበብ ከየቤቶቻቸው ተጐትተው ሽገር አውራ-ጐዳና ላይ ተጣሉ:: ለካንስ ያለተከለለልህ ክልል ውስጥ መኖር ክልክል ነው:: በተለይ ለማኝ ካልሆንክ፣ በተለይ ሀብት ማፍራት ከጀመርክ:: ሰው ዛፍ ይመስል ከተወለደበት መሬት በቅሎ፣ አድጐ፣ አርጅቶ እዛው እንዲሞት ካልሆነ በቀር እንዲህ ያለው አካሄድ ለኔ እንደሚታየኝ ፀረ-ህይወት እና ፀረ-ስልጣኔ ነው::

የሰው ከቦታ ቦታ መዘዋወር ተፈጥሯዊ እና የነበረ ያለ የሚኖርም ነው:: ይህ ደግሞ አዳዲስ ሁነቶችን እየወለደ ዓለምንም እኛን ኢትዮጵያውያንንም እዚህ አድርሶናል:: በዘመናት የሰው ልጆች የመቀራረብ ሂደትም አገራት ተፈጥረዋል:: ኢትዮጵያችንም አንዷ ናት:: ኢትዮጵያውያንም በዚህ መልክ የተፈጠረች ኢትዮጵያ ውጤት ነን:: ህብረ-ብሔርነታችን እንዳለ ሆኖ:: ምንም አልን ምን፣ የቱንም አስቀደምን የቱን አስከተልን ሰው መሆናችን ግን ቀዳሚ የተፈጥሮ ሀቅ ነው::

ከሰውነት ቀጥሎ ደግሞ ዓለምም የሚገልፀን እኛም ራሳችንን የምናውቀው በኢትዮጵያዊነት ነው:: የረዥሮም ዘመን የህይወት መስተጋብር፡- በጋብቻም ሆነ በአምቻ፣ በፍቅርም ሆነ በጡንቻ፣ በጦርነትም ሆነ በሰላም፣ በወረራም ሆነ በስምምነት፣ በውድም ሆነ በግድ፣ በገበያም ሆነ በጀብድ፣ በጌትነትም ሆነ በሎሌነት፣ በነፃነትም ሆነ በባርነት፣ በበታችነትም ሆነ በበላይነት፣ በአድሎም ሆነ በእኩልነት፣ በታናሽነትም ሆነ በበኩርነት፣ በጭሰኝነትም ሆነ በፊውዳልነት፣ በሙስሊምነትም ሆነ በክርስቲያንነት በኢትዮጵያዊነት ስር እንድንኖር አድርጐናል:: ኢትዮጵያዊነት መለኮት፤ ኢትዮጵያውያንም የመላእክት ስብስብ አልነበሩምና የፈጠሯት ኢትዮጵያም ኤደን ገነት/ጀነት አልሆኑም:: ሰው እንጂ ሌላ ስላልነበሩም በብዙ ተሳስተዋል:: በብዙም ደግ ሰርተዋል:: እንኳን በምድር በገነትም ሰዎች ስተዋል::

ታዲያ የነዚህ ሰው ኢትዮጵያውያን ልጆች የሆኑ የዛሬ-ዘመን አንጋፋ ትውልዶች የትናንቱን የአባቶቻቸውን እና እናቶቻቸውን ልማትና ጥፋት በሃቀኛ ሚዛን ሳይመዝኑ፤ ከዛ ሁሉ የታሪክ ክምር ነዶ አንዷት ነጠላ ሰበዝ ብቻ መዘው አገሪቷን እያመሷት ይገኛሉ:: አመፃና ክርክር እንጀራቸው ሆኗል:: አንዳንዶቹ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ መልካምና አጉል አስተሳሰብን ባንድ ላይ የሙጢኝ ብለው የጅምላ ወገኛ ሆነዋል:: ሌሎቹ ያለፈውን ታሪክ ሂሳብ በጥንቃቄ ሳያሰሉ ለማወራረድ የሚሹ አክራሪ አብዮተኞች ናቸው:: በዚህ መሃል ደግሞ አገሬና ወገኖቼ እኔም ጭምር በብዙ ተጐዳን:: የሁላችንም ሰብሳቢ እናት-ዓለም ኢትዮጵያ በፉክክር ደጇ ሳይዘጋ ማደር ከጀመረ እነሆ 40 ዓመት ሊሞላው 3 ዓመት ብቻ ቀረው::

ከ1967ቱ አብዮት የጀመረው ኢትዮጵያን እንደ አዲስ የማዋቀር ሙከራ በዋናነት በተተኩት ሁለት አምባገነን አገዛዞች የተነሳ እንዳይሳካ ሆኗል:: በመጀመሪያው የደርግ ወታደራዊ አምባገነን የኢትዮጵያ ዋና ችግር ተደርጐ የተወሰደው የመደብ ቅራኔ በሁለተኛው አምባገነን አገዛዝ ኢህአዴግ ወደ ብሔር ቅራኔ ተሸጋግሯል:: ከአንዱ 'ቅራኔ' ወደ ሌላው በግብታዊነት እና በጥራዝ-ነጠቅነት እየተሻገርን እዚህ ደርሰናል:: የቀደመውን አምባገነናዊ-ጥፋት በተከታዩ አምባገነን 'እርማት' እየተካን ጨቋኞች ስናቀያይር ይኸው ቅርፁን የቀየረ ጭቆና ታቅፈን አለን:: 'ኢትዮጵያ የብሔር-ብሔረሰቦች እስር ቤት ናት!' ሲሉ የዘውዳዊውን ስርዓት የተቹ ትውልዶች እና ተከታዮቻቸው ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ወደ ብሔር-ብሔረሰብ ድርጅቶች ታሳሪነት ቀይረውናል:: የማውቀውን ቋንቋ የማይናገሩ አምባገነኖች የማውቀውን ቋንቋ በሚያቀላጥፉ ፈላጭ-ቆራጮች ተተኩ:: 'ነፃ-አውጪዎቻችንም' በደምና በአጥንት ዋጋ የከፈሉበትን 'ነፃነት' በነፃ ሊሰጡን አዳገታቸው::

ከኢኮኖሚያዊ ደረጃችን ሲመዘዝ የነበረው 'ቅራኔም' ከቋንቋዊ ማንነታችን ተስቦ የልዩነት አጥር ተበጀልን:: ይህን ተከትሎም ልዩነት-ተኮር የብሔር ፌደራሊዝም በህወሓት ቀማሪነት ተጠንስሶ በነኦህዴድ እና ብአዴን ጋሻ-ጃግሬነት ወደመሬት ወረደ:: እነሆም ክልል ተከለለ፤ ከዜግነት በላይም ዘር የኢትዮጵያውያን መስፈሪያ ሆነ:: 'ይሄ ሰው ከየት ነው?' መባልም ቀዳሚው ጥያቄ ሆነ::

ይሁን እንጂ ይሄን መጤ ፖለቲካዊ አወቃቀር የቀደመ የህዝቦች አሰፋፈር እና ሰላማዊ ማህበራዊ ግንኙነት በኢትዮጵያ ውስጥ ስር የሰደደ ነው:: ድሮውኑም ቢሆን በኋላቀሩ አፄያዊ ስርዓት ሎሌዎች ውስጥ እንጂ በምልዓተ-ህዝቡ ውስጥ የሌለው የልዩነት አባዜ ኢትዮጵያዊነትን ሊሸረሽር አይችልም:: በመሆኑም ይህ ህዝባዊ-መሰረት የሌለው በቋንቋዊ ማንነት ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ የመቧደን ፖለቲካ ከላይ ወደታች በህዝቡ ላይ ሊጫን የሚፈለግ እንጂ ነባራዊና ህዝባዊ ፈቃደኝነት ኖሮት የሚቀነቀን አይደለም:: ለዚህ ደግሞ ተጨባጩ የለት-ተለት ህይወታችን ህያው ምስክር ነው::

በጉራፈርዳም የሆነው ከዚሁ ያልተለየ ነው:: በቤንች ማጂ ዞን ውስጥ ከሚኒጥ እና ሌሎች ልዩ ልዩ ብሔሮች ጋር በአብሮነት እየኖሩ የነበሩት የአማራ ተወላጆች እስካሁን ድረስ ወረዳው ሳይጠባቸው እና በጠላትነት ሳይተያዩ ከርመዋል:: እንደውም አንዳቸው የሌላኛውን መልካም ባህል እና ተሞክሮ እየቀሰሙ፣ በቋንቋዎቻቸው እየተግባቡ፣ በማህበራዊ ህይወት ግንኙነት እየተዋሃዱ ኖረዋል:: ይሄን ደግሞ ያስባለኝ ከወረዳው ለተፈናቀሉ አማርኛ ተናጋሪ ወንድሞቻቸው እና እህቶቻቸው ያደረጉት የፍቅር እና የርህራሄ ተግባር ነው:: እስከ 5 እና 7 ኪሎ ሜትር ድረስ አብረዋቸው በመጓዝ ብሎም ያላቸውን ያህል ገንዘብ ለመጓጓዣ እንዲሆን በማለት እስከመስጠት የደረሰ ሰብዓዊና ዜግነታዊ ሰናይ ተግባር ከውነዋል:: የሆነ ሆኖ ሁሌም ከሰብል መሃል አረም፣ ከስንዴ መሀል እንክርዳድ አይጠፋምና በዘር-ፖለቲካ አዕምሮዋቸው የናወዘ ህሊና-ቢስ ካድሬዎች ለስግብግብ የግል ጥቅማቸው ሲሉ ይህን የአብሮነትና የፍቅር ገመድ ለመበጠስ እንደ እብድ ውሻ ተክለፍልፈዋል:: 'ውሾቹን ተዉ በኋቸው' አይደል ተረቱስ:: ይህን ተረት በዳንኤል ክብረት ከተፃፉ መጣጥፎች በአንዱ ሳየው ትኩረቴን ሳበውና ሙሉውን አነበብኩት:: ታሪኩ እንደማስታውሰው ባጭሩ እንዲህ ነው፡- በአንድ ሰፈር ውስጥ የነበሩ የጐረቤታም ውሾች ይጣላሉ:: በዚህ ወቅት አንድ በመንደሩ የተከበሩ አዛውንት 'ውሾቹን ተዉ በኋቸው፤ ኋላ ነገሩ ጥሩ አይሆንም!' በማለት ያሳስባሉ:: ውሾቹ እርስ በርስ እየተጣሉ ሲናከሱም የአንዱ ቤት ታዳጊ ህፃን የነሱ ውሻ በመነከሱ ይናደድና ያንን የጐረቤት ውሻ በዱላ ይመታዋል:: በዚህ የተናደደው እኩያው የጐረቤት ልጅ መቺውን ህፃን ይመታዋል:: ልጇ የተመታባት እናት ደግሞ በተራዋ የልጇን መቺ ትመታለች:: በዚህ ወቅት የሁለቱ ልጆች እናቶች ወደጠብ ያመራሉ:: የአንደኛዋ ባል ለሚስቱ አግዞ የጐረቤቱን ሚስት ይደበድባል:: የተመቺዋ ባልም ከሚስቱ ደብዳቢ ጋር ይገጥማል:: የተደብዳቢው ባል ወገኖች ደግሞ ጥቃት ተሰምቷቸው ለበቀል ይዘጋጃሉ:: እንግዲህ የአዛውንቱ ምክር ልክ አይደለም? በእንጭጩ መቀጨት የነበረበት ጉዳይ ስር አልሰደደም? በውሾቹ ምክንያትስ መንደሩ ሁሉ ለጥፋት አልተመቻቸም?

ኢትዮጵያ ሰፊ ናት፤ ለሁላችንም ትበቃናለች:: ብትበቃስ አይደለ እንዴ ከህንድና ከቻይና ለመጣው ጭምር መሬቷ በርካሽ ዋጋ የተሰጠው¡ ታዲያ ለህንድና ለቻይና የሰፋች ኢትዮጵያ ለአማራው ልትጠብ ከቶ እንዴት ይቻላታል? እንደህዝብ ተሞክሮስ የምንቀስመው ከጃፓንና ከእንግሊዝ ብቻ ነውን? ሚኒጥ እና አማራስ ከህይወት ተሞክሮዎቻቸው አይማማሩም? ባህል፣ ጥበብ፣ ክህሎት አይለዋወጡም? አያዳብሩም? አያዋህዱም? አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ የሚገነባውስ የሰው ዝምድናና መስተጋብርን በክልል ከልክሎ የበድን አስፋልት መዓት በማስተሳሰር ነውን? አንድነታችንስ ለዳር-ድንበር መስዋዕትነት እና ለድንጋይ ካብ ግድብ መዋጮ ብቻ ነውን? ታዲያ እንዲህ ከሆነ፡- የቤኒሻንጉሉ ህዳሴ ግድብ ለአማራው ምኑ ነው? ለኔ ይህ የሰው ልጆችን ተፈጥሯዊ የመቀራረብና የመዛመድ ብሎም የመዋሃድ ዑደትን መግታት፤ ብሎም ሰዎችን በየአባታቸው ብሔር ወገን እየለዩ በአንድ ሰው-ሰራሽ መጋዘን ውስጥ ማጐር ከናዚው ሂትለር ዘረኛ የ'አርያን ንፁህ ዘር' ሰይጣናዊ ዕሳቤ ጋር የመንፈስ አንድነት ያለው የአውዳሚነት ዝንባሌና አዝማሚያ ነው:: የዚህ አካሄድ አቻነትም ከሩዋንዳው የኢንተርሃምዌይ የእልቂት ቁልቁለት፣ ወይም ከዚሁ ከናዚው የኦሽዊትዝ የሞት አዳራሽነት አሊያም ከቀዝቃዛው ጦርነቱ የምዕራብ እና ምስራቅ ጀርመን ከፋፋይ የበርሊን ግንብ ጋር ብቻ ነው::

### "የሸንበቆው ምርኩዝ"

ህገ-መንግስታችን በአንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 19.2 ላይ የሚከተለውን ይደነግጋል::

1. ህገ-መንግስቱ የአገሪቱ የበላይ ህግ ነው:: ማንኛውም ህግ፣ ልማዳዊ አሰራር እንዲሁም የመንግስት አካል ወይም ባለስልጣን ውሳኔ ከዚህ ህገ-መንግስት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

- ለዚህ አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ምን ምላሽ ይኖራቸው ይሆን?

2. ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌሎች ማህበራት እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው፣ ህገ-መንግስትን የማስከበርና ለህገ-መንግስቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው::

-ለዚህስ ኢህአዴግ እና አቶ መለስ ለጉራፈርዳ ተፈናቃዮች ስላለባቸው ኃላፊነት እና ተጠያቂነት ምን ይሉ ይሆን? ህገ-መንግስቱስ ልንመካበት የምንችል አስተማማኝ ዋስትና ሊሆነን ይችላል? አሊያስ ብዙዎች እንደሚሉት የሸንበቆ ምርኩዝ ይሆን?

ይኸው ህገ-መንግስት በክልሎች ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱ የፌዴራል መንግስት ጣልቃ እንዲገባ ሊታዘዝ እንደሚችል ሲጠቁም በአንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 16 ላይ እንዲህ ይላል፡- ‹‹በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር በራሱ አነሳሽነትና ያለክልሉ ፈቃድ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፣ በተደረሰበት ውሳኔ መሰረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል::›› ይህ ስልጣን የተሰጠው ለፌዴራል ተወካዮች ምክር ቤት ነው::

- ታዲያ እነዚህ ተፈናቃዮች ወኪላቸው ማነው? ብሔሩ አልታወቅ ያለው ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ብአዴን ሊወክላቸው ይችላልን? ታዲያ በግፍ ሲፈናቀሉ የት ነበር? ወይስ በግፍ የተፈናቀሉ 'ወገኖቹን' ወደተወለዱበት አካባቢ በማስመለስ ነው ለነርሱ 'ጥቅም' የሚሰራው? መልካም አስተዳደርና ዴሞክራሲ እየተባለ ቀን-ከሌት የሚለፈፈውስ በቃ ይኸው ነው???!!! ድንቄም መልካም አስተዳደር¡ ድንቄም ዴሞክራሲ¡

በዚህ የትንሳኤ ሰሞን ከቀዬአቸው ከተፈናቀሉት ውስጥ አንዱ አባወራ እንደገለፀው ባለቤቱ ለእሁ አጥቢያ ቅዳሜ ሌሊት ወንድ ልጅ ተገላግላለች:: ስሙንም 'አይሸበር!' ብዬዋለሁ ብሏል:: በአንድ ወቅትም ጠ/ሚኒስትር መለስ ሲናገሩ እንደሰማሁት፡- ‹‹…አገር ማለት ወንዙ፣ ተራራው፣ ሜዳው ሳይሆን በዋናነት ህዝቡ! ነው:: …›› ብለዋል:: ስለዚህ አይሸበርም አገር ነው:: አገር ደግሞ ሲሰደድ፣ ሲፈናቀል፣ ሲጐሳቆል ማየት ያሳዝናል:: ምን ማሳዘን ብቻ! ያስቆጣል:: እኔም በግሌ በዚህ ልቤ ተሰባብሯል::

‹‹አነሰ አይፈቅድ እርአይ ሙስናሁ ለሀገር
አምጣነ ሀሎኩ በዛቲ ሕይወት ምድራዊት››
(በሕይወት እስካለሁ ድረስ አገር ሲጠፋ ማየትን አልፈልግም) አፄ ገላውዲዎስ

አምላክ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ይባርክ! አሜን!



በሙስነህ አያሌው
muleayalew@yahoo.com

# ቤንች ማጂ ቀጣዩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እጣ ፈንታ አመላካች?

በኢትዮጵያ የብሔር ፖለቲካ ላይ ጥናት ያደረጉ ምሁራን በአብዛኛው አሁን እየተከወነ ባለው የፖለቲካ አስተዳደር ስርዓት ላይ ተቀራራቢ አቋም አላቸው:: የመጀመሪያው የፌዴራል ስርዓቱን ‹‹የትም ያልተሞከረ እና ተሞክሮም ለሃያ አመታት ያህል በተግባር ተጨባጭ ለውጥ ያላመጣ ነው›› ይሉታል:: የፌዴራሉ ክልሎችም ‹‹ራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር ይችላሉ›› ተብሎ የነበረውም መከራከሪያም ውሃ የሚቋጥር አልሆነም:: አቶ አሰፋ ፍሰሃ ***"Theory versus practice in Ethiopian ethnic federalism"*** በሚለው ፅሁፋቸው ላይ ይህንን ሀሳብ ያጠነክሩታል:: እንደርሳቸው አገላለፅ ከሆነ፣ ***‹‹በአሁኑ ጊዜ ክልሎች ራሳቸውን ከማስተዳደር አልፈው ፌዴራል መንግስት ለሚያወጣቸው ፖሊሲ እና ህግጋት ተፈፃሚነት በአጋዥነት የሚረዱበት አቅም ገና አላዳበሩም››*** ይላሉ::

ሌላኛው የፖለቲካ ተንታኞቹ መግባቢያ ነጥብ በአገራችን እስከዛሬ የተከሰቱትም ይሁን ሊከሰቱ ይችላሉ የሚባሉ የብሔር ቅራኔዎች ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች እና ባህሪያት አላቸው/ ይኖሯቸዋል ብለው ማመናቸው ነው::

**ብዙኃኑ በጥቂት ልሂቃን ላይ**፡- ይህኛውን የግጭት ምክንያታዊ ኃሳብ የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ተንታኞች እንደሚሉት ከሆነ ጥቂት የትግራይ ልሂቃን በብዙሃኑ ላይ ለረጅም ጊዜ በስልጣን የበላይ ሆነው ለመቆየት የሚያደርጉት ትንቅንቅ ‹‹ብዙሃኑን ለአመፅ ይገፋፋዋል›› ብለው የሚያምኑ ናቸው:: በዚህም ብዙኃኑን በጥቂቶቹ ላይ ማመጹ የብሄር ቅራኔ ለመፈጠር ፖለቲካውን ምቹ ያደርገዋል::

**በቀድሞዎቹ እና በአሁኑ ገዢዎች መካከል**፡- ሁለተኛው የብሔር ግጭት ሞዴል እንደሚለው ከሆነ ቀድሞ በአገሪቷ ላይ በገዢነት ትልቅ ቦታ የነበራቸው የማህበረሰብ ቡድኖች (አማራ) አሁን በስልጣን ላይ ካለው ቡድን (ትግራይ ልሂቅ) ጋር በጥቅም ይገባኛል ጥያቄ የሚፈጥረው ግጭት በኢትዮጵያ ለብሄር ቅራኔ ምክንያት ሁለተኛውን ረድፍ ይይዛል:: *(Amhara Vs Tigray)*

**በተጠቀሙትና ባልተጠቀሙት መካከል**፡- ሶስተኛው የብሄር ግጭት ሞዴል ትንተና የሚያጠነጥነው ‹‹በታሪክ አጋጣሚ እስከ አሁን ድረስ በአገሪቷ የፖለቲካ ታሪክ ላይ አንዳችም ጊዜ ተጠቅመን አናውቅም›› የሚሉ ቡድኖች በአንድ ወገን፤ ‹‹ከዚህ በፊት ተጠቅመው አልፈዋል/በአሁኑ ሰዓትም እየተጠቀሙ ነው›› ብለው በሚያምኗቸው ቡድኖች መካከል የሚፈጠር የግጭት መስመር / fault line/ በኢትዮጵያ ሌላኛው ለብሔሮች ግጭት አይነተኛ ምክንያት ናቸው ብለው ያምናሉ:: *(Non-privileged Vs privileged groups)*

## ተለምዷዊ ትርክት

**ማሳያ-1(case-1)**. የአፄ ኃ/ሥላሴ መንግስት የኢትዮጵያን አንድነት ለማስጠበቅ ከተጠቀሙባቸው ዘዴዎች መካከል ‹‹የአንድ ብሔርን ቋንቋ እና ማንነት በሌሎቹም ላይ በመጫን ወጥ የሆነ የፖለቲካ ስርዓት መመስረት ይቻላል›› የሚለው ዕምነታቸው ነበር:: ንጉሱ በተለይ የሸዋ አማራ እና የትግራይ ልሂቃንን የያዘ የመንግስት አስተዳደር መመስረታቸው እና ሌሎች ብሔሮችን ከፖለቲካው ጨዋታ ማግለላቸው ለአሁኑ የ‹‹*አማራ*›› ምንነት ትርጉም መዛባት ላይ የራሱን አሉታዊ የታሪክ መሰረት ጥሏል:: በጊዜው የተሰጣቸው ተቀባይነት የ‹‹አማራ›› ተወላጆችን በስራ እና በኑሮ አጋጣሚ ወደተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች እንዲስፋፉ አድርጓቸዋል:: መስፋፋትም ብቻ ሳይሆን በነበራቸው ተቀባይነት ምክንያት የ‹‹*አገረ ገዢነት*›› መንበሩም የእነርሱ ነበር:: በተመሳሳይ መልኩ የአፄው መንግስት ውድቀትን ተከትሎ የተቋቋመውም ወታደራዊ መንግስት የዚህ ብሔር ማንነትን ከገዢነት አስተሳሰብ ጋር ማዋሀዱን ቀጥሎበታል::

**ማሳያ-2(case-2)**. ስለዚህ ኢህአዴግ የብሔር ፖለቲካውን ወደ አደባባይ ሲያመጣ አስቀድሞ በመከራከሪያነት ያቀረበው የ‹‹*አማራ ገዢ መደብ*›› በታሪክ የነበረው የበላይነት ያበቃለት መሆኑን ተከትሎ ሌሎች ብሔሮች ራሳቸውን ማስተዳደር እንደሚችሉ ነፃነት እንደተሰጣቸው ማወጁ በማህበረሰቡ መካከል የ‹‹ጨቋኝ›› እና የ‹‹ተጨቋኝ›› አስተሳሰብ እንዲሰርፅ አድርጎታል:: ይህ ብቻ አይደለም:: ኢህአዴግ ተቀናቃኝ የፖለቲካ ፓርቲ በገጠመው ቁጥር ከአማራ የተዛባ የማንነት ትርጓሜ ጋር በማያያዝ በማስፈራሪያነት ይጠቀምበታል:: ለዚህ ማስረገጫ ቅንጅቶች በ97ቱ ምርጫ ወቅት የተሰጣቸውን የ‹‹*ነፍጠኛ*›› ስያሜ ማየት ይቻላል::

## በክልል የሁለተኛ ዜግነት……

ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ እ.ኤ.አ. በ2009 ***"Ethiopia: Ethnic Federalism and its Discontent"*** የሚል አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርቦ ነበር:: የዚህ ፅሁፍ ዋና አላማ የነበረው አገራችን እየሄደችበት ያለውን ብሔር ተኮር የፌዴራል ስርዓት በአገሪቷ የተፈለገውን ውጤት እያመጣ እንዳልሆነ ማሳየት ነው:: ጥናቱ በተለያዩ ጊዜያት ተከስተው የነበሩ ድንበር ዘለል እና በክልል ማዕቀፍ ውስጥ የተነሱ ግጭቶችን በዋቢነት ጠቅሶ አቅርቧል:: ይህ ሪፖርት በኢህአዴግ መንግስት የማንቂያ ደወል ከመሆን ይልቅ እንደተለመደው ‹‹ጉንጭ አልፋ ክርክር›› አልያም ‹‹የወጣበትን የወረቀት እና የቀለም ዋጋ እንኳ መሸፈን የማይችል››፣ ‹‹የተላላኪዎች ዘገባ›› አልያም በአቶ መለስ አነጋገር ‹‹የአይጥ ምስክር›› ድንቢጥ ከመባል አልተረፈም::

ሪፖርቱ መንግስት በሚገባ መርምሮት ቢሆንና የተባሉ ስህተቶችን ማረም ችሎ ቢሆን ኖሮ የአሁኑ አይነት የዜጎች ከተለያዩ አካባቢዎች በግዳጅ የመፈናቀል ክስተት እውን ባልሆነ ነበር:: ሪፓርቱ በክልሎች ውስጥ በሚገኙ በብዙኃን እና አናሳዎች መካከል በኢትዮጵያ በተለይ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም አስመልክቶ ቅራኔ ሊነሳባቸው የሚችልባቸውን አንዳንድ ነባራዊ ፖለቲካ ሁነቶችን ዳስሶ የመፍትሄ አቅጣጫም አሳይቶ ነበር::

በአገራችን በተለይ ‹‹አማራ›› የሚባለው ‹‹ብሔር›› ያልሰፈረበት ቦታ እና አካባቢ አለ ብሎ ማሰብ እንደሚከብድ ይገለéል:: እነዚህ ስፍራዎች እንደ የአካባቢዎቹ ያላቸው የቁጥር መጠንም ይሁን አሰፋፈር ይለያያል:: በአንዳንድ አካባቢዎች በከተማ ዙሪያ በብዛት ሰፍረው ሲገኙ ሌሎች አካባቢዎች ደግሞ በገጠር አካባቢ ተሰማርተው ይገኛሉ:: በከተማ አካባቢ ያሉት ነዋሪዎች በተለይ በንግዱ ኢኮኖሚ ዘርፍ ብዙ ሃብት ያፈሩ ሲሆን በገጠሩ አካባቢ የሚገኙት ቡድኖች ደግሞ በግብርናው ዘርፍ የተሳካላቸው ናቸው:: ኢህአዴግ የብሔር ፖለቲካውን በስራ ላይ ሲያውል አማሮች እና ሌሎች ብሔሮች/ደገኞች/ ከተሰጣቸው ክልል ውጭ በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሁለተኛ ነዋሪነት ፍቃድ እንዲያገኙ አስገድዷቸዋል:: ይህ ለውጥ በተለይ ዜጋውን ከኢትዮጵያዊነት ወደ ክልላዊ ማንነት ዝቅ እንዲል ያደረገ ነበር:: እርምጃው ነዋሪዎቹን ለሁለት እንዲከፈሉ አስገድዷቸዋል:: የመጀመሪያው አስቀድመው የክልሉ ነዋሪ በገዢው ፓርቲ አነጋገር ‹‹አገር በቀል›› (Indigenous) የሚባሉትን የራስ ገዝ አስተዳደር መብት ሲሰጣቸው ከሌላ አካባቢ በተለያየ ምክንያት የመጡትን ነዋሪዎች ደግሞ ወደ ሁለተኛ የዜግነት መብት ዝቅ እንዲሉ አስገድዷቸዋል::

ይህ የመብት ጥያቄ በአንድ ላይ ለረጅም አመታት አብረው በኖሩ የማህበረሰቡ አካሎች መካከል አለመተማመን እና ቅራኔ ከመፍጠሩ ባሻገር አገር በቀሎቹን በመሬቱ /ክልሉ/ ላይ ***‹‹የኔነት››*** ስሜት እንዲላበሱ ሲያደርግ ሌሎቹን ደግሞ ወደ ***‹‹አገራችሁ ሂዱ!››*** ወደሚል የመግፊያ ድምዳሜ ላይ እንዲደርሱ አስገድዷቸዋል::

ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ በእንዲህ አይነት የፖለቲካ ቅራኔዎች የተፈጠሩትን አንዳንድ ግጭቶች በምሳሌነት አቅርቧል:: ለምሳሌ በአሶሳ በበርካታ የአማራ እና የኦሮሞ ብሄሮች መካከል፤ በአሩሲ፣ በባሌ እና በሐረር ‹‹ሰፋሪዎች ይውጡልን›› በሚል የተካሄዱ ጭፍጨፋዎች፤ በደቡብ በሚኖሩ የሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ በሲዳማ እና ወላይታ ነዋሪዎች የተካሄዱ ግጭቶችን በማስረጃነት አቅርቧል::

ከላይ በትንታኔ ያቀረብኩትን የ‹‹ክልል ይገባኛል›› ጥያቄን ተከትለው የተፈጠሩ ግጭቶች እና በተወሰዱ እርምጃዎች ላይ ሁለት ማሳያዎችን እንመልከት::

***ማሳያ 1 (Case -1)*** ጋምቤላ፡- ኢህአዴግ ወደ መንበረ ስልጣን ከመምጣቱ በፊት ደርግ በሰፈራ ፕሮግራሙ ከተለያዩ አካባቢዎች ዜጎችን ለም ወደሆነው የጋምቤላ አካባቢ አስፍሯል:: ጋምቤላ ከቀድሞ ነዋሪዎቿ (Natives) አኙዋክ እና ኑዌር በተጨማሪም ደገኛ የሚባሉትን የአማራ፣ የኦሮሞ…… ብሔር ተወላጆችን በውስጧ እንድታቅፍ አስችሏታል:: የፌዴራል ስርዓት መታወጁን ተከትሎ ጋምቤላ ከዘጠኙ ክልሎች አንዷ እንድትሆን ሲደረግ በሰላም አብረው ተቻችለው ይኖሩ በነበሩ ብሔሮች መካከል ቅራኔ ተጀመረ:: አገር በቀል የሆኑት ነዋሪዎች ‹‹መሬታችን›› እና ‹‹ክልላችን›› ማለት ሲጀምሩ ሌሎቹን ነዋሪዎች ደግሞ ሁለተኛ የክልሉ ዜጋ አድርገው በማሰባቸው አማሮች ወደ አማራ ክልል፣ ኦሮሞዎች እና የሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎችን ( በኢህአዴግ አጠራር ሰፋሪዎችን) ወደ ክልላቸው ይመለሱ የሚል ጥያቄ እንዲያነሱ አስገድዷቸዋል::

ደገኞቹ የሚመለሱበት ቦታ አልነበራቸውም:: ክልል ይኑራቸው አይኑራቸው የሚያውቁት ጉዳይ የለም:: ያፈሩትን ሀብትና ንብረት እንዴት አድርገው ይውሰዱ? ስለዚህ የመጣውን ከመቀበል ውጭ ሌላ አማራጭ አልታያቸውም:: ፕ/ር ጆን አቢቢኒክ ‹‹Ethnic based federalism and ethnicicty in ethiopia reassessing the experiment after 20 yers›› በመሚለወ ጥናታዊ ፁፋቸው እ.ኤ.አ. በ1996 ‹‹አገር በቀል›› የሆኑት አኙዋኮች ‹‹በደገኞቹ›› ላይ በወሰዱት እርምጃ ለብዙ ዜጎች ህይወት መጥፋት ምክንያት ቢሆንም ችግሩን ለመታደግ ሲባል የፌዴራል መንግስት በወሰደው ጣልቃ ገብነትም ቢሆን ብዙ ‹‹አገር በቀል›› ነዋሪዎች መገደላቸውን ይናገራሉ ነው::

***ማሳያ 2 (Case -2) ቤንች ማጂ ዞን***፡- የሚንጥ ብሔረሰቦች ይባላሉ:: ከ1993 ዓ.ም. በፊት ይተዳደሩ የነበሩት በሸኮ ወረዳ ውስጥ ነበር:: ሌሎች ብሔሮች እራሰን በራስ የማስተዳደር ህልውና ሲሰጣቸው (the Silte model) እነርሱም ‹‹ለራሳችን የሚሆን ወረዳ መመስረት እንፈልጋለን›› የሚል ጥያቄያቸውን ለሚመለከተው የመንግስት አካል አቀረቡ:: ነገር ግን ከበላይ የተሰጣቸው መልስ አጥጋቢ አልነበረም:: ‹‹አሁን ያላችሁት ብዛታችሁ ትንሽ ስለሆነ ወደፊት ቁጥራችሁ ሲያድግ ልታሟሉት ከሚገባው መስፈርት አንዱን እውን ስለምታደርጉ ያን ጊዜ ተመልሳችሁ ኑ›› ተባሉ:: ስለዚህ ይህንን የህዝብ ቁጥር ለማሟላት ያስችላቸው ዘንድ ዘዴ ማውንጠን ጀመሩ:: አንድ መላም መጣላቸው:: ከተለያዩ አካባቢዎች መጥተው በቡና ለቀማ እና በጉልበት ስራ በሌሎች ወረዳዎች የሚኖሩ የአማራ ክልል ተወላጅ የሆኑ ዜጎችን መጠቀም የሚል:: የሚንጥ ማህበረሰብ አባላት እንዲህ የሚል ማስታወቂያ አስነገሩ - ‹‹ወደ ወረዳችን መጥቶ ማልማት እና መጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ዜጋ ይምጣ እና ይጠቀም››:: በዚህ መልካም ብስራት የተበረታቱ ዜጎች ራሳቸውን ለመቻል ብሎም ንብረት ለማፍራት ወደ አካባቢው ሳይውሉ ሳያድሩ ተመሙ:: የቀበሌ እና የወረዳ አስተዳዳሪዎችም ለእነዚህ ዜጎች የሚሆን መሬት በህጋዊ መንገድ ሸንሽነው አከፋፈሏቸው:: የሚንጥ ብሔሮችም የተጠየቁትን መስፈርት አሟልተው ዳግም ቀረቡ:: ምኞታቸው ተሳክቶም ራስን በራስ የማስተዳደር መብት አገኙ:: ወረዳቸውም ***‹‹ጉራ ፈርዳ››*** ተባለች::

የተረት አገር ላይ አይደለ የምንኖረው? የሚንጥ ብሔሮች ጨዋታውን ጨረሱ እና አመረሩ:: ‹‹በቃ! የፈለግናችሁ ለዚህ ስለነበር በህገ-ወጥ መንገድ የወሰዳችሁትን መሬታችንን አስረክባችሁ ወደ መጣችሁበት ክልል ተመለሱ›› የሚል:: **(*ተጨማሪ ምንጭ ሪፖርተር ጋዜጣ መጋቢት* 26/2004 *ዓ.ም ዕትም*)**

ይህንን የወረዳውን አስተዳዳሪ ትዕዛዝ የሚያጠናክር ሪፖርት ከደቡብ ክልል ፕሬዚዳንትም ቢሮ ወጥቷል:: ‹‹የአገሪቱ ህገ-መንግስት ተጥሷል›› እንዳንል በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ በተፃፈው ደብዳቤ ላይ እንዲህ የሚል ቃል ሰፍሮ እናገኛለን:: ‹‹በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ሰፈራን በሚመለከት ያለው አሰራር ከክልል ክልል የሚፈፀም ሳይሆን በክልሎች በውስጣቸው ብቻ እንዲፈፀም የጋራ አገራዊ ስምምነት ተደርጓል::›› ***(ለቤንች ማጂ ዞን አስተዳደር በ2001 በክልሉ ፕሬዘዳንት ከተፃፈ ደብዳቤ የተወሰደ)***

ስለዚህ ለዚህ አይነት ትእዛዝ ህጋዊነትም ይሁን ህገ-ወጥነት ማመሳከሪያ የምናገኘው በክልሎች ህገ-ደንብ ውስጥ ይሆናል ማለት ነው:: ለዚህ ማስረጃ የሚሆነን የደቡብ ክልል ህገ-መንግስት ከሌሎች አካባቢዎች መጥተው ስለሚኖሩ የሌሎች ክልል ነዋሪዎች የሚለውን ማየት ያስፈልጋል::

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ህገ-መንግስት አንቀጽ 34 ‹‹የሌሎች ክልሎች ተወላጆች መብት›› በሚለው ስር ለነዚህ ዜጎች የሚሰጣቸውን የህግ ከለላ እንዲህ አስፍሮታል፡-

1. የሌሎች ክልሎች ተወላጆች የሆኑ ኢትዮጵያውያን በዚህ ክልል ውስጥ እንደማንኛውም የዚህ ክልል ተወላጅ ሰርቶ የመኖር፣ ከስፍራ ስፍራ በነፃ የመዘዋወር፣ ሀብትና ንብረት የማፍራትና የመያዝ መብት አላቸው::

2. የክልሉን፣ የዞኑንና የልዩ ወረዳውን ቋንቋ የሚያውቅ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በማንኛውም የክልሉ፣ የዞኑና የልዩ ወረዳው ሕዝባዊና መንግስታዊ ስራ ውስጥ ተመርጦ የመስራት መብት አለው::

በአንቀጽ 34 (1) (2) ላይ የሰፈሩት የሌሎች ክልል ነዋሪዎች መብት አሁን በተወሰደው የማፈናቀል እርምጃ የክልሉ ህገ መንግስት ተጥሷል የሚል እምነት አለኝ:: መንግስት ሰዎቹ የያዙት መሬት ህገ-ወጥ ነው ከተባለ መጠየቅ ያለባቸው የወረዳው እና የክልሉ አስተዳዳሪዎች እንጂ ነዋሪዎቹ (‹‹ሰፋሪዎቹ››) አይደሉም:: ከ78,000 በላይ ህዝብ ሲሰፍር እንዴት ዝም ሊባል ቻለ? ‹‹ህገ-ወጥ ነው›› ከተባለ የባለይዞታ ሰነድ እንዴት ሊይዙ ቻሉ? ይህንን ያህል አመት ህገ ወጥ ስራ ሲከናወን እነርሱ የት ነበሩ? ነዋሪዎቹ ለብዙ አመታት ያፈሩትን ሃብት እና ንብረት በአንድ ጀንበር ለቀው እንዲወጡ መደረጉስ ከሰብዓዊ መብት አንፃር አግባብ ነው? ወዴትስ ነው እንዲሄዱ የተፈለገው? ህገ-ወጥ ናቸው ከተባለስ ህጋዊ አድርጐ/ተለዋጭ መሬት ሰጥቶ/ እዚያው ማቆየት ለምን አልተቻለም/አልተፈለገም? ወደ አገራችሁ ሂዱ ማለትስ ምን ማለት ነው? አገሩ የማን ነው?!

በማሳያ 1 (ጋምቤላ) እና በማሳያ 2 (ቤንች ማጂ ዞን) መካከል ያሉትን በገዥው ልሂቃን ስያሜ ‹‹ደገኞች›› ‹‹ከአገር በቀሉ›› ጋር ባለው ቅራኔ መካከል እና በተወሰደው ፖለቲካዊ እርምጃ ላይ ሁለት መሰረታዊ ልዩነቶችን ማየት ያስችለናል::

**ማሳያ 1**- በጋምቤላ የተፈጠረው ችግር ‹‹በአገር በቀሎች›› እና (ከአንድ በላይ በሆኑ ‹‹ደገኞች››) መካከል ነበር:: በተጨማሪም ቅራኔው በከተማ ውስጥ ሀብትና ንብረት አፍርተው በሚኖሩ ደገኞች ላይ ሲሆን ለተፈጠረው ችግር የመንግስትን ጣልቃ ገብነት እናያለን::

**በማሳያ** 2- ላይ ያለው ተሞክሮ ከዚህ የተለየ ሆኖ እናገኛለን:: ቅራኔው አንድ ለአንድ ከመሆኑም በተጨማሪ የመንግስት ጣልቃ ገብነት ፈፅሞ የለውም::

## "Ethnic-Apartheid"

የአማራው ክልል ተወላጆች በተለያዩ ጊዜያት በመንግስት የተሰጠው ‹‹የጨቋኝ››ነት ተቀጥላ እያደር ዘር እያፈራ ይገኛል:: ኢትዮጵያ በምትባል አንዲት አገር ውስጥ ብዙ አገሮች እየተፈጠሩ ይገኛሉ:: የኢህአዴግ መንግስት ስርዓት በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ እና በእነዚህ ብሔር ቡድኖች ላይ ተደጋጋሚ መገፋት እና መባረር እጣ ፈንታቸው እየሆነ ከመጣ ምን ሊፈጠር ይችላል? የሚለውንም ማየት ተገቢ ይመስለኛል::

ኢህአዴግ ገና መንበረ ስልጣኑን እንደያዘ ከአማራ ክልል ላይ እየቆረሰ ወደ ሌሎቹ ያጠቃለላቸው መሬቶች እና በማህበረሰቡ ላይ የወሰዳቸው አሉታዊ እርምጃዎች ቀስ በቀስ ‹‹ለአማራ ህዝብ ህልውና እቆማለሁ›› የሚል ድርጅት እንዲፈጠር እንዳስቻለ አቶ ዘላለም ቁምላቸው የሚባሉ ምሁር ይናገራሉ::

አቶ ዘላለም፣ ‹‹የኢትዮጵያዊነት እና የአማራነት መለያዎች ህብር›› በሚለው ፅሁፋቸው ላይ ‹‹ይህንን የህዝብ ግፍ ለመታደግ ሲባል የመላው አማራ ህዝቦች ድርጅት /መአህድ/የሚል ድርጅት እንዲመሰረት ምክንያት እንደተፈጠረ ይከራከራሉ›› :: አሁንም ቢሆን እርምጃው በዚህ ከቀጠለ አማራውን ብቻ ማ°ከል ያደረገ ፅንፈኛ ብሄር ተኮር ቡድን እንደማይመሰረት ምንም መተማመኛ አይኖርም:: አሁን ባለው ሁኔታ በዚህ መንገድ የሚቋቋም ብሄር ተኮር ተቃዋሚ ድርጅት ፖለቲካውን አደገኛ ያደርገዋል:: ከዚህ በተጨማሪም አሁን የተጀመረው የማፈናቀል እርምጃ ወደ ሌሎች የክልል ዞኖችና ወረዳዎች ሊዛመት የሚችልባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ:: **(በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ድብዳቤ ላይ በደቡብ ክልል ውስጥ ያሉ ሌሎች ዞኖችም ተመሳሳይ መንገድ ሊከተሉ እንደሚገባ የሚጠቁም አንቀፅ እንዳለው ልብ ይሏል)** የዚህ አይነት እርምጃዎች የሚፈጥሩት የፅንፈኝነት ስሜት በብሄሮች መካከል የበቀል ፅዋ መርጨታቸው አይቀሬ ስለሚሆን በተቻለ አቅም ጥንቃቄ ያስፈልገዋል:: እያንዳንዱ ክልል ቀስ በቀስ በውስጡ ያሉትን የሌሎች ክልል ተወላጆች ማባረር ከጀመረ በአገራችን ታይቶ የማይታወቀውን ብሔር ተኮር አፓርታይድ ልናይ እንደምንችል እርግጠኛ መሆን ይቻላል::

## መውጫ መንገድ…

***ማሳያ*** **1 (Case -1)**፡- በአፄ ኃ/ስላሴ ስርዓት ላይ የነበራቸውን ጥላቻ ለመግለፅ ተማሪዎቹ የግድ ከተጨቋኝ ወገን መሆን አይጠበቅባቸውም ነበር:: በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተሰባሰቡ ከተለያዩ አካባቢ የመጡ ተወላጆች (ጨቋኝ የሚባሉትንም ጨምሮ) በንጉሱ ላይ ያሰሙት የተባበረ ድምፅ የንጉሱን ዙፋን ለማነቃነቅ የወሰደበት ጊዜ በጣም አጭር ሊባል የሚችል ነበር:: እነ ዋለልኝ መኮንን፣ እነ ማርታ እና የሌሎቹ ብሄር ተወላጆች የነበራቸው የ‹‹ያገባኛል››፣ ‹‹ይመለከተኛል›› የሚለው አገራዊ አንድነት ለድል አብቅቷቸዋል::

***ማሳያ*** **2 (Case -2)**፡- በብሔር ፖለቲካው ሃያ አመታትን አሳልፈናል:: ከዚህ በኋላ ወደ ኋላ መመለስ የማንችልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: ገዢ ልሂቃኑ እንተወው ቢባል እንኳን እንዳይሆን አድርገው ቆላልፈውታል:: ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ቀስ በቀስ ከላያችን፣ ከውስጣችን እየተገፈፈ መጥቷል:: እርስ በርስ በጥርጣሬ መተያየት ከጀመርን እነሆ ብዙ አመታትን አሳልፈናል:: አባቶቻችን ሰርተውታል ከምንለው ታሪካዊ ስህተት በባሰ የኛ ትውልድ ጥፋት ሰርተናል አሁንም እየሰራን እንገኛለን:: እርስ በርስ ለመሬት፣ ለቋንቋ፣ ለብሄር፣ለሀብት ብለን ተላልቀናል:: ምን አይነት አገር እየተፈጠረች እንደሆነ ማስተዋል ተስኖናል:: ልጆች እየተወለዱ ነው:: ምን አይነት አገር ለማውረስ እየተዘጋጀን እንደሆነ ቆም ብለን ማየት ይገባናል:: እንደ ባዕድ ከአገሬ ውጣ እና ውጪ የሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሰናል:: የአንዱ ማህበረሰብ ቁስል ሌሎቻችንን ላይ እስካልደረሰ ‹‹አያገባንም›› ማለቱን ተያይዘነዋል:: መፍትሄው ቀላል ነው:: የኢትዮጵያ ፖለቲካ ቅንነትን ብቻ ነው የሚፈልገው:: ቅን እና ኢትዮጵያዊ የሆነ መሪ ያስፈልገናል:: ከብሔራችን ማንነት በበለጠ ኢትዮጵያዊ አንድነት ሊያስተሳስረን ይገባል:: አሁንም ጊዜ አለን:: አልረፈደም:: ኢትዮጵያ ለሁላችንም ትበቃናለች::

# የወጣቱ የፖለቲካ ፍዘት

ወጣቱ ዓይኑን ከፖለቲካ ላይ ነቅሏል፡፡ ፖለቲካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያለው ተሳትፎና መሳብ አናሳ ሆኗል፡፡ እንደ ማግኔት የሚስቡት ሌሎች ያነሱ ጉዳዮች ሆነዋል፡፡ የፖለቲካው ማግኔት መሳብ ያለበትን አካል ሊስብ አልቻለም፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የወጣቱ ድርሻ ከፍ ያለ የነበረ ቢሆንም አሁን አሁን ግን የፖለቲካ ፍዘት (Political apathy) በከፍተኛ ሁኔታ እየተስተዋለ ነው፡፡

### ያ ትውልድ

የወጣቱ ላቅ ያለ የፖለቲካ ተሳትፎ በከፍተኛ ደረጃ መታየት የጀመረው በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግስት በተነሳው የተማሪዎች ንቅናቄ ወቅት ነው ማለት ይቻላል፡፡

‹‹መሬት ላራሹ›› የሚለውን መፈክር ያነገቡት የወቅቱ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በኃይለ ሥላሴ ከስልጣን መወገድ ረክተው ወደኋላ አልተመለሱም፡፡ ለሀገሪቱ ያዋጣሉ ያሏቸውን የተለያዩ የፖለቲካ መስመሮች ተከትለው፣ ትግላቸውን በፓርቲ ደረጃ ጭምር ቀጠሉ፡፡ በከፍተኛ ደረጃ አንባቢና ጠያቂ የነበሩት የዛ ትውልድ አባላት የዘመኑን መንፈስ ተከትለው ለሀገራችን ያዋጣል ያሉትን የሶሻሊዝም ርዕዮት ከማርክስ እና ከሌኒን እያጣቀሱ ይዘምሩት ገቡ፡፡

በእርግጥ የዛ ትውልድ ወጣት የፖለቲካ ተሳትፎ ከፍተኛ የነበረውን ያህል ያስከተለው ውጤትም አስከፊ ነበር፡፡ የጊዜው ወጣቶች በኢሠፓ፣ በኢህአፓ፣ በመኢሶን፣ ወዘ ሊግና በመሳሰሉት የፖለቲካ ፓርቲዎች ታቅፈው በፖለቲካው መድረክ የተሳተፉ ቢሆንም በተለይ በደርግና በኢህአፓ መካከል የነበረው ልዩነትና ግጭት በቀይ ሽብርና ነጭ ሽብር ሊፈታ መሞከሩ ከፍተኛ ጠባሳ ትቶ አልፏል፡፡

### ቀጣዩ ዘመን

በደርግ ዘመን የተከሰተው የእርስ በእርስ እልቂት ከዛ በኋላ ለመጣው ትውልድ አስቃቂ ዜና መሆኑ አልቀረም፡፡ ወንድም፣ ወንድሙን የገደለበትን ታሪክ የሰማው አዲሱ ትውልድ ፖለቲካን በመጥፎ ገፅታው እንዲረዳውና ራሱን ከፖለቲካ እንዲያገል ሳያደርገው የቀረ አይመስልም፡፡ የቀይ ሽብርንና ነጭ ሽብርን ክስተት እያየና እየሰማ ያደገው ትውልድ ፖለቲካን ሞት የሚታጨድበት መስክ አድርጐ ለመቁጠር ተገዷል፡፡ ልዩነቶች በጉልበትና በጦር መሳሪያ በሚፈቱበት ሀገር የበቀለ ወጣት እሱም ጉልበተኛ ከመሆን ወይም ከጉልበተኞቹ መንደር ራሱን ከማግለል ውጪ አማራጭ የለውም፡፡ እና አብዛኛው የትውልዱ አባል ሁለተኛውን አማራጭ መርጦ ራሱን ከፖለቲካ አገለለ፡፡

### ምርጫ 97

በኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመን የወጣቱ የፖለቲካ ተሳትፎ ጐልቶ የታየው በምርጫ 97 ወቅት ነው፡፡ ምርጫ 97 ወጣቱ በሀገሬ ጉዳይ የምር ያገባኛል ብሎ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ በወቅቱ የነበረው አንፃራዊ የነፃነት መንፈስ ወጣቱ በልበ ሙሉነትና ያለፍርሃት ሀሳቡን እንዲያራምድና የወደደውንና የፈቀደውን እንዲመርጥ አድርጐታል፡፡ ነገር ግን ያ መልካም ጅምር እንደነበረ አልቀጠለም፡፡ የምርጫውን ቀን ተከትሎ በተፈጠረው የመንግስትና የተቃዋሚዎች እሰጣ ገባ እና ህዝቡ የምርጫውን ውጤት ለማስከበር ባደረገው እንቅስቃሴ ምክንያት በመንግስት የተወሰደው የግድያ እርምጃ መልካሙና ዴሞክራሲያዊውን ምርጫ በሀዘን እንዲደመደም ሰበብ ሆነ፡፡

### ከ97 በኋላ

ምርጫ 97 የተጠናቀቀው ህዝቡ እንዳላሰበው ሆኖ ነው፡፡ እውነተኛ ነፃ ምርጫ እንደሚካሄድ አምኖና በነበረው የክርክርና የቅስቀሳ ሂደትም የዴሞክራሲን መኖር ተማምኖ ከፍተኛ ተሳትፎ ያደረገው ህዝብ በተለይም ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል በተፈጠረው ነገር ወሸመጡ ተቆረጠ፡፡ ያልጠበቀው የመንግስት እርምጃ ክፉኛ አስበረገገው፡፡ ፖለቲካን በሩቁ የምትለው ስሜት ዳግም ተቀሰቀሰች፡፡ በነፃነት ላመኑበት ዓላማ መታገልና መንቀሳቀስ ሞትን ማስከተሉ፤ ወጣቱን ፖለቲካ ውስጥ ጥፋት እንጂ ልማት የለም፣ ጉዳት እንጂ ጥቅም አይገኝም ወደሚል አዝማሚያ ገፋው፡፡

ይህ ሳያንስ ከምርጫው በኋላ በኢህአዴግ የተወሰዱ ተከታታይ እርምጃዎችና የፀደቁ ህጐች የፖለቲካውን መስክ የበለጠ አስፈሪ አደረጉት፡፡

የሲቪክ ማህበራት ህግ፣ የፕሬስ ህግና የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ በነፃነት ማሰብና ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማድረግ አደገኛ አደጋ እንደሆነ ወጣቱ እንዲረዳ የሚያስገድዱ ክስተቶች ሆኑ፡፡

### የህልውና ጉዳይ

ከምርጫ 97 በኋላ ኢህአዴግ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ አባላትን በብዛት መመልመል ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ በዩኒቨርስቲዎች ላይ በትኩረት ሰርቷል፡፡ አባል ካልተኮነ የሚፈጠረውን የስራ እጥነት ችግር በማሰብ አብዛኛው ወጣት በአባልነት ተመዝግቧል፡፡ ይህ እርምጃ ኢህአዴግን ወጣቱን በቁጥጥር ስር ለማዋል እና እንቅስቃሴውን ለመግታት እንዲሁም በቅርብ ክትትል ስር እንዲሆን ለማድረግ ጠቅሞታል፡፡ በተቃራኒው የተቃውሞው ፖለቲካ በፍዘት እንዲበከል አስገድዷል፡፡

ሰራተኛው ወጣትም ከስራ ላለመባረርና እድገት ለማግኘት ሲል አባል ሆኗል፡፡ ወጣቱ ትውልድ መሰረታዊውን ፍላጐት ማሟላት ባለመቻሉ፣ የእለት ጉርሱንና የዓመት ልብሱን በየትኛውም መንገድ ለማሟላት ከመኳተን ውጪ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ማንሳት እንዳይችል እንደሆነ የሚጠቅሱ ተንታኞች አሉ፡፡

ይህ በእርግጥም የኢህአዴግ ፍላጐት ይመስላል፡፡ በዕለት ተዕለት ኑሮ ተይዞ፣ ስለሌሎች ጉዳዮች ማሰብ እንዳይቻል ማድረግ፡፡ አሁን ባለው ሁኔታም ፍላጐቱ ተሳክቶለታል ማለት ይቻላል፡፡

### የአደጋው መብዛት

ወጣቱን ከፖለቲካው ከሚያሸሹት ምክንያቶች አንዱ የአደጋው መብዛት ነው፡፡ ቤተሰብ የመርዳት ኃላፊነት በጫንቃቸው ላይ የወደቀባቸው ወጣቶች አሉ፡፡ እነዚህ ወጣቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ለማድረግ ፍላጐቱ ቢኖራቸውም፣ ፖለቲካ ውስጥ በመግባታቸው ምክንያት እነሱ ላይ ብቻ ሳይሆን ቤተሰባቸው ላይም ችግር እንዳይደርስ ይሰጋሉ፡፡ ከታሰሩ ቤተሰባቸው የሚደግፈው አካል እንደሚያጣና በችግር እንደሚሰቃይ ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ ራሳቸውን ከፖለቲካው ያርቃሉ፡፡ የሚመጡ መከራዎችን ለመቀበል ዝግጁ ሳይሆኑ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ማድረግ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ከባድ ይመስላል፡፡ ስለዚህ ብዙሃኑ ወጣት የጥንቃቄ ኑሮን መርጧል፡፡ ወጣቱ የሚያስበውን እውነተኛ ሀሳብ በማንፀባረቅና የሚያምንበትን ነገር በማድረግ በሽብርተኝነት ወንጀል የመከሰስ አደጋ ውስጥ ከመግባት ወይም በደህንነት ሰራተኞች ክትትልና ማስፈራሪያ ስር ከመውደቅ ዝም ብሎ መኖርን ለጊዜው በጀ ብሎ ተቀብሎታል፡፡

### የትምህርት ፖሊሲ

የትምህርት ፖሊሲው ራሱ ለፖለቲካው ፍዘት አስተዋፅኦ አድርጓል የሚሉ ተከራካሪዎች አሉ፡፡ የቀደመው ትውልድ ንቁ የፖለቲካ ተሳትፎ ጠንካራ ከነበረውና ምሁራዊነትን ከሚያበረታታው የትምህርት ፖሊሲ የመጣ ነው፡፡ አሁን ስራ ላይ ያለው የትምህርት ፖሊሲ ትምህርቶች በጥልቀት የማይሰጡበት፣ ምርምር እምብዛም የማይታይበትና ለብ ለብ በሆነ ሁኔታ የተማሩ ‹መሀይማን› በብዛት የሚፈለፈሉበት እንደሆነ የሚተቹ የጉዳዩ ተከታታዮች ጥቂት አይደሉም፡፡ ያሁኑ የትምህርት አሰጣጥ ሐንድአውት ሸምድዶ የመግባት ወይም ከኢንተርኔት ላይ ገልብጦ የማቅረብ እንጂ ጥልቅ ጥናትና ምርምር እንዲሁም በሰፊው ማንበብ የማይታይበት መሆኑ በፖለቲካው መልክዓ

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

# ትንሳኤ የሚያስፈልገው የኢህአዴግ ፍርሃትና የእኛ ስጋት

ዳንኤል ተፈራ

እነሆ ትንሳኤ፡፡ እነሆ ሞቶ መነሳት፡፡ እነሆ ክርስቶስ ለሰዎች ህይወትን ለመስጠት ሞተ፡፡ የፍቅር መጨረሻው ስጦታ ነብስን እስከመስጠት እንደሚደርስ አስተማረ፡፡ ከዚያም በሦስተኛው ቀን ሞትን ድል ነስቶ ተነሳ፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች ይህንን ትንሳኤ ይሉታል፡፡ ፋሲካ፡፡ እንኳን ለብርሃነ ትንሳኤው አደረሳችሁ፡፡

ያኛው የመንፈሳዊ ህይወታችን ትንሳኤ፤ የክርስቶስ ታላቁ አስተምህሮት ፍቅርን ሳይሰስቱ እስከመጨረሻው መስጠት ለእኛ ለሰዎች ብዙ ጊዜ የወደቅንበትና ከባዱ ፈተና ነው፡፡ በእውነት ባሁኑ ዘመን ያጣነው ትልቁ ነገር ፍቅር ይመስለኛል፡፡ እናም የመንፈሳዊውን ትንሳኤ ለሊቃውንቱ ልተውና ለምድራዊው ህይወታችን፣ ለተጐሳቆለው ኑሮአችን፣ ጋንግሪን ለያዘው ፖለቲካችን፣ በቁሳዊ ሀብት ክምችት ላበዱት ባለስልጣኖቻችን፣ ጥበብን መሸቀያ ላደረጉት አርቲስቶቻችን፣ ፍርሃት ስላጥለቀለቀው ገዥ ፓርቲያችን፣ የቻይና ብልጭልጭ ኢኮኖሚ ስላጠቃው ኢኮኖሚያችን፣ በየጊዜው እየተቆለለ የሊማሊሞ ዳገትን ስላከለው የሸቀጦች ዋጋችን፣ ምርጫ ሲደርስ በቶክሲዶ/ ሙሉ ልብስ/ ሽክ ብለው እንደ መስቀል ወፍ ብቅ ስለሚሉ ተቃዋሚዎቻችን፣ ከመንግስት ሌባ ጋር እየተመሳጠሩ ሀገሪቱን የዘረፉ ‹‹ልማታዊ›› ባለሀብቶቻችን፣ እኛ ደግሞ እንደ ህዝብ ስጋታችን… ይሄ ሁሉ ትንሳኤ የሚፈልግ ችግራችን ነው፡፡

ስላሉብን ዘርፈ ብዙ ችግሮቻችን እያነሳን ስንፅፍ ችግራቸው የተቀረፈላቸው ካድሬዎች ክፉኛ ይበሳጫሉ፡፡ ልማቱን ለማደናቀፍ የሚያሴሩ፣ የእንትን ተላላኪዎች ለማለትም ይቃጣቸዋል፡፡ ብዙዎቹ ከስርዓቱ ጋር በጥቅም የተሳሰሩ ናቸውና ለምናቀርባቸው ትችቶች ተገቢ መልስ በመስጠት ፈንታ በተለመደውና በኖሩበት የሴራ ትንተና ይፈርጁናል፡፡ ‹‹የፈሪ ዱላው አስራ ሁለት ነው›› እንደሚባለው ይሆናሉ፡፡ የገዢውን ፓርቲ መልካም ስራ ኢቲቪ እየቀባባ ማቅረቡ ያንስባቸዋል፡፡

ከላይ የዘረዘርኳቸውንና ትንሳኤ ያስፈልጋቸዋል ያልኳቸውን ችግሮች ‹‹አይ እንሱማ ትንሳኤ አግኝተዋል!›› ብሎ አንድ፣ ሁለት በማለት የሚያስረዳኝ ካለ እሰየው ነው፡፡ የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች ግን ‹‹የብዕር ግብግብ›› የምትባል ነገር ብዙ አትመቻቸውም፡፡ እናም በየጊዜው ከሚያወጧቸው ‹‹ህጐቻቸው›› እየጠቀሱ በአይጋፎረም በኩልና በሌሎች ከኢህአዴግ ጋር ፍቅር በወደቁ ሚዲያዎቻቸው በኩል ሊያስፈራሩን ይፈልጋሉ፡፡ በጣም አስቂኝና አስደናቂ በሆነ መልኩ የ3 ብር እስክርቢቶ ብቻ በእጃችን ያለ ወጣቶችን እነሱ ቡና ከተጣጡትና ክርስትና ከተነሱት ቀይ ይሁን ጥቁር ከማናውቀው ሻዕቢያ ጋር ለማነካካት ይሞክራሉ፡፡ የድሬዎችን ቋንቋ ልዋስና ‹‹አቦ እዚያው በፀበላችሁ!›› ብያለሁ፡፡ የኤርትራ መንግስት ጋር በፍቅር የወደቃችሁም እናንተ፣ የተጣላችሁም እናንተ፡፡ የምትተዋወቁም እናንተ ናችሁ፡፡

እኔ ግን መፃፌን እቀጥላለሁ፡፡ ስለገዢው ፓርቲ ችግር ወይም ደግሞ በኢትዮጵያውያን ላይ ስላለው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግር የምፅፈው ሚርተኛ ስለሆንኩ አይደለም፡፡ እውነት ስለሆነ ብቻ ነው፡፡ ዋጋ በየዕለቱ በሚቀለልበት ሀገር፣ ችጋር የብዙዎችን የመኖር ህልውና በተገዳደረበት ጊዜ፣ በብሄር ፖለቲካ የተነሳ ኢትዮጵያዊያን ብሄርቸው ከረጢት ውስጥ በገቡበት ወቅት በርካታው፣ በተለይ ደግሞ አምራቹ ኃይል ወደ ውጭ ለመውጣት ቀዳዳ በሚፈልግበት ሀገር ጥጋብ ነው፣ ፌሽታ ነው፣ ሁሉም ሙሉ ነው ብሎ ለመፃፍ የቃላት ስስት ሳይሆን ልማታዊ ጋዜጠኛ መሆን ይጠይቃል፡ ፡ ወይም እንደ ማሽን ተሞልቶ ሲያበቃ ያንን ብቻ የሚናገር ዕቃ መሆን ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ ምርጫው ማሽን የመሆንና ያለመሆንይመስለኛል፡ ፡

ሀሳብ የማያልቅበት ፀሀፊ ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን) አዲስ ጉዳይ መጽሔት ላይ የ‹‹ዘበርጋ ጥያቄ›› በሚል ርዕስ ስር ሞጋች ጥያቄዎችን ያለመታከት ይደረድራል፡፡ እንዲህ በማለት፡-‹‹ብዙ ዕድገቶች፣ በዚህን ያህል መቶ ተለውጠናል፤ በዚህን ያህል በመቶ ድህነት ቀንሷል የሚሉ አሀዞች ሞልተዋል፡፡ ግን እነዚህ አሀዞች በምድር ላይ የት ነው ያሉት? የስኳር ምርት እጥረት የለም፣ ዘይትም በሽበሽ ነው፡፡ ስንዴም ከበቂ በላይ አለ የሚሉን ሰዎች ለምን የት እንዳለ አይነግሩንም? ስኳር በስንት ልመናና ዝምድና እያገኘን እንደሆነ አልሰሙም ማለት ነው? ይሄንን ተከማችቶበታል የሚሉትን ቦታ ለምን አይጠቁሙንም?…›› እያለ የፖለቲከኞች ፕሮፓጋንዳና ምድር ላይ ያለውን ተጨባጭ እውነታ እያሰናሰነ ያሳየናል፡፡

ካድሬዎች ለእንደዚህ አይነት ከራር ጥያቄዎች መልስ የላቸውም፡፡ መልሳቸውም አንድና አንድ ነው ‹‹ፀረ-ልማት!›› የሚል፡፡ ከአባቶች እንደሰማነው በደርግ ጊዜ የወታደሮች አካሄድ ያልጣማቸው ምሁራን ‹‹ኧረ አብዮቱ ሀዲዱን እየሳተ ነው?›› የሚል ስጋት አዘል ጥያቄ ሲያነሱ የሚሰጣቸው መልስ አንድ ነው፡፡ ‹‹የአብዮቱ ጠላቶች›› የሚል፡፡ እነዚህ ሀገር ወዳድ ስጋተኛ ግለሰቦችም ‹‹የአብዮት ጠላት ናቸው›› በሚል አይቆምላቸውም፡፡ ክቡር ህይወታቸውን ይነጥቋቸዋል እንጅ! ስለደርጉ አብዮት መሳሳት የሚናገሩት ወይም የሚፅፉት በእርግጥም የአብዮቱ ጠላቶች አልነበሩም፡፡ ጠላትነታቸው የመንግስቱ ኃይለማርያምና የስልጣናቸው እንጅ!

‹‹አብዮተኛውን›› ደርግ በመሳሪያ የጣለው ‹‹አብዮተኛው›› ኢህአዴግም በተለይ ከ97 ወዲህ እየተከተለ ያለው መንገድ ሲታይ ከደርጉ ጋር የሚያመሳስለው ብዙ ነገር አለው፡፡ ‹‹እሳት ካየው ምን ለየው!›› ይሉት አይነት ነው፡፡ ኢህአዴግ መለስ ዜናዊ የሚባሉ የማይነኩና የማይገሰሱ ሰው ፈጥሯል፡፡ ልክ እንደ ደርግ ጊዜ ሁሉ የኢህአዴግን የፖለቲካና የኢኮኖሚ አካሄድ መተቸት፤ ኢህአዴግ ሀዲዱን የሳተ ባቡር መሆኑን መናገር ስም ያሰጣል፡፡ ኢህአዴግንና መሪውን ተችቶ መፃፍ ‹‹ሽብርተኛ፣ የአመፅ ጥሪ አስተላላፊ›› ያስብላል፡፡ ከዚያም አልፎ ያሳስራል፣ ያሰድዳል፡፡

ትንሳኤ የሚሻው የገዢው ፓርቲ አስተሳሰብም ይሄው ነው፡፡ ኢህአዴግ ለባለፉት 20 አመታት ቃል የገባቸውና ያልፈፀማቸው ጉዳዮች በርካታ ናቸው፡፡ ቢያንስ ታጋዮች የሞቱለትን ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ማስፈን አልቻለም፣ ቢያንስ የምንጉርሰው እናጣ ይሆን ከሚል ስጋት አላላቀቀንም፡፡

በርካታ ጉዳዮችን ማንሳት የምንችል ይመስለኛል፡፡ ዋናው ግን ፍርሃቱ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲያችን በፍርሃት ተውጦ፣ ፍርሃቱ ደግሞ ለእኛ ስጋት ሆኖን መኖር ከጀመርን ብዙ ዓመት ቢሆንም ዋናው የፍርሃት ዘመን የሚጀምረው ግን 97 የተባለ ዓመት መጥቶ ካለፈ በኋላ ነው፡፡ አንዳንድ የኢህአዴግ የውስጥ አዋቂዎች ሲናገሩ እንደሰማነው የአልባኒያ ኮሚኒዝም አቀንቃኝ የነበሩት የአሁኑ የቤተ መንግስት ሰዎች የያንጊዜ ታጋዮች ወደ ምዕራባዊያኑ ካፒታሊዝም የመጡት በድንገት ነው፡፡ የቀዝቃዛው ጦርነት ማክተምና የሶብየት ህብረት ጐራ መፈራረስ አንዱ ገፊ ምክንያት ሊባል ይችላል፡፡ ከዚያም ወደ ምዕራቡ ዓለም ፊትን ማዞር የግድ ሆነ፡፡ የካፒታሊዝም አቀንቃኝ የሆኑት እነ አሜሪካና አውሮፓ በበላይነት የሚቆጣጠሩት የዓለም ባንክና አይ.ኤም.ኤፍ የአልባኒያ ኮሚኒዝም ተከታይ የሆኑት እነአቶ መለስንና ፓርቲያቸውን ማጥመቅ ፈለጉና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት፣ የነፃ-ገበያ መር ኢኮኖሚና ፕራይቬታይዜሽን (የመንግስት ተቋማትን ወደ ግል ማዞር)… የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀመጡ፡፡ እንደአቶ ተመስገን ዘውዴ ያሉት ስለፕራይቬታይዜሽን ሲነሳ ‹‹ኢህአዴግ ወርቁንና ማዕድኑን ወደ ግል አዙሮ የዱቄት ፋብሪካውን ይዞ ተቀመጠ፡፡›› በማለት ከወርልድ ባንክ የመጣባቸውንና እዳና እነሱ ሂሳቡን እንዴት እንዳወራረዱት ያነሳሉ፡፡

ኢህአዴግም የሆዱን በሆዱ አድርጐ ብራቸውንም መመሪያቸውንም ተቀበለና ጉዞው ተጀመረ፡፡ በግራ በኩል የአልባኒያው ኮሚኒዝም እየጐተተው፤ በቀኝ ደግሞ ካፒታሊዝም እያላጋው በመንታ ጐዳና እየሄደ 1997 ዓ.ም. ምርጫ ላይ ደረሰ፡፡ ይህ ዓመት ኢህአዴግ የምዕራባዊያንን ቀልብ ለመግዛት የፈለገበት ዓመት ነበር፡፡ አንዳንድ አስተያየት ሰጭዎች ደግሞ እንደ አሮጌ የእባብ ቆዳ ሶሻሊስትነቱን አውልቆ ለመጣል የተነሳበት ዓመት አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው ደግሞ በኢህአዴጉ ፊታውራሪ አቶ መለስ ዜናዊ የተነገረው፡- ‹‹እንከን የለሽ ምርጫ እናደርጋለን!›› የሚለው ልብ አንጠልጣይ ቃል ነው፡፡ መቼስ ጠቅላይ ሚኒስትሩ መስጠቱ ነው እንጂ የሚያቀታቸው ልብ ማንጠልጠሉን ይችሉበታል፡፡

እነዚህ ቅድመ ታሪኮች የኢህአዴግ ፍርሃት መነሻዎች ናቸው፡፡ እንደተባለው የ97 ምርጫ እንከን የለሽ መሆኑ ቀርቶ ባለ ብዙ እንከን ሆነና ተጠናቀቀ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ አቶ በረከት በመጽሐፋቸው እንደነገሩን ራሳቸው ከፈጠሩት ናዳ ለማምለጥ ሩጫ ጀመሩ፡፡ የፍርሃት ሩጫ የምላችሁ ይህንን ነው፡፡ ከናዳው ለማምለጥ የያዙት ስልት እነሱ እንደነገሩን በስራ መጠመድና ቅቡልነትን ማረጋገጥ ሳይሆን በሌላ መንገድ ነበር፡፡

ይሄው ስውር መንገድም የፍርሃት መንገድ ነው፡፡ በመጀመሪያ በምንም ሆነ በምን ፓርላማውን በሙሉ መያዝ፤ ከዚያ ለጥቆ ደግሞ እያንዳንዱን ተቋምና ግለሰብ ሊቆጣጠሩ የሚያስችሉ ህጐችን ማውጣት ነበር፡፡ ፓርላማውን ጠቅልሎ መያዝ በአንድ ለአምስት ስልት ተሳክቷል፡ ከዚያ በኋላ የወጡ ህጎችንም ታውቋቸዋላችሁ፡፡ ከሚፅፉት እስክርቢቶና ወረቀት በስተቀር ምንም የሌለውን ግለሰብ ሁሉ እየተከተሉ እንደ ቀይ ካርድ የሚመዙትን የፀረ-ሽብርተኝነት ህግ ጨምሮ የወጡ ህጐችን መርምሩ፡፡ ከጀርባቸው ‹‹ፍርሃት›› ተሸሽጐ ታገኛላችሁ፡፡ ትንሽ ነገር ስለጫርን እጃቸውን የሚቀስሩብን ስለሚፈሩ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

ለኢህአዴግ የፍርሃት አስተሳሰብና ፍርሃቱ ገዝፎ ምን ያመጣብን ይሆን? ለሚለው የእኛ ስጋት ትንሳኤ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የገዢው ፓርቲ ተከታይ አቀንቃኝ ያልሆነ ሁሉ፤ የተለየ አስተሳሰብ ያለውን ሁሉ ‹‹ጠላቴ›› ነው እያሉ በፍርሃት ከማለቅ ቀረብ አድርጐ መነጋገርና መወያየት ይጠቅማል፡፡

እስቲ ከማጠናቀቁ በፊት አንድ የቅርብ ድርጊት ላንሳ፡፡ የዋጋ ውድነቱ የመኖር ዋስትናቸውን የተፈታተነባቸው መምህራን የደመወዝ ጥያቄ አነሱ፡፡ የተጨመረው ማላገጫ ነው ለእኛ ይህ አይገባንም አሉ፡፡ ከዚያም እንደሰማነው ማስፈራሪያ የታከለበት ማስታወቂያ ተለጠፈባቸው፡፡ የኢንተርኔት አገልግሎትም እንዲቋረጥባቸው ሆነ…. ግን ለምን? ሰብስቦ ማወያየትና ችግሩን መፍታት ነው የሚቀለው ወይስ ማዋከብና ግንኙነታቸውን መቁረጥ? በጣም በርካታ ፍርሃት የወለዳቸውን ምሳሌዎች ማንሳት አይገድም፡፡ ግን ፍርሃቱ አይጠቅምም፡፡ እነሆ ከፊታችን ትንሳኤ እየመጣ ነው፡፡ የኢህአዴግ የፍርሃት አገዛዝም ትንሳኤ ያስፈልገዋል፡፡ ንስሃ መግባትም እንዲሁ፡፡

መልካም በዓል!

በዚህ ዓምድ የአገራችንን ህጎች ፣ ዓለም አቀፍ ህግጋት ፣ በሀገራት መካከል የተደረጉ ስምምነቶችን እንዲሁም ለንፅፅር እና ለማገናዘቢያ ይረዳን ዘንድ ሌሎች ሀገሮችን ህጎች መሰረት በማድረግ ከማንኛውም አይነት የፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መልኩ ትንታኔ ይሰጣል፡፡

# ፅንስን ማቋረጥ (ውርጃ) ሕጋዊ ወይስ?

ከሚፈጥረው የማህበራዊ ህይወት መስተጋብር ቀውስ፣ በትውልድ ቀጣይነት ላይ ካለው አሉታዊ ተፅዕኖ፣ በጉዳዩ ዙሪያ የሚነካቸው ግለሰቦች ውስን አለመሆን እንዲሁም ከሚያስከትለው የሞራል ዝቅጠት አንፃር ፅንስን ማስወረድ (ወይም በተለምዶ አጠራር ውርጃ) በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ መንግስታትን፣ የፓርቲ መሪዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ የጐሳ አለቆችን የሃሳብ ልዩነት እንዲፈጥሩና በቃላት እንዲቆራቆዙ ምክንያት ሆኗል፡፡ መንግስታት ፅንስን ማስወገድ በመፍቃድ እና በመከልከል ዙሪያ ከተቀናቃኞቻቸው ከፍተኛ ሙግት ገጥሟቸዋል እየገጠማቸውም ነው፡፡ የሃይማኖት መሪዎች የጉዳዩን አሳሳቢነት ለተከታዮቻቸው አሳስበዋል ውርጃን መፈፀም በሃይማኖቶቻቸው አስተምህሮት መሰረት ክልክል እንደሆነ በአደባባይ ተናግረዋል፡፡ የጉዳዩ አሳሳቢነት በተለያዩ ተያያዥ ምክንያቶችና የግለሰቦች መብት ከፍተኛ ቦታ እየተሰጠው ሲመጣ አብሮ በመነሳት ለሙግት እና ለውዝግብ እየተመቸ ቢሄድም አለመግባባቱ የጀመረው ከጥቂት ዓመታት በፊት እንዳልሆነ አንዳንድ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ 1960ዎቹ ድረስ በአሜሪካ ፅንስን መስወረድ ህገወጥ የነበረ ሲሆን ከስልሳዎቹ በኋላ ግን በተለያዩ ወገኖች አማካኝነት ክርክር ማስነሳት ጀመረ፡፡ በ1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ የአሜሪካን ጠቅላይ ፍርድ ቤት በውርጃ ህጋዊነት ዙሪያ የሚያሻማ ፍርድ ሰጠ፡፡ ፍርድ ቤቱ በ1973 በያዘው Roe Vs wade ጉዳይ በአሜሪካ በየትኛውም ክልል የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ፅንስን ስለማስወረድ ያደረጉትን ክልከላ እንዲያነሱ ድርጊቱም ህገ-መንግስታዊ እንዳልነበረ በመግለፅ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በየትኛውም ዓለም በውርጃ ላይ ያለው ውዝግብ በግለሰቦች መብት እና በመንግስታት ፍላጐት መካከል ያለው አለመግባባት እንደሆነ በዚሁ ዙሪያ ጥናት ያደረጉ ምሁራንን ያስማማል፡፡ በአንድ በኩል የግለሰብ መብት በሌላ በኩል ደግሞ የማህበረሰብ መብት /Collective right/ የውዝግቡ መንስኤ እንደሆኑ ይታሰባል፡፡ ፅንስ በራሱ ለተፈጥሮ ሰው የሚሰጠው መብት ያልተሰጠው መሆኑ በሌላ ወገን ግለሰቦች በራሳቸው አካላት ላይ የሚፈፅሙት ማናቸውም ነገር በህግ የተከለከለ አለመሆኑ ፅንስን ማስወረድ መፍቀድ እና መከልከልን አስቸጋሪ አድርጐታል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ፅንስን ማስወረድ በአብዛኛው የህብረተሰብ ክፍል እንደመጥፎ ተግባር የሚወሰድ እና በሀገሪቷ በሚገኙ ብዙ ተከታይ ያላቸው ሃይማኖቶች እንደ ውግዝ የሚቆጠር ተግባር ነው፡፡ ምንም እንኳ በፍትሐብሔር ጉዳይ አንድ ፅንስ እስካልተወለደ ድረስ ይህ ነው የሚባል ለተፈጥሮ ሰው የሚሰጥ ሙሉ መብት ባይኖረውም የሀገራችን የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ፅንስን ማስወረድ በሕግ ከተፈቀደላቸው ምክንያቶች በስተቀር ክልክል እንደሆነ እና ከዚህ ውጭ ውርጃም የሚፈፅሙ ግለሰቦች ወንጀለኛ እንደሚሆኑ ደንግጓል፡፡ የኢፌድሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ከአንቀፅ 545 እስከ አንቀፅ 552 ውርጃን በተመለከተ ሊያስቀጡ የሚችሉ ሁኔታዎችን ከነ አጠቃላይ መርሁ ደንግጓል፡፡ በመርህ መልክ የተቀመጠው አንቀጽ 545 ንዑስ አንቀፅ 1 እንዲህ ይላል፡- በአንቀጽ 551 ከተገለፀው ውጭ በማናቸውም መልኩ በየትኛውም ደረጃ ላይ ያለን ፅንስ አውቆ ማቋረጥ ከዚህ በሚከተሉት አንቀፆች አማካኝነት ያስቀጣል፡፡ በዚህ አንቀጽ መርህ መሰረት ፅንስን አውቆ ማቋረጥ (ምክንያቱም ፅንስ ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድም ሊወርድ ስለሚችል ነው) ያስቀጣል፡፡ ፅንስ በሰው ሰራሽ መንገድ በባህላዊም ይሁን በዘመናዊ መልኩ ሊቋረጥ ይችላል፡፡ ከዚህ ሌላ ሳይታሰብ በስራ መብዛት ወይም ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ሊቀጥል የማይችልበትም ሁኔታ አለ፡፡ ይሁን እንጂ በሀገራችን ህግ መሰረት አውቆ ፅንስን እንዳይቀጥል ማድረግ በምንም መልኩ የተደረገ ቢሆንም ያስቀጣል፡፡ ከዚህ ሌላ አንቀጽ 545 (1) ውስጥ የተቀመጠው መሰረታዊ ጉዳይ የፅንሱ ደረጃ ነው፡፡ በዚህ መርህ መሰረት ፅንሱን ለማውረድ የፅንሱ እድሜ ወይንም የእድገት ደረጃን እንደ ማስረጃ ወስዶ መከራከር አይቻልም፡፡ በየትኛውም ደረጃ የሚገኝን ፅንስ በህግ ከተፈቀደው አግባብ ውጭ ማቋረጥ ወንጀል ነው፡፡ አንዳንድ ሀገራት ፅንስን በማስወረድ ላይ ያላቸውን አለመግባባት ከሁለቱም ወገን ፅንፍ ይዞ ላለማስቀመጥ ጥቂት ወራት የሆናቸውን ፅንሶች ማስወረድ ህገ ወጥነት እንዳልሆነ በህጐቻቸው አካተዋል፡፡ ይሁንና ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ አልተካተተም፡፡ የፅንሱ የእድገት ደረጃ እንደ መከራከሪያ ሊቀርብ አይችልም፡፡

በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት ፅንስን ማቋረጥ የሚፈቀድባቸው ሁኔታዎች በአንቀጽ 551 የተካተቱት ሲሆኑ የቀሩት ግን ህገ ወጥ ተግባራት እንደሆኑ አንቀጽ 545 ደንግጓል፡፡ ለመሆኑ ፅንስን ለማቋረጥ በህግ የተፈቀደላቸው ሁኔታዎች ምን ምን ናቸው? አንቀጽ 551 ፅንስን ለማቋረጥ በህግ የተፈቀዱ ሁኔታዎች ብሎ ይዘረዝራል፡፡ አንቀፅ 551 (1)፡- እውቅና ካለው የህክምና ተቋም ሙያው በሚፈቅደው የጊዜ ገደብ ውስጥ የሚደረግ ፅንስ የማቋረጥ እርግዝናው የመጣው በአስገድዶ መድፈር ወይም ከፍላጐት ውጭ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከሆነ፣ የእርግዝናው መቀጠል እናትየውን ወይንም ፅንሱን አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ ፅንሱ የማይድን የአካል ጉዳት ያለበት ከሆነ እና እናትየው በአካል እና በአእምሮ ብቃት ችግር ኖሮባት ልጅ መውለድ የማትችል ከሆነ በሀኪሞቹ ትእዛዝ መሰረት ፅንሱን ማስወረድ እንደሚቻል ደንግጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንቀፅ 551 (2) አደገኛ የሆነ አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ አንቀጽ 75 በሚፈቅደው መሰረት ፅንስን ማቋረጥ ወንጀል እንዳልሆነ ይገልፃል፡፡ አንቀጽ 75 ደግሞ ሁኔታውን ለማስቀረት ሌላ አማራጭ ከሌለ ፅንስን ማቋረጥ ወንጀል ሊሆን እንደማይችል ይገልፃል፡፡

ምንም እንኳን ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ፅንስን ማቋረጥ ወይም ማስወገድ ወንጀል ባይሆንም ህጉ ያስቀመጣቸው ቅድመ ሁኔታዎች መሟላታቸው የግድ ነው፡፡ ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ እና ዋነኛው አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢኖሩ እንኳ ፅንሱን የማቋረጥ ስራው መፈፀም ያለበት እውቅና ባለው የህክምና ተቋም መሆን አለበት፡፡ በዚህ ውጭ የሚደረግ የፅንስ ማቋረጥ ተቀባይነት ስለማይኖረው ከወንጀለኛነት አያድንም፡፡ በአንቀፅ 551 (1) (ሀ) ውስጥ የተጠቀሰው የመጀመሪያ አስገዳጅ ሁኔታ እርግዝናው የተከሰተው በአስገድዶ መድፈር ወይም ከፍላጐት ውጭ በሆነ የግብረ ስጋ ግንኙነት ከሆነ እውቅና ባለው የህክምና ተቋም የሚደረግ ፅንስ ማቋረጥ ህጋዊ ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ ውርጃን የሚፈቅድ ህግ በሌሎች ሀገራትም በስራ ላይ ያለ ሲሆን ዋና ዓላማው አስገድዶ መድፈር የተፈፀመባት ግለሰብ ከደረሰባት አደጋ በተጨማሪ አደጋው ይዞት ከሚመጣው የተፈጥሮ፣ የስነ ልቦና እንዲሁም የኢኮኖሚ ችግር ለመታደግ ታስቦ የተቀመጠ ነው፡፡ በአስገድዶ መድፈር ምክንያት ያረገዘችው ግለሰብ ከደፈራት ሰው ፅንሱ ሊወስድ የሚችለው ዘረ መል በውስጡ ተፈጥሮአዊ ችግሮች ካሉት በፅንሱ በወደፊት ህይወት ላይ አደጋ ሊፈጥር ስለሚችል እናትየው ያለፍላጐቷ ባጋጠማት ግንኙነት ምክንያት የዚህ አደጋ ገፈት ቀማሽ እንዳትሆን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ተፈጥሮአዊ ተያያዥ ችግሮችም በወደፊት የልጇ ህይወትና በእርሷ ላይ ችግር ይፈጥራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ፅንሱን ካልፈለገችው ብታስወርደው እንደወንጀል አይቆጠርባትም፡፡ ሌላው ችግር ግለሰቧ ሊደርስባት ከሚችለው የስነ ልቦና ችግር አንፃር ልጅን የመጥላት እና በደፈራት ግለሰብ አይን የማየት ሁኔታ ሊኖር ስለሚችል ለሚወለደው ልጅ ደህንነት እንዲሁም ለእናትየው የስነ-ልቦና ጤንነት ሲባል ፅንሱን እውቅና ያለው የጤና ተቋም ሄዳ ብታቋርጠው እንደ ወንጀል አይቆጠርም፡፡ አስገድዶ በመደፈር የመጣን ፅንስ ለማቋረጥ ህጋዊ ሽፋን የተሰጠበት ሌላው ምክንያት በሚወለደው ልጅ ምክንያት እናትየው ሊገጥማት የሚችሉትን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ከወዲሁ ለመታደግ ነው፡፡ ምንም እንኳ እናት ለልጅዋ ማድረግ የሚገባት ነገሮችን ህግ ቢያስገድድም እናቶችም ይህን የማድረግ የሞራል ግዴታ ቢኖርባቸውም እንደዚህ ዓይነት የህይወት መስመር ውስጥ ለመግባት የእናትየው ፍላጐት አሁን ያላት የኢኮኖሚ አቅም እና ሌሎች ጉዳዮች ሊወስኑት ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዱብዳ የሚፈፀሙ አስገዳጅ ምክንያቶች በእናትየውም ሆነ በሚወለደው ህፃን የወደፊት የኑሮ ሁኔታ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ስለሚችሉ እናትየው ፅንሱን ለማስወረድ ከፈለገችና በተገቢው ቦታ ሄዳ ከፈፀመችው ህጉ ሽፋን ይሰጣታል፡፡ ይቀጥላል፡፡

ቸር እንሰንብት፡፡

## የነፃው ፕሬስ ... ከገፅ 2 የዞረ

ፕሬስ ለማፈን መወሰኑን ያሳያል፡፡ ይህን ቅጣት መክፈል ያልቻሉ የፕሬሱ አባላት ቅጣታቸው ወደ እስር ይዛወራል፡፡ ዶ/ር ቴሬሴ “A test of democracy: Ethiopia’s mass media and freedom of information proclamation” በሚለው ስራቸው እንደሚያወሱት ይህን መሰል የተጋነነ የገንዘብ ቅጣት የፕሬሱን የገንዘብ ምንጭ በማድረቅ ጋዜጦቹን ወደመዘጋት ያቀርባቸዋል፡፡ የፕሬሱ የተለምዶ የገንዘብ ምንጭ ማስታወቂያ እና ሽያጭ ቢሆንም ብዙዎቹ ተቋማት ስርዓቱ በመልካም ዓይን በማያያቸው ፕሬሶች ላይ ማስታወቂያ ማውጣትን ከህልውናቸው ጋር በማያያዛቸው ጋዜጦቹ በአንባብያን ላይ ብቻ እንዲመሰረቱ አድርጓቸዋል፡፡ ከብዙ ውስጣዊ እና ውጪያዊ ተግዳሮቶች አንፃር የጋዜጦቹ የሽያጭ ቁጥር እጅግ አነስተኛ መሆኑ በዛው ልክ የጋዜጦቹን ገቢ ዝቅ ያለ አድርጐታል፡፡

ገዢው ፓርቲ እነዚህ ጉዳዮች ላይ ያለው አቋም ግልፅ ይመስላል፡፡ ጋዜጦች ላይ ማስታወቂያ እንዲወጣ የሚሹ ድርጅቶችን በተመለከተ ‹‹ማስታወቂያ የሚያስነግሩ ተቋሞች በተለይም የመንግስት ድርጅቶች እና ልማታዊ ባለሀብቶች ማስታወቂያቸውን ለስርዓቱ አደጋ በሚሆኑ ተቋሞች ላይ ማውጣቱን እንዲተዉት›› ይመከራል፡፡ በመጋቢት ወር 1999 ዓ.ም. ‹‹የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ትግል እና አዮታዊ ዴሞክራሲ›› በሚል ርዕስ ፓርቲው ያሳተመው ድርሳን እንደሚያትተው ፕሬሱ የሚቆምበትን የአንባቢዎች ክፍያ እንዴት እየተቀዛቀዘ ሊሄድ እንደሚችል ሲያብራራ ‹‹ዜጎች በሂደት ስርዓቱን ለአደጋ የሚጥል ሚዲያ መጠቀም በራሳቸው ላይ እባብ መጠምጠም መሆኑን ተገንዝበው›› ጋዜጦቹን ከመግዛት እንደሚቆጠቡ ይጠቅሳል፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ መኖር ያለበት ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ሚዲያ›› ነው የሚለው ይህ ዶክመንት የእነዚህ ሁለት ሁነቶች መፈጠር ፓርቲው የሚፈልጋቸው ጋዜጦችን ብቻ በአደባባዩ ላይ እንዲያስቀር ያስችለዋል፡፡

ዶ/ር ቴሬሴ እንደሚሉት በዚህ አነስተኛ ገቢ ላይ የቆሙ የፕሬሱ አካላት ላይ ተደጋጋሚ የገንዘብ ቅጣት መጣል የጋዜጦቹን ህልውና ያከስማል፡፡ ፀሐፊው ‹‹የገቢ አቅምን መጭመቅ›› ሲሉ የጠሩት ይህ የገዢው ፓርቲ ስልት ፖለቲካዊ መነሾ እንዳለው ማሳያ የሚሆነው የህፃናት ጉልበት ብዝበዛን አልያም አስገድዶ መድፈርን በተመለከተ የተቀመጡት የገንዘብ ቅጣቶች ፕሬሱ ላይ ከተጣሉት እጅግ ያነሱ መሆናቸው ነው፡፡ ትዝታ ከበደ የተባሉ ፀሐፊ “Ethiopia: Independent media professionals deplore press law” በሚለው መጣጥፋቸው እንደሚያነሱት ለአስገድዶ መድፈር ወንጀል የተቀመጠው የገንዘብ ቅጣት ከአንድ ሺህ ብር አለመብለጡ ፕሬሱ ላይ ከተቀመጠው ጋር ሲታይ የፕሬሱን ቅጣት አስከፊነት ያጎላዋል፡፡

ከፕሬስ ህጉ በተጨማሪ ገዢው ፓርቲ ፕሬሱን ለማድቀቅ እየተጠቀመበት ነው ተብሎ በብዙ የጋዜጠኞች ተቆርቋሪ ተቋማት የሚከሰስበት ህግ የፀረ-ሽብርተኝነቱ አዋጅ ነው፡፡ ይህን ብዙዎች ‹‹አፋኝ›› ሲሉ የሚተቹትን አዋጅ በተመለከተ የሚሰጡ አስተያየቶች ወደ አንድ ጫፍ ያዘነበሉ ናቸው፡፡ ዘካሪያስ ሙሉታ የተባሉ ፀሐፊ በጥልቅ ሰብዓዊ መብት ጥሰት የሚወነጀለው ስርዓት ይህን ህግ የማውጣቱ መነሻ አምባገነናዊ ጉዞው ላይ የሚቆሙ ዜጐችን ለመጨፍለቅ ነው ሲሉ ይሟገታሉ፡፡ ፀሐፊው አዋጁ በሽብር ወንጀል ተጠርጥረዋል የሚባሉ ዜጎችን በተመለከተ ለፖሊስ የሰጠው ገደብ አልባ ስልጣን፣ የመንግስት የደህንነት ተቋማት ስልክ፣ ፋክስ፣ ኢንተርኔትና መሰል ነገሮችን ካለዜጎች ፍቃድ የመጥለፍ መብት ማግኘቱ አልፎም የደህንነት ተቋሙ የሚያገኛቸውን መረጃዎች ምንጭ ለፍርድ ቤት እንዲያስረዳ አለመገደዱን በመጥቀስ አዋጁ የመንግስቱን የስራ አስፈፃሚ ክፍል ጡንቻ ለማጎልበት እንደሚጠቅም “Antidemocratic system of governance in Ethiopia under absolute dictatorship of TPLF regime” በሚለው ፅሁፋቸው ይከራከራሉ፡፡

የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ የፕሬሱን ህልውና ስለመፈታተኑ ከቀደመው ዓመት ወዲህ የተከሰቱት ሁኔታዎች በቂ ማሳያ ይመስላሉ፡፡ በዚህ አዋጅ መነሾ ሁለት ጋዜጦች ሲዘጉ፣ ከስደት የተረፉት ጋዜጠኞች ከባድ እስር ገጥሟቸዋል፡፡ ይህ አዋጅ በውጭ የሚገኙ ድረ-ገጾችን እና የቴሌቪዥንን ጣቢያንም በ‹‹ሽብርተኝነት›› ለመክሰስ ጠቀሜታ ላይ ውሏል፡፡ ለገዢው ፓርቲ እነዚህን የዲያስፖራ ሚዲያዎች በዚህ ክስ መክሰስ ሚዲያዎቹ በሀገር ውስጥ የሚኖራቸውን የመረጃ ምንጭነት ለማድረቅ ህጋዊ ሽፋን ይሰጠዋል፡፡ የአዋጁ ተራዛሚ ተፅዕኖ አሁን በሀገር ውስጥ ባሉት ጋዜጦችና ጋዜጠኞች ላይ እያሳደረ ያለው ጫና (Chilling effect) ከበድ ያለ ይመስላል፡፡ የጋዜጠኞች መብት ተቆርቋሪ ተቋሙ ሲ.ፒ.ጄ “Attacks on the press” በሚል ርዕስ ባወጣው መድብል ላይ ኢትዮጵያን በተመለከተ አስተያየቱን ያሰፈረው የተቋሙ አማካሪ ቶም ሮድስ ‹‹ግራ-የሚገባ››´ሲል የከሰሰው አዋጅ ወደ ፕሬሱ እጁን መዘርጋቱ ከባድ የፖለቲካ ስህተት እንደሆነ ይናገራል፡፡ ‹‹ሽብርን የሚያበረታቱ ፅሁፎችን›› በተመለከተ አዋጁ የዘረዘራቸው ጋዜጠኞችን ለመክሰስ እየዋሉ ያሉ አንቀፆች ለፖለቲካዊ ትርጓሜ በሚጋለጡ ሀሳቦች ስለመሞላታቸው ብዙ ተንታኞች ይስማማሉ፡፡ በወሳኝ ሀገራዊ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ የሚወጡ ዘገባዎች እና ትንታኔዎች ላይ ጥልቅ ገደብ የሚያደርገው ይህ አዋጅ የመጨረሻ ግቡ ማህበረሰቡን ከአንድ ሚዲያ ብቻ በሚገኝ መረጃ መጠርነፍ ይመስላል፡፡

## ስለአፄ ቴዎድሮስ ... ከገፅ 3 የዞረ

ያደርጋቸው የቴክኖሎጂ ሽግግርን ጭምር ተልመው በመንቀሳቀሳቸው ነው፡፡ ጋፋት የያኔዋ ‹‹የኢንዱስትሪ ዞን›› እንደነበረች ከብዙ ፅሑፍት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ የእጅ ሙያ ያላቸውን አውሮፓውያን ጋፋት ላይ በማስፈር ልዩ-ልዩ መሳሪያዎች እንዲመረቱ ያደርጉ ነበር፡፡ ጋሪ፣ ፋስ፣ መዝጊያና ይህን የመሳሰሉትን ስራዎች ቴዎድሮስ መሰልቸት ስለጀመሩ የኢንዱስትሪ ዞኑ ምርቱን ወደ መድፍና አዳፍኔ እንዲያሳድግ መጎትጎት ጀመሩ፡፡ ለዚህም ገንዘብ፣ እህል፣ ማር፣ ቅቤ የትኛውንም አስፈላጊ ነገር በገፍ ከማቀረባቸው ሌላ ማበረታቻ የብር ጋሻ፣ ወርቅ ቅብ የበቅሎ ማሰሪያ፣ በቅሎና ፈረስ ይሸልሙ ነበር፡፡ እንዲህ ያደርግ የነበረ የዘመነ-መሣፍንት አንድ ገዢ ካለ በዕውቀቱ ሊነግረን ይገባል፡፡

አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማስለጥ ከመጣር ባሻገር እራሳቸውም የተግባሩ ተሳታፊ ነበሩ፡፡ ዶክተር ሔንሪ ብላንክ ‹‹የእስራት ዘመን አበሻ አገር›› በተሰኘ መጽሐፉ ላይ ‹‹አፄ ቴዎድሮስ ከወደቡ ላይ ተቀምጠው ጥይት እየሰሩ ‹ስራዬን ታያለህን? በዚህ ስራ አላፍርበትም› አሉ›› ይለናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገፅ 116 ላይ እንዲህ የሚል አስፍሯል፡-

‹‹አፄ ቴዎድሮስ በጣና ባሕር ላይ የሚንሳፈፉ ጀልባዎች ለማሰራት ያላቸው እምነትና ፍላጐት ገና የፀና ስለነበር የሌሎቹን ርዳታ ለማግኘት እንዲረዳቸው ሲሉ ራሳቸው ወርደው መርከብ መስራት ጀመሩ፡፡ ሰፊ ወለል ያለውና በከባድ መንኰራኵር የሚንቀሳቀስ ጀልባ ሰሩ፡፡ እንዲያውም ፓድል ስቲመር ፈልስፈው ሰርተው ነበር፡፡ ዳሩ ግን የሎኮሞቲቭ ክፍሉ ሳይሰራ ቀረ፡፡ ጀልባዋ ብዙ ጊዜ ከባህሩ ውስጥ እናያት ነበር፡፡ ጀልባዋን የሚያንቀሳቅሰው ሁለቱ መንኰራኵር በጣም ትልቅ ስለነበር ወደ ውሃው ውስጥ ጠልቆ እንዲገባ ለማድረግ በመቶ የሚቆጠር ሰው ያስፈልግ ነበር፡፡ በዚሁ ጀልባ ስራ መንፈሳቸው በጣም ተመስጦ ስለነበር ጊዜአቸውን በሙሉ ለዚሁ ተግባር ስላዋሉት ከሰፈፈራቸው አራት ማይልስ እርቆ ከሚገኝ ስፍራ ላይ ኃይለኛ ጠላት ተነስቶ ሳይሰሙ ቆይተዋል፡፡››

የበዕውቀቱ አፄውን የማሣነስ ድምዳሜው ከተግባራቸው እስከ ሞራል አቋማቸው ድረስ የዘመተ ነበር፡፡ እንዲህ ብሏል ‹‹እውነት ለመናገር አጤ ቴዎድሮስ በዘመናቸው ከነበሩ ወደረኞቻቸው ጋር ሲመዛዘኑ በሞራል እጅግ ኂላቀር ነበሩ፡፡›› በዕውቀቱ ለዚህ ድምዳሜው አስረጅ ያቀረበው የአፄውን ፀሐፊ ትዕዛዝ የአለቃ ዘነብን ምስክርነት ነው፡፡ የማሳነስ ችግሩ ለሚያተልቅ ማስረጃ ቀልቡን አለመስጠቱ ነው እንጂ እዚያው መጽሐፍ ውስጥ አለቃ ዘነብ ስለአፄው እንዲህ ይላል፡-

‹‹ይህንን ክፋት ባየ ጊዜ እግዚአብሔር በሀበሻ ላይ ንጉሥ ቴዎድሮስን አስነሳ፡፡ ምንዝር የማይወድ፡፡ ገንዘብ፣ ሐሰት፣ ስርቆት የማይወድ፡፡ ሽፍጥንም ሁሉ የማይወድ፡፡ እግዚአብሔርን የፈራ፡፡ እጅግ የሚሰጥ፡፡ እንግዳ የወደደ ለታመመ የሚያዝን በአንዲት ሴት የቆረበ፡፡›› በዕውቀቱ የጠቀሰው በእርግጠኝነት ከታመነ ይሄም የማይታመንበት ነገር አይታየኝም፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ያከናወኗቸው የጭካኔ ተግባራት በዕውቀቱ እንዳደረገው በሌጣው የሚታዩ አይደሉም፡፡ ከህዝቡና ከከባቢ ሁኔታው ጋር ተገናዛቢ እንጂ፡፡ ይሄንን አስልተው የተደላደለ አቋም ላይ ለማረፍ የሞከሩ መርዕድ ወልደ አረጋይ የተሰኙ የታሪክ ምሁር ናቸው፡፡ ‹‹የቴዎድሮስ ዓላማዎች ከየት እንደመነጨ›› በተሰኘ ጥናታቸው እንዲህ ይላሉ፡-

‹‹ቴዎድሮስ ከልጅነታቸው ጀምሮ በሰዎች ተወዳጅነትን ወይም መጠላትን ካፈሩላቸው ጠባዮች መካከል ሐቀኝነታቸውና ታማኝነታቸው ነበሩ፡፡ በረጅሙ የኢትዮጵያ ታሪክ ሒደት ኢትዮጵያውያን እውነት በመናገራቸውና በቃላቸው ፅኑ በመሆናቸው በጐረቤትና በሩቅ ሕዝቦች ታውቀዋል፡፡ ካስራስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን እነዚህ ጠባዮች ለብዙ ኢትዮጵያውያን እንግዶች እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በግራኝ ወረራ አብዛኛው ሰው ጉልቱንና ሕይወቱን፣ እንዳያጣ ፈርቶ ንጉሱን ከድቷል፡፡ ሃይማኖቱን ክዷል፡፡ ከግራኝ ወረራ በኋላም ሰላምና የመንፈስ እረፍት የሚያሳጡ ሁኔታዎች በመፈራረቅ በመነሳታቸው የአድርባይነትና የምቀኝነት ጠባዮች እየጐሉ ሄዱ፡፡ በፊት ኢትዮጵያውያን በሐቀኝነታቸው የታወቁትን ያህል ከዚህ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በወላዋይነታቸውና አጠራጣሪነታቸው ዝናን አተረፉ፡፡ ይህን የጠባይ ለውጥ ያስመጡ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የኑሮ አስተማማኝ አለመሆን ሲሆን ቴዎድሮስ እነዚህን ገና ሳያሻሽሉ የአስተያየት ለውጥ ማምጣትን አስቀደሙ፡፡››

አፄ ቴዎድሮስ የቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን የሞራልም ሥልጣኔ አባታችን ነበሩ የምንላቸው ለዚህ ነው፡፡ እንኳን አፄ ቴዎድሮስን ያህል ግዙፍ አምድ ለመገርሰስ ቀርቶ የመንደር ግራዋም ለመቁረጥ ምክንያትና-ጉልበት፣ ልምምድና ጥናት ሊኖር ግድ አይልም-በዕውቀቱ?

## ኪነጥበብ

# ታዳጊ የሚሻው ቴአትር ፬

ውድ አንባቢያን ሆይ

በዚህ አምድ ላይ ይህን ርእስ አስቀድሜ መጻፌ የሚታወስ ነው። ታዳጊ የሚሻውን ቴአትራችንን መንግስት ምሁራን ውዴታው ያላቸው የጥበብ ሰዎች እንዴት እያስኬዱት እንደሆነ በወፍ በረር ለመቃኘት ሞከርኩ። ይህን ቅኝቴን ያልወደዱት ቴአትርን ‹‹ተምረናል›› የሚሉት አንዳንዶች ማጉረምረማቸው አልቀረም። ጉርምርምታዎች ስለምን ተሰሙ? መግባባትም እንችል ዘንድ ያነሳኟቸውን እና ያላነሳኟቸውን በብርቱ እንይ። መነጋገራችን ካልቀረ ‹‹ቴአትራችን›› አሁንም ታዳጊውን የሚሻ ነውና!!

አሁንም ጥበብ

ጥበብ ለስልጣኔ መገለጫ ለሰለጠነ ህዝብም መታያ መሆኗን ማን ይክዳል? የሚሰለጥን ህዝብ ጥበብን ይጠቀማል። የሰለጠነ ህዝብ ጥበብን ያጣጥማል። ጥበብ የሰውን ልጅ አእምሮ ታመጥቃለች። በሃሴት ባህር ታጥለቀልቃለች። መብላት መጠጣት መተኛት እና መነሳት ብቻ ምኞት ሊሆኑ አይችሉም። ብቻቸውን የእስር ቤት ህይወት ናቸው። ይህንን ክቡድ መንፈስ ማባረር የሚቻለው በጥበብ ነው። ጥበብ ሊባል የሚገባውን ሁሉ በቀላል እና በመልካም ዘዴ መግለጽ መቻል ነው። ያለ ንዝንዝ ያለ ንትርክ ያለ ፕሮፓጋንዳ!!

ጥበብ ራሱን ችሎ ሳይንስ ነው። ራሱን የቻለ ፍልስፍና አለው። ከየት ተነስቶ ከማን መንጭቶ ለማን ይሄዳል? ለማንስ ይሰጣል? ይህን ማየት ማወቅም ጽድቅ ነው። የሰው ልጆች የፈጠራ እና የነጻነት መገለጫ በሆነው ጥበብ ላይ እጅን መክተት ደግሞ ሃጢአት ነው። ለዚያውም ህዝቡን ጨቁኖ የሚገዛበትን እጅ፤ ንጹሃን እንዳይናገሩ የታፈኑበትን እጅ፤ ሙስና ውስጥ ገብቶ የሚፈተፍትን እጅ፤ ከኔወዲያ ሃሳብ ለዚች ሀገር አይጠቅምም ብሎ ለመፈከር የተጨበጠን እጅ ጥበብ ውስጥ አስገብቶ መነካካት ከባድ ሃጢአት ነው።

የጅልነት እሳቤን ፤ የስግብግብነት ምኞትን፤ ያላዋቂ ስሜትን፤ ያላዋቂ መሪነትን፤ ያለርህራሄ ገዥነትን፤ ያለትምህርት መምህርነትን፤ ያለፍላጎት ተፈላጊነትን፤ ያለልማት አልሚነትን፤ ያለስልጣኔ አሰልጣኝነትን ይመስክሩልን ብሎ የጥበብ ሰዎችን አንቆ አስጨንቆ መያዝ ከባድ ሃጢአት ነው። ዳሩ ይህን የምንለው ከጨቋኞች ኅሊና ያለው ካለ ነው።

ጥበብ ከሁሉም ትበልጣለች። ጥበብ በብዙ መንገዷ ትገለጣለች። ቴአትር ጥበብ ነው። ቴአትር በባህርይው የጥበባት ውህድ ነው። በዘመናዊ ቴአትር ውስጥ ፈልገን የምናጣው የስነ-ጥበብ ዘርፍ የለም። ስዕል ሙዚቃ ዳንስ ውዝዋዜ ግጥም ወዘተ. በዚሁ የጥበብ ዘርፍ ውስጥ ይገኛሉ። ለዚህም ይመስላል ጥበቡ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ አቀንቃኞች ዕይታ ውስጥ የወደቀው። ለዚህ ይመስላል በከባድ ቁጥጥርና ፈተና ውስጥ የሆነው። ለዚህ ይመስላል ተንከባካቢ እና አሳቢ አጥቶ የመነጋርያ አጀንዳ የሆነው።

የቴአትር ጥበብ ስልጣኔን ያበስራል አለዚያም የሰለጠነ አእምሮ መገለጫ ነው ስንል የፖለቲካ ፍጆታ ማራመጃ ጠመኔና ሰሌዳ ነው ማለታችን አይደለም። የነጻነት፤ የፍልስፍና፤ የእውቀት ሜዳ ነው ማለታችን እንጅ። ጥበብ መተንፈሻ ነው፤ መተንፈስ ደግሞ ነጻ እንዲሆን ግድ ነው። የሚበላው አጥቶ የሚቀይረው ልብስ ተቸግሮ የሚናገርበት ጥበብ ተጨቁኖበት ዜጋ እውን በዴሞክራሲያዊት ሀገር ነኝ ይላልን?

አሁንም ጥበቡ ሊታሰብለት ይገባል። አሁንም ጥበቡ ነጻ ሊተው ይገባል። አሁንም ጠቢቡ የእውነት ጥበበኛ መሆኑን ማሳየት ይገባዋል። አሁንም መጠበቢያ ስፍራዎች በርካታ ሊሆኑ ያስፈልጋል። አሁንም ጥበብ አፍቃሪያን የልባቸውን ሊያገኙ ያሻል። አሁንም ጥበቡ ታዳጊውን ይሻል።

ህዝቡ

ባለመብት ነው። የትም መቼም በቴአትር ጥበብ እንዲዝናና እንዲማርም መብቱ ነው። የሰለጠነ ህዝብ ጥበብን ይጠቀማል። ጥበብም የሰለጠነ ህዝብን ታፈራለች። ለኪነጥበብ ልዩ ቦታ ያላቸው ሰዎች ለብልጽግናና ለአዳዲስ እሳቤ ቅርብ ናቸው።

ህዝብ ልቡ የፈቀደውን መስራት መብት እንዳለው ሁሉ በንጹህ ጥበብ የመዝናናት መብትም አለው። አንዳንድ ሰዎች ቴአትር ስለኮብልስቶን አለዚያም ስለልማታዊ መንግስት ቢሰብክ ሃጢአት የለውም ይላሉ። እርግጥ ሃጠአት ላይሆን ይችላል። ሃጢአት የማይሆነው ግን ህዝቡ ሊዝናና በመጣበት ሰዓት እና መድረክ ላይ ይህን ሰበካ ሳያካሂድ ሲቀር ነው። ገንዘቡን ከፍሎ ሰዓቱን ሰውቶ ተዝናንቶ ለመሄድ የመጣን ህዝብ ዕለት ዕለት በኢቲቪ አንድና ሁለት እጅ እጅ እስኪለን የሚሰበኩ ፕሮፓጋንዳዎችን እንካ ተቋደስ ማለት የሃጢአት ሁሉ ሃጢአት ነው። ሃጢአቱ ደግሞ በአብዮዊ ዴሞክራሲ መራሹ መንግስታችን አዝማችነት እና የጥበቡ ባለቤት ነኝ ባይ በሆኑ ሰዎች ዘማችነት ይካሄዳል ማለት ነው።

በመሰረቱም ትልቁ ምስቅልቅል የተፈጠረው ቴአትርን ለልማት መጠቀም እና ልማታዊ ቴአትር የተባሉ ሁለት የማይገናኙ ጽንሰ ሐሳቦች ሲደበላቁ ነው። ተምሬአለሁ የሚል የቴአትር ባለሙያ ‹‹ልማታዊ ቴአትር›› የሚል ስልት /ኢዝም / ወይም ዘውግ /ዣነር/ ስለመኖሩ ይመሰክራል የሚል እምነት የለኝም። ታዲያ ይህ ፍልስፍና ከወዴት ነው የመነጨው? ከፖለቲከኞች መሆኑን እያወቅን የቴአትር ተመልካቹን ስለልማታዊ መንግስት መስበክ ሃጢአት አይደለም የሚባለው እንዴት ሆኖ ነው?

ይመስለኛል ህዝቡ ተንቋል። ተጨቁኗል፤ ተረግጧል፤ የትም አይሄድም፤ ምንም አያመጣም፤ በሚል የጨቋኞች ፍልስፍና እንጅ ‹‹ልማታዊ ቴአትር›› የሚባል ቅዠት ከዘር የመጣ ውርስ አለዚያም ከዘመን የተወረሰ ስልጣኔ አይደለም።

ህዝብ የመማር መብት፤ የማምለክ መብት፤ የመኖር መብት አለህ እንደተባለው ሁሉ / ስለመብቶቹ መከበር አለመከበር ሳንጨቃጨቅ/ የመዝናናት መብት ባህሉን ጥበቡን እሳቤውን የማጎልበት መብት ሊከበርለት ይገባል። የውሃ ማቆርያ ጉድጓድ /የወባ ትንኝ እርባታ ጣቢያ/ ማቋቋም ብቻ ለህዝብ አሳቢነትን አይገልጽም።

የኪነጥበብ ባለሙያዎች በነጻነት የህዝብ አገልጋዮች እንዲሆኑ ማስቻል እና የኪነጥበብ ማሳያ ቦታዎችን ማስፋፋት ግዴታ ቢሆን እንጅ የመንግስት መብት ሊሆን አይችልም ።

ከሚዳብር ባህልና ኪነጥበባዊ እሳቤ እንጅ ወረቀት ላይ ከሚደረደር ፖሊሲ ህዝብ ስልጣን አያገኝም። ኪነጥበባዊ ብልጽግና እንጅ ከአንድ ለአምስት አደረጃጀት ጠብ የሚል ብልጽግና የለም።

አሁንም ባለሙያ

አሁንም ባለሙያ እንፈልጋለን። ጥበቡን የሚረዳ መብቱን የሚያስከብር ጥራዝ ነጠቅ ሳይሆን ጠሊቅ እውቀት ያለው የቴአትር ባለሙያ የዚችን ሀገር ቴአትር ለመታደግ አስፈላጊ ነው። ባለፈው እንዳልኩት ልማታዊ ቴአትር በል ሲባል የሚል ስለልማታዊ መንግስት ስበክ ሲባል አበባ እና ቁጤማ ይዞ ድምጹ እስኪዘጋ መፈክር የመሰለ ቃለ ተውኔት የሚለፈልፍ ሳይሆን ጥበቡን ጥበብ ብሎ ሳይንሱን ተረድቶ የሚሠራ ባለሙያ እንፈልጋለን።

ለመሆኑ ይህ ክፍተት የተፈጠረው ለምን ይሆን? የዲግሪ እጥረት ኖሮ ነውን? አይመስለኝም። ባለፈው ሳምንት እንዳልኩት ላለፉት ሰላሳ አመታት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብዙ ምሩቃንን የቴአትር ዲግሪ እያስያዘ ሸኝቷል። ከተመረቁት ስንቱ ሰሩ፣ ከተመረቁት ስንቱ በተማሩበት ኖሩ፣ ከተመረቁት ስንቱ የተማሩትን ሙያ ያውቁታል፣ ከተመረቁት ስንቱ ለውጥ ፈጣሪዎች ናቸው፣ ከተመረቁት ስንቱ የምላስ ሳይሆን የጭንቅላት እውቀት አዳብረዋል፣ ከተመረቁት ስንቱ ጥበቡን አስፋፍተዋል፣ ከተመረቁት ስንቱ ከተጠናወተን ዘልማዳዊነት የጥበብ አስተሳሰብ ሊያላቅቁን ቆርጠዋል ከተመረቁት ……?

በሀገራችን የቴአትር ጥበብ ውስጥ የዋሻ ያህል የተበረቀሰውን ክፍተት ማጥበብ ያልቻሉት ዳዴ የሚለውን የቴአትር ጉዞ ማስሮጥ ያልቻሉት የፖለቲከኞችን ጣልቃ ገብነት አስቀርቶ ጥበቡን መታደግ ያልቻሉት ስለምንድን ነው? በእርግጥ ይህ ጥያቄ በተደጋጋሚ ይነሳል። ዩኒቨርሲቲው በዘመኑ ካስመረቃቸው መካከል ጥቂቱ ብቻ ናቸው በቴአትር ጥበብ ውስጥ ያሉት ።ካሉትም ጉልህ ድርሻ ያላቸው ጥቂቱ ናቸው። ይሕ የሆነው መጀመርያውኑ ያለፍላጎታቸው ስለሚማሩ ነው ይባላል። ምክንያቱ ሊያሳምን ቢችልም ዩኒቨርሲቲው ግን ይህንን ችግር ተንትኖ አጥንቶ መርምሮ መፍትሄ የሰጠው አይመስለኝም። የሰዎችን ስራ ለመተቸት የምላስ ብቻ ትንታኔ ለመስጠት የማይሰንፉ ባለሙያዎችን አይደለም ለሃገሪቱ የቴአትር ጥበብ ብልጽግና አቅም መሆን የሚችሉትን ብቻ እንፈልጋለን።

አሁንም መንግስት

አዎ አሁንም መንግስት እንፈልጋለን። ጥበቡን የሚታደግ ሀቀኛ መንግስት እንፈልጋለን። ለጥበብ ቅድሚያ መስጠት ስራ ፈትነት ነው ብሎ የማያምን የጥበቡ ታዳሚዎችን በግል አጀንዳው የማያደነቁር በየቀበሌው አረቂ መሸጫ ሳይሆን የጥበባት ማዕከል የሚያስፋፋ መንግስት ያስፈልጋል።

ስልጣኑን የያዘው መንግስት የጥበብን ጥቅም አያውቀውም ማለት ያስቸግራል። ታጋዩንና ሰራዊቱን በጥበብ ትሩፋቶች እያነቃቃ ለስልጣን እንደበቃ የሚታመን ነው። ከዚያ በኋላ ግን አንዳችም እንኳ አለማድረጉ ያሳዝናል።

ሁለት መንግስታትን የተሻገሩ ሦስት ቴአትር ቤቶችን ይዞ ሀገሪቱ የባህልና የኪነጥበብ ፖሊሲ አላት የሚያስተባብርም የባህል ሚንስቴር አለ ማለት ይከብዳል። ተዝቆ የማያልቅ የባህል ጸጋ አላት በምትባል ሀገር ጥንታዊያን የቴአትር ህንጻዎችን ይዞ መቀመጥ አያስደስትም።

በየጊዜው ስለፖሊሲ መቀያየር ስለስትራቴጂ ለውጥ ስለሲምፖዚየም መዘጋጀት ሲወራ እንሰማለን። አይጥ የሚዘልበት የጣውላ መድረክ መቀየር ግን አልተቻለም። ቢያንስ በከተማ ላሉ ሚሊዮን ዜጎች የሚሆኑ ቴአትሮች አልተገነቡም። በሦስት ከተሞች የተሰሩ የሰማእታት መታሰቢያ አዳራሾች እንኳ ብዙ ጊዜ የስብስባ እንጅ የጥበብ አዳራሽ አልሆኑም። እና ብዙ ብዙ ……. ፣ከነዚህ ሁሉ ድክመቶች ነጻ የሚያወጣ መንግስት ያስፈልጋል። ቴአትርን እንዲህ መታደግ ይቻል ይሆናል።

## የወጣቱ የፖለቲካ … ከገፅ 9 የዞረ

ምድርም ላይ የሚሳተፉና ሀሳብ የሚያዋጡ ወጣቶች እንዳይፈጠሩ ምክንያት ሆኗል።

እየተተገበረ ያለው አዲሱ የ70/30 ፖሊሲም የፖለቲካውን መስክ የበለጠ ምድረ በዳ የሚያደርግ ይመስላል። ዩኒቨርስቲ ከሚገቡ ተማሪዎች 70 በመቶዎቹን የተፈጥሮ ሳይንስ ተማሪ በማድረግ 30 በመቶዎቹን ብቻ የሶሻል ሳይንስ ተማሪ ማድረግ፣ የመብት ጥያቄዎችን በማንሳትና የፖለቲካ ተሳትፎ በማድረግ የሚታወቁትን የሶሻል ሳይንስ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስና የፖለቲካ ፍዘቱን ለማጠናከር እንደሆነ የሚገልፁ የፖለቲካ ተንታኞች አሉ። ይህም ፖለቲካውን የበለጠ የሚያፈዘው ይሆናል።

### ወጣቱ የት ነው?

የዘመኑ ወጣት ያለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሳይሆን ዲስቲቪ ቤቶች ውስጥ ነው። ከምርጫ 97 ወዲህ ወጣቱ በከፍተኛ ደረጃ ወደ እግር ኳስ ፈልሷል። እግር ኳስን መሸሸጊያ ምሽግ ያደረገውም ይመስላል። የፕሪምየር ሊግ ጫወታዎች እንደሀገራዊ አጀንዳዎች ዋና የትኩረት ማዕከል ሆነው ቀልብን ስበዋል። እንደትልቅ ርዕስ ጉዳዮችም የመወያያና የመከራከሪያ ጭብጦች ሆነዋል። የመገናኛ ብዙሃን ነጋ ጠባ የሚያወሩት ስለውጪ ክለቦች ግጥሚያና ስለተጫዋቾቹ የአደባባይና የጓዳ ታሪክ ነው። ስለሀገሩ ጉዳይ አንድ ዐረፍተ ነገር የማይተነፍስ ጋዜጠኛ (እሱም ያው ወጣት ነው) የተጫዋቾቹንና የአሰልጣኞቹን የጀርባ ታሪክና ምስጢር በጥልቀት ይተነትናል። ሀገራዊ ፋይዳው ምን እንደሆነ ማሰብ የለም። ጠቀሜታው ምን ያህል ነው ብሎ መጠየቅ የለም። ዝም ብሎ ማነብነብ ብቻ።

በሚዲያዎች አራጋቢነት ታግዞ ወጣቱ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግን ከፖለቲካ ፍትጊያ ማምለጫ ዋሻ አድርጐታል ማለት ይቻላል።

ሌላው ወጣቱ የሚገኝበት ስፍራ ሺሻ ቤት ነው። ጫት፣ ሲጋራ፣ ሺሻ፣ ሀሽሽ ወጣቱን የተቆጣጠሩ ሱሶች ናቸው። ሱስ እንኳን ለሀገራዊ ጉዳዮች ለራስም ትኩረት እንዳይኖር ያደርጋል። ለሁሉም ነገር ደንታ ቢስ መሆንና ችላ ማለት የሱሰኞች መገለጫዎች ናቸው።

ይህ ትውልድ የሱስ ሰለባ መሆኑ ለፖለቲካ ፍዘቱ አንድ አስተዋፅኦ አበርክቷል ማለት የሚቻል ይመስላል።

ይህ ሁሉ የሚነግረን አንድ ነገር ነው። ወጣቱ ትውልድ ፖለቲካን በሩቁ ብሎ በእግር ኳስና በሱስ ውስጥ ራሱን ደብቋል የሚል እውነት።

### ምን ይሁን?

የፖለቲካ ፍዘት ሲበዛ ብሔራዊ ክትረትን ያስከትላል። ይህ አሳሳቢ ነው። ነገር ግን ሁኔታዎች ከተመቻቹ ፍዘቱ ሊሰበር እንደሚችል በምርጫ 97 ወቅት አይተናል። ስለዚህ ምንም እድሉ የጠበበና አስቸጋሪ ቢመስልም ከፖለቲካ ፍዘት የመላቀቅ ተስፋ አለ።

አደጋ በሌለበት ሁኔታ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ የሚቻልበት፣ ዴሞክራሲያዊ መብትን ያለፍርሃትና ስጋት የመተግበር እድል የሚመቻችበት፣ ሁኔታ ካለ ፖለቲካዊ መነቃቃት ሊፈጠር ይችላል። ይህ ግን የሚሆን ካለመምሰሉም በላይ በኢህአዴግ በጐ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ነው። እንዲሁም በኢህአዴግ ተመን ልክ የተቀነበበ ንቃት መፍጠር ላይ የተወሰነ ይሆናል።

ከዚህ ይልቅ ጠባብ የሚመስሉ እድሎችን ማስፋት ላይ ማተኮር አግባብ ይመስላል። የተዘጉ በሮችን ለማስከፈት መታገልና የተዘጉ የሚመስሉ ግን ገርበብ ያሉ በሮችን ከፍቶ መግባትና በሮቹን ማስፋታ ላይ መትጋት ከፖለቲካ መሪዎች የሚጠበቅ ነው።

ከፊት የሚቀድምና መስዋዕት ሊሆን የተሰናዳ ቆራጥና ደፋር መሪ ማግኘት ግድ ነው። ወጣቱ የተሻለ አማራጭ የሚያሳዩትንና መምራት የሚችሉ መሪዎችን ካገኘ መነቃቃት እንደሚጀምር በምርጫ 97 ያየነው ስለሆነ የመሪዎቹ ብቃት ጉዳይ ወሳኝ ይመስላል።

የወጣቱን የፖለቲካ ፍዘት ቅኝት ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ‹‹የኢትዮጵያ ወጣቶችና አገዛዝ›› በተሰኘ ፅሁፋቸው ላይ ያሉትን በመጥቀስ እንደምድም።

‹‹የመብት ጥያቄ ሰው የመሆን ጥያቄ ነው፤ ሰው የመሆን ጥያቄ ሁለት ዋና ነጥቦች አሉት፤ አንደኛ፣ እያንዳንዱ ሰው ራሱ ሰው መሆኑን ተገንዝቦ በሚኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን መብትና ግዴታ ማወቅ አለበት። ሁለተኛው ግፍን፣ በደልን፣ ጥቃትን፣ አድልዎንና ሕገ-ወጥነትን አልቀበልም፣ እምቢ የማለት ጠንካራ አቅዋም እንዲኖረው ያስፈልጋል።››

1ኛ ዓመት
መታሰቢያ



ወ/ሮ ዕፀገነት ተክሉ

(ሚያዝያ 15 ቀን 1958 - መጋቢት 13 ቀን 2003 ዓ.ም)
የወ/ሮ ዕፀገነት ተክሉ የ1ኛ ዓመት መታሰቢያ መጋቢት 11 ቀን 2004 ዓ.ም. በገርጂ ደብረገነት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን በፀሎተ ፍትሀትና ነዳያንን በመዘከር ታስቦ ውሏል።
እግዚአብሔር ነፍሷን ከጻድቃንና ሰማዕታት ጋር ያኑራት
ሁሌም የእግር እሳት ነሽ

ባለቤቷ መድኃኒቱ ማሞ

# አብዮታዊነት ከኢትዮጵያዊነት በላይ የመኖር ዋስትና ሆኖ ከተገደድን ሀገራችን የት ነው?



ሀብታሙ አያሌው
(የባለራዕይ ወጣቶች ማህበር አመቻች ኮሚቴ እና የቀድሞ የአ.አ ወጣቶች ፌዴሬሽን እና ፎረም ፕሬዝዳንት)
visionaryyouth@gmail.com

…መቼም የአብዮታዊነት ዳራ አብሮን የተወለደ ይመስል በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ተጣብቆ ለዘመናት እየታገለን ነው:: ዛሬም የደርግን ዘመን ከተሻገርነው ሀያ ዓመታት አስቆጥረን እንኳ ሌላኛው የአብዮት ገፅታ ከኢትዮጵያዊነታችን በላይ ግዳጅ ሆኗል:: ሀሳብህን በነፃነት ለመግለጽ፤ ተምረህ ስራ ለመቀጠር መብትህን ጠይቀህ ለማግኘት፤ የአብዮታዊው ስርዓት ተከታይ መሆን ዋነኛ መመዘኛ ሆኖአል:: አርቲስት ከሆንክ ልማታዊ አርቲስት፣ ነጋዴ ከሆንክ ልማታዊ ነጋዴ፤ ካህን ወይም ሼክ ከሆንክም ልማታዊ ሼክ ወይም ካህን መሆን ይጠበቅብሃል፤ ከዚህም በላይ ኩርማን መሬትህን የምታርስ ገበሬ ብትሆንም እንኳ ልማታዊ ገበሬ ካልተባልክ በኢትዮጵያዊነትህ ብቻ ኢትዮጵያዊ ተብለህ መኖር ፈተናው ብዙ ሆኖአል:: እርግጥ ነው አብዮታዊ እና ልማታዊ ያልሆነ ይህ ይደርስበታል ተብሎ የተፃፈ ድንጋጌ የለም ይሁን እንጂ የእጅ አዙር ስትራቴጂው ግን ከየት በኩል እንደተወረወረ ሳታውቀው አንገትህ ውስጥ እየጠለቀ ይጎትትሃል:: ዛሬ ዛሬ የአብዮታዊው ስርዓት ተከታይ እስካልሆንክ በኢትዮጵያዊነህ ብቻ ልበ ሙሉ መሆን የማይታሰብ ሆኖአል::

ማንኛውም ዜጋ ባመነበት ጉዳይ ላይ ብቻ ሊሳተፍ ይገባል እንጂ ባላመነበት ጉዳይ ገብቶ እንዲዳክር መገደድ የለበትም በተለይ የዴሞክራሲ ስርዓትን መከተል በመርህ ደረጃም ቢሆን በመረጠ ሀገር ውስጥ ዜጎች ከአንድ ፈርጣማ ፓርቲ የተለየ አስተሳሰብ ይዘው በመጡ ቁጥር መሰደድ የለባቸውም:: የሃሳብ ነፃነት የሌለው ያመነበትን መናገር የወደደውን መፃፍ፣ የመረጠውን መደገፍ፤ የጠላውን መቃወም የማይችል ሰው በህይወት መኖሩ ብቻ ምን ትርጉም አለው:: ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሰው በመሆናችን ብቻ ከፈጣሪ በጸጋ ስጦታ ያገኘናቸው ሀብታት ናቸው:: እነዚህን የፀጋ ስጦታ በማንኛውም ሌላ ኃይል የተነጠቀ ሰው ከነዚህ መብቶች ውጪ መኖር ለህይወቱ ትርጉም ስለማይሰጠው ሁል ጊዜም ነፃነት የሚያገኝበትን መንገድ ሲፈልግ መኖሩ የማይቀር ነው::

ዛሬ ዛሬ የአብዮቱ አዙሪት እየከረረ በመምጣቱ ዜጎች ስርዓቱን የሚተች ጋዜጣ እያነበቡ መገኘት እንኳን እንደወንጀል ቆጥረው እንዲሸማቀቁ አድርጓቸዋል:: ስርዓቱ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ህጻን አብዮታዊ ዴሞክራሲን እስኪዘምር እንዲዘልቅ የታቀደ ይመስላል:: የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዓት ስልጠና ልማታዊ አርቲስት፤ ልማታዊ መምህራን፣ ልማታዊ ተማሪ፣ ልማታዊ ሴቶች፣ ልማታዊ ወጣቶች ከሰሞኑ ደግሞ ልማታዊ የጎዳና ተዳዳሪዎች በሚል ቀጥሏል፤ ይህ አይነቱ የፖለቲካ ስርዓት የአንድ አገር ህዝብ ሙሉ በሙሉ የአንድ ፓርቲ አባል እንዲሆን ከማቀድ የሚነሳ በመሆኑ ይህንኑ የፓርቲ ዓላማ ለማሳካት መወሰድ የሚገባው እርምጃ ሁሉ ይወስዳል በመሆኑም ዜጎች ስርዓቱን ሳይከተሉ መኖር እንደማይችሉ እንዲያምኑ ስነ ልቦናዊ ተፅዕኖ የሚያደርግ አደገኛ የፖለቲካ ስትራቴጂ ነው::

አብዮታዊ ዴሞክራሲና መድብለ ፓርቲ

አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከግራ ዘመሙ የሶሻሊዝም ባህር የተቀዳ በመሆኑ ፖለቲካዊ ማንነት የፈጠረለት ማርክሲስታዊ የሌኒን አስተሳሰብ አመክንዮ ፓርቲውን በልጅነት ጥምቀቱ የተቆራኘው በመሆኑ የእምነት ለውጥ አድርጌያለሁ ብሎ የአብዮታዊ እምነት ዶግማ ቀርፆ ርዕዮተ ዓለም ማራመድ ከጀመረ ከ20 ዓመታት በላይ አስቆጥሮ እንኳን ታርጋው ካፒታሊዝም ቢሆንም ከኮሚኒዝም እና ከካፒታሊዝም ከተቀነጫጨበ የፖለቲካ ስርዓት ያልተላቀቀ በመሆኑ ሂደቱ በየጊዜው የሚንገራገጭ እና ቅጥያጣ የፖለቲካ ባህሪ መለዋወጦችን የሚያሳይ ነው::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ በሶሻሊስታዊ ባህሪው ከብዙሃን የማህበረሰብ ትንታኔ የሚነሳ ሲሆን ፓርቲው በጊዜ ብዛት ከዴሞክራሲያዊ ባህሪና ፍላጐቱ እየወጣ አምባገነናዊ ባህሪው እየጎለበተ በመሄዱ እራሱን እያስፋፋ አማራጭ ሀይሎችን ሁሉ በማቀጨጭ ለብቻው ጠቅላይ ገዥ ሆኖ የሚኖር የፈረጠመ ፓርቲ ወደ መሆን ተሸጋግሯል::

ይህ የዛሬው የፓርቲው አላማ ገና በጠዋት ብዙዎች ከፓርቲው ጎን ተሰልፈው ለመታገል ከቆሙለት የህዝቦች የዴሞክራሲ፣ የነፃነትና የእኩልነት ጥያቄ አንፃር ሙሉ በሙሉ መሰረቱን እየለቀቀ እንደሆነ ይስተዋላል:: ፓርቲው የያዘው የፖለቲካ ባህሪ ወይም ባይ እንደሚያሳየው የዴሞክራሲ፣ የነፃነት፣ የእኩልነት፣ ጥያቄና ለዚሁ የህዝብ ጥያቄ የተከፈለውን መስዋዕትነት እንደመወጣጫ ተጠቅመው ስልጣን የተቆናጠጡ አካላት አንድ ጊዜ ተደላድለው የተቀመጡበትን የስልጣን ወንበር ለማስጠበቅ ከቅድመ ታሪክ የፓርቲው ባህሪ ሙሉ በሙሉ በመውጣት አምባገነናዊ ባህሪ እያጎለበቱ በመሆኑ አብዮታዊነት ከኢትዮጵያዊነት በላይ የመኖር ዋስትና እንዲሆን አስገዳጅ ስርዓቶች በህዝብ ልጆች ነፃ ህሊና ላይ እየተጫኑ እንደሆነ ይስተዋላል::

እንዲህ ያለው የፖለቲካ አስተሳሰብ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ሳይሆን አምባገነናዊ የጠቅላይ ገዥነትን የሚያሰፍር በመሆኑ በመርህ ደረጃም ፓርቲው የግል አመኔታዬ ነው በማለት በሰነድ ያሰፈረው የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓት ከይስሙላ ሰነድነት አልፎ ወደ ተግባር መለወጥ እንዳልቻለ ይስተዋላል::

የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓት አለ የሚባለው ይህንን የፖለቲካ አማራጭ የተቀበለ ማንኛውም ሀገር በህግ እንዲደነገግ በማድረግ ብቻ የሚገለፅ የመድብለ ፓርቲ የፖለቲካ ስርዓት ለመኖሩ ማረጋገጫው ለስርዓቱ መስፈን ዋነኛ መሰረት የሆነው የዴሞክራሲ ምህዳር በበቂ ሁኔታ የመኖሩ ጉዳይ ነው:: መስከረም 2001 ዓ.ም. ቅጽ 2 ቁጥር 3 የታተመው አዲስ ራዕይ የኢህአዴግ ልሳን መጽሔት የፓርቲውን የፖለቲካ እምነት በሚተነትን ምዕራፍ ገፅ 9 ላይ 1.2 ከመድብለ ፓርቲ ስርዓትና ከነፃ ማህበራት ውጪ ዴሞክራሲ አይታሰብም በሚለው ንዑስ አንቀጽ ስር እንዲህ ሲል ያትታል

‹‹ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መስመራችን ብዙሃኑን የኢትዮጵያ ህዝቦች በዙሪያው ማሰለፍ የሚያስችል አቅም እንዳለውና በተግባርም እያሳለፈ እንደሆነ ይታወቃል:: ይሁንና መስመራችን የሁሉንም የኢትዮጵያ ዜጐች ጥቅም በእኩልና በተሟላ መልኩ ማስጠበቅ አይችልም:: ልማታዊ መስመር ጥቅማቸውን በላቀ ደረጃ የሚያስጠብቅላቸው ዜጐች የመኖራቸውንም ያህል የኪራይ ሰብሳቢነት መስመር ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅላቸው ዜጐች መኖራቸው አይቀሬ ነው::›› ቅዱስ መጽሐፉ ‹‹በመጨረሻም ዘመን አንባቢው ያስተውል›› እንዲል እንዲሁ አንባቢ እንዲያስተውል እለምናለሁ::ከጽሑፉ እንደምንረዳው ይህ የኢህአዴግ እምነት በቅድሚያ የኢህአዴግን ብዙሀኑን ከጎኑ የማሰለፍ አቅሙን ይገልፃል፤ ዝቅ ሲል አጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ በሁለት ይከፍልና ግማሹን ለልማታዊ አስተሳሰብ የሚጠቀም ግማሹን ደግሞ ለኪራይ ሰብሳቢነት የሚጠቀም ብሎ ይከፍላል::

ሲቀጥል ኢህአዴግ ሁሉንም ህዝብ በአንድ ላይ ተጠቃሚ ማድረግ እንደማይችል አንፃራዊ አቅሙን ያሳያል፤ ከዚህ ሲቀጥል በኪራይ ሰብሳቢነት የሚጠቀምና በልማታዊነት የሚጠቀም ብሎ በሁለት ጎራ የመደበውን የኢትዮጵያ ህዝብ ኪራይ ሰብሳቢ ወይም ልማታዊ የሆነውን የለየበት ባህሪ በእጅጉ የሚያስገርም ነው::…. ‹‹ስለሆነም ሁሉም አማራጮች የሚደመጡበት መድረክ መፍጠር ለልማትና ዴሞክራሲ አማራጭ የሌለው ከሆነ ቢያንስ ሁለቱን ዋንኛ አማራጮች የሚወክሉ ፓርቲዎች መኖራቸው አይቀሬ ነው›› በማለት ሲደመድም በሁለት ጎራ ያሰለፈውን ህዝብ በአሰላለፍ ሲፈርጅ፡- የኢህአዴግን አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚከተል ህዝብ ልማታዊ ከዚህ ውጪ ያለውን ኪራይ ሰብሳቢ በማለት ይደመድማል::

አብዮታዊ ዴሞክራሲ እና ብዙሃን ማህበራት

አዲስ ራዕይ ከላይ በተጠቀሰው እትሙ ገፅ 10-11 ባለው ሐተታ ላይ ስለብዙሃን የነፃ ማህበራት ጉዳይ እንዲህ ይላል:: ‹‹ሴት አርሶ አደሮች የራሳቸው የተለየ መብትና የጥቅም ጥያቄ ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ ይህ መብትም ጥቅምም በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከወንድ አርሶ አደሮች ጋር የሚቃረንበት አጋጣሚ አለ የወጣት አርሶ አደሮች መብትና ጥቅምም ከወላጆች መብትና ጥቅም በከፊል የተለየና አልፎ አልፎ የሚጋጭም ነው:: በሀብታም አርሶ አደሮችና በድሃ አርሶ አደሮች መካከል ልዩነት በተመሳሳይ ሊታይ ይችላል:: ድርጅታችን እነዚህን በጋራ ጥቅም አስተሳስሮ ማሰለፍ ችሏል:: ድርጅታችን እነዚህን በጋራ ጥቅም አስተሳስሮ ማሰለፍ ችሏል:: ይህንን ማድረጉም ተገቢ ነው:: ይሁንና የወጣቶች፣ የሴቶች ወዘተ… መብት በይበልጥ ለማጉላት ከድርጅታችን ባሻገር የወጣቶች፣ ሴቶች፣ መምህራን፣ ሰራተኞች፣ ሀኪሞች ወዘተ…የሙያና የብዙሃን ማህበራት ያስፈልጋሉ….›› በማለት በአብዮታዊው እምነት ዙሪያ የሚያሰልፋቸውን ሰራዊቶች በተመለከተ ያለውን እቅድ እና እምነት ያብራራል::

ከዚህ እምነት የተነሳው ኢህአዴግ ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ ልማታዊ ሴቶች፣ ልማታዊ መምህራን፣ ልማታዊ ሀኪሞች፣ ልማታዊ አርቲስቶች በማለት…. የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ርዕዮት አሰልጥኖ ስርዓተ ጥምቀቱን ፈፅሟል:: በ2001 ዓ.ም. ክቡር ጠቅላይ ሚኒስቴር ከወጣቶች ጋር ያደረጉትን ውይይት ይዞ በኢፌዴሪ ወጣቶችና ስፖርት ሚኒስትር መስሪያ ቤት በታተመው መጽሔት ገጽ 19 ላይ ጠቅላይ ሚኒስቴር የነፃ ማህበራትን አስመልክተው ሲናገሩ ‹‹መንግስት ማህበራት እንዲጠነክሩ፤ እንዲስፋፉ፣ ማበረታታት እና መደገፍ እንዳለበት እናምናለን ነገር ግን ማህበራቱ ደግሞ ነፃነታቸውን ጠብቀው ማህበረሰቡ የኔ አደረጃጀቶች ናቸው ብሎ እንደእድር እና እንደ እንቁብ የሚጠብቃቸው ማህበራት ሊሆኑ ይገባል፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ማህበራቱ በመንግስት በጀት የሚንቀሳቀሱ ከሆነ ዞሮዞሮ ተጠሪነታቸው ለመንግስት በመሆኑ በዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታው ላይ ምንም ፋይዳ አይኖራቸውም›› በማለት ነበር ለወጣቱ የመከሩት:: ታዲያ ዛሬ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ካድሬዎች የሚያስፈፅሙት የማንን እምነት ነው? በነፃ ማህበራት ስም ተደራጅቷል እየተባለ ሙሉ በሙሉ በመንግስት በጀት የሚንቀሳቀሰው የአዲስ አበባ ወጣቶች ፎረም እራሱን ችሎ እንዲቀንስ የነፃ ተቋምነት ህልውናው ይጠብቅ በማለታችን ስንቶቻችን የካድሬዎችን እርግማን ተሸከምን፤ ነፃ ተቋም ያስፈልጋል በማለት በቅርቡ ወደ ተቋቋመው ባለራዕይ ወጣቶ ማህበር የገቡ ወጣቶችስ ከፎረሚ፤ ከማህበር ወዘተ…. አባልነታቸው እንዲባረሩ በይፋ በጉባኤ መመሪያ የሰጡ ካድሬዎችስ እውነት የአብዮታዊ ዴሞክራሲን ተልዕኮ እይፈፀሙ ነው? የዴሞክራሲ ሀሁ… ገብቷቸዋል? ወጣቱስ የሀሳብ ልዩነት በመያዙ እንዲሳደድ እንዲሸማቀቅና ባላመነበት እንዲጓዝ ሊገደድ ይገባልን? ዴሞክራሲ የታለ?

የአብዮቱ ተጽኖ በመላው ህዝብ ላይ

የፓርቲው እምነትና ባህሪ ሁሉም ህዝብ በመልክ በገጽ እና በአምሳል እሱን እንዲመስሉ በማለም የነበረውን ውስጥ ዴሞክራሲ ባህሪ አሟጥጦ በማጥፋት በአላማው ዙርያ አሳምኖ ማህበረሰቡን የማሰለፍ ባህሪውን በመተው በተጽኖ አስገዳጅ ስልቶችን በመዘርጋት የሚያምኑበትን ተከታዮች በዙርያው ወደሚያሰባስብበት ስርዓት ተሸጋግሯል::

በዩኒቨርስቲ ያሉ ተማሪዎች በብሔር ፖለቲካው ጽንፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ተከስቶ የማያውቅ በቡድን የብሔር ግጭት እዚም እዛም በስፋት ተከስቶ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል::ኢህአዴግ የብሄር ፖለቲካው ቀውስ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እየፈጠረ ያለውን የፖለቲካ ትኩሳት ለማብረድ የተከተለው ዋነኛ ስትራቴጂም ከመሰረቱ ችግሩን በማናት የተወሰደ እርምጃ ሳይሆን ለፖለቲካ ትርፍ ብቻ የተማሪዎችን የኢኮኖሚ አውታር መቆጣጠሪያ በእጁ በማድረግ ተማሪዎች ተመርቀው ሲወጡ ስራ የማግኘት እድላቸው በፓርቲ አባልነት እንዲወሰንና ድህረ ምረቃ ስራ የማግኘት እድል በሞያ፣ በክህሎት ሳይሆን የአብዮታዊነት መመዘኛ ቀዳሚ በማድረግ በግብር ፓርቲውን ባይመስሉም እንኳን የፓርቲ አባልነት ፎርም ሞልቶ መታወቂያ መያዝ እንደዋስትና እንዲቆጠር የሚያደርግ ሁኔታ በመፍጠሩ ለጊዜው የብዙሃኑን ጥያቄ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የኢኮኖሚ ተፅዕኖ ፈጣሪነት መድበስበስ ችሏል::

የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ሙያተኞች በእውቀትና በክህሎት ደረጃ እየተመዘኑ የሚመደቡበት እንደታላቋ አሜሪካ እና ምዕራባዊያን ያሉ ሀገራት መንግስት በተቀያየረ ቁጥር ሲቪል ተቋማቱ የመጣው አመራር የፖለቲካ ስልጣኑን ይዞ የሚመራበትን እድል እየሰጡ የሚቀጥሉበት ነው:: የኛ ግን አብዮታዊያን እና የልማት ሰራዊት የሚል ስያሜ የሚሰጣቸው የገገር መደቡን ርዕዮተ-ዓለም የሚያቀነቅኑትን በማከማቸት የማይቀያየር ዘለዓለማዊ የስልጣን አላማ ያለውን ፓርቲ እንዲያስተናግድ የተመቻቸ በመሆኑ በስልጣን ቆይታ እንጂ በሀገር ግንባታ ረገድ ብዙ ፋይዳ አለው ማለት አይቻልም:: በጥቅሉ እንዲህ ያለው የኢህአዴግ የፖለቲካ ስትራቴጂ መልኩ ካልተቀየረ እና ዴሞክራሲና ነፃነት የህዝብ ልጆች ከዛሬ አብዮተኞች በችሮታ የሚለምኑት መሆኑ ካልቀረ አንድ ሉአላዊ ሀገር መገንባት ፈፅሞ የማይታለም ነው:: ኢትዮጵያ በደቡብ አፍሪካዊው ማንዴላዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ አብሮነት እውን የሚሆንበት ብሔራዊ እርቅ ተደርጎ ስልጣን በህዝቦች ውሳኔ ብቻ የሚከበርበት ዜጐች ሳይፈሩና ሳይሸማቀቁ ነፃ አስተሳሰባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁባት ሀገር ልትሆን ይገባል::

ኢትዮጵያዊ የአብዮታዊው ርዕዮተ አለም አራማጆች ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች የጋራ መኖሪያና መከበሪያ መሆኑዋ በተግባር እስካልተረጋገጠ ድረስ የባለስልጣኑን እድሜ ለማስረዘም ልዩነታችን ብቻ እየከረረ ከተጠመዘዘ የኢትዮጵያዊ አንድነት ግንባታውም ለፖለቲካ ትርፍ በተፈለገ ጊዜ ብቻ አጀንዳ ከሆነ እንዴት እንደ የበለፀገ ሀገር ሊፈጠር ይችላል?

የህዝቦች ሰላማዊ የትግል መስመር ሙሉ በሙሉ እስካልተዘጋ ድረስ ፍፁም ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተጠናከረ ትግል ማድረግ ይገባል::

የሰላማዊ ትግሉ ስኬት ግን በዜጐች ለሀገር ታማኝነት የሚለካ ነው፤ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፋት ከፖለቲካ ፓርቲዎች በላይ ዜጎች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው:: ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲዳብር የዜጐች መብት እንዲጠበቅ ቀልጣፋ የፍትህ ስርዓት እንዲኖር ሙሰኞች በሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድል እንዳይኖራቸው በምርጫ የህዝብ ድምጽ እንዲከበርና የማጭበርበሪያ መንገዶች እንዲዘጉ ማድረግ እንዲሁም ዜጐች እንደራሳቸውን ጥላ ከሚከተላቸው ፍርሃት ወጥተው የተሳሳተውን ተሳስቷል ትክክል የሆነውን ትክክል ነው ማለት የሚችሉበት የትግል መድረክ መፈጠር አለበት:: ዜጐች ለሀገርና ለህዝብ ጥቅም ቅድሚያ ሰጥተው ሰላማዊ በሆነ እና በተደራጀ ሁኔታ መታገል ሲጀምሩ ያን ጊዜ ለታላቋ አሜሪካ እና ለምዕራባውያኑ የሰፈነው ዴሞክራሲ ለኛም የጠረኑ መዓዛ ይደርሰናል::

የፖለቲካ መሪዎችም ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን ቁርጠኛ ሲሆኑ ነፃና ገለልተኛ ተቋማት በተግባር ነፃ እና ገለልተኛ ሆነው እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራሉ:: ቁርጠኛ መሪዎች በሌሉበት ደግሞ ለሀገርና ለህዝብ ታማኝ የሆኑ ዜጐችና ተቋማቱ እንዲኖሩ ያደፈርጋሉ:: ይህ በሌለበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በምኞት ብቻ ሊመጣ ስለማይችል ዜጐች በተለይም ወጣቱ ትውልድ ኃላፊነቱን በብቃት ሊወጣ ይግባል የሚል ፅኑ እምነት አለኝ::

ይህንን ስል በወጣቱ ጫንቃ ላይ የተጫነውን የፍርሃት ድሪቶ በመዘንጋት አይደለም:: የዛሬው እውነታ የሚያሳየኝ የስርዓቱ ደጋፊ ስትሆን በነፃነት የምትኖርበት የልዩነትን ሀሳብ ይዘህ ዴሞራሲያዊ ትግል እንኳን ስታደርግ ሰው በመሆንህ በህይወት ዘመንህ የሰራኸው ሀጢያት ካለ ተፈልጎ ለማሸማቀቂያ የሚቀርብበት በመሆኑ ብዙዎች በፍርሃት ተሸማቀውና አንገታቸውን ደፍተው የሚኖሩበት ሁኔታ ነው በግልፅ የሚታየው፣ አልፎ ተርፎ ተፈልጎ ሀጢያት ቢጠፋብህ እንኳ በየቀኑ ሲፈለግ እና ሲፈጠር የሚታደር በመሆኑ ፈተናው ቀላል እንደማይሆን ግልጽ ነው::

እንደዚህ ያለውን አስተሳሰብ ታግለን ማስተካከል ደግሞ የዜጐች በተለይ የወጣቶች ዋንኛ ኃላፊነት ነው:: ይህ ካልሆነ የተሳሳተው አስተሳሰብ ከዚህ በላይ እየረዘመ ሄዶ አብዮታዊነት ከኢትዮጵያዊነት በላይ መሆኑ ይቀጥላል፣ መንግስት ቆም ብሎ ስህተቱን ለማየትና ለማረም ዝግጁ ካልሆነ አብዮታዊነት ከኢትዮጵያዊነት በላይ የመኖር ዋስትና ሆኖ መገደዱ ከቀጠለ ታድያ ሀገራችን የት ነው?

ዕንቁ የቤተሰብዎ መፅሔት
ነገ በገበያ ላይ ትውላለች
ጃዝ ምስለ ረቂቅ ሙዚቃ
ሠርፀ ፍሬስብሀት
አክሳፎስ
ይስማዕከ ወርቁ
ነፍስ ያላት ቤተክርስቲያን
አባይነህ ካሴ
“ባለሥልጣን ወይስ ባለሰይጣን”
ቢኒያም እሸቱ (ጆቤሣ)
አስገራሚ ነገሥታት በጥንታዊት ኢትዮጵያ
ቢንያም ወርቁ


## አለም አቀፍ

# የሩሲያ እና የቻይና እጅ በሶርያ

ካሳሁን አ.

ከስምንት ሺህ በላይ የሚሆኑ ሶርያውያንን ህይወት የቀጠፈው አመፅ አሁንም እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህንን ብጥብጥ ያስቆማል የተባለለት ባለስድስት ነጥብ የሰላም ስምምነት እቅድ በቀድሞው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናን ለበሽር አላሳድ መንግስት የቀረበ ሲሆን በቅድመ ይዘቱም ላይ መሪው በሽር አላሳድ መስማማታቸው ተገልጿል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና የአረብ ሊግ ተወካዮች እንደገለፁት ከሆነ የሶሪያው ፕሬዚዳንት በኮፊ አናን የቀረበላቸውን ባለስድስት ነጥብ የሰላም ስምምነት የያዘውን ደብዳቤ መቀበላቸው እና ለተግባራዊነቱም የበኩላቸውን እንደሚያደርጉ መናገራቸው የሰላም ስምምነቱ ተስፋ እንዲጣልበት አድርጎታል ይላሉ፡፡

### የኮፊ አናን መንገድ

የኮፊ አናን ቃል አቀባይ የሆኑት አህመድ ትውዚ እንደ ገለፁት ከሆነ በሰላም ስምምነት ውስጥ ተካተው ተቀባይነት ካገኙት ቅድመ ሁኔታዎች መካከል የሰብዓዊ አገልግሎት ተቋማት የሚያቀርቧቸውን የተለያዩ ሰብአዊ እርዳታዎች እንዳይስተጓጎሉ ለማድረግ ለሁለት ሰዓታት ያህል የጦር አቁም ስምምነት ማድረግ፣ ወታደሮች እና ከባባድ የጦር መሳሪያዎችን የተሸከሙ ካሚዮኖች ሲቪል ሰዎች ካሉበት አካባቢ ማስወጣት፣ ሁሉም ወገኖች ብጥብጡን ለማስቆም በቁርጠኝነት እንዲሰሩ መተባበር፣ ያለምንም ማስረጃ በዘፈቀደ የታሰሩት ግለሰቦች በአፋጣኝ እንዲፈቱ ማድረግ፣ ወደ ረብሻው ቀጠና ጋዜጠኞች ገብተው እንዲዘግቡ ፍቃድ መስጠት፣ ለሶሪያ ዜጎች የመሰብሰብ፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን ማረጋገጥ እና ተፋላሚ ቡድኖች የሁለትዮሽ ምክክር ለማድረግ የተዘጋጁ መሆን አለባቸው የሚሉትን መሰረታዊ የማመቻመች ሀሳብ በውስጡ ያዘለ ነው፡፡ ይህ የስምምነት ቅድመ ረቂቅ በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ማግኘት ከቻለ ሶርያ አሁን ካለችበት የቀውስ አዘቅጥ ባጭር ጊዜ ውስጥ ልትወጣ ትችላለች የሚለው የብዙዎቹ እምነት ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ ይህ ስምምነት በዘላቂነት የሶርያን ችግር አይፈታም የሚሉ ወገኖች ቢኖሩም ስምምነቱን ተከትሎ ሶሪያ ለአጭር ጊዜም ቢሆን ለምታገኘው ሰላም ዋጋ መስጠት ይገባል ይላሉ፡፡

ኮፊ አናን በበኩላቸው ይህ የሰላም ስምምነት ፍሬያማ ይሆን ዘንድ አስቀድመው በቻይና እና በሩሲያ መንግስታት ላይ ጫና ማሳደር ተገቢ መሆኑን ስላመኑበት የዲፕሎማሲውን ስራ የጀመሩት ከዚያው ነው፡፡ የሶርያ ችግር ያለሁለቱ አገራት ቀና ተሳትፎ መስመር መያዝ እንደማይችል ይናገራሉ እኚህ ግለሰብ፡፡

የአለም መንግስታት እስከዛሬ በሶሪያ መንግስት ላይ እየተወሰደ ባለው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ማዘናቸውን የገለፁ ቢሆንም በሌሎቹ የአረብ አገራት ላይ እንደወሰዱት አይነት እርምጃ ለመውሰድ ሲቸገሩ እናያለን፡፡ የተ.መ.ድ የፀጥታው ምክር ቤት በሶሪያ ላይ ሊወሰድ ስለታሰበው የተለያዩ አማራጮች በጋራ መወሰን አልቻለም፡፡ ለዚህም በምክንያትነት የተቀመጠው በድርጅቱ ድምፅን በድምፅ የመሻር ስልጣን የተሰጣቸው የሩስያ እና የቻይና እምቢተኝነት ነው፡፡

### የሩሲያ እና የቻይና እጅ

ሶሪያ በአለማችን ከሚገኙ አገራት አብዛኛውን የጦር መሳሪያ ግዢ የምትፈፅመው ከሩስያ ነው፡፡ ቻይናም ቢሆን በአለማችን ብዙ ሸቀጦቿን ከምታራግፍባቸው ሶስት አገራት መካከል ሶርያ አንዷ ናት፡፡ እነዚህ ሁለቱ አገራት በበሽር አላሳድ መንግስት ላይ ተንጠላጥሎ የተመሰረተው የኢኮኖሚ ጥቅማቸውን ለሌላ አሳልፈው መስጠት አይፈልጉም፡፡ አገራቱ ከሰብዓዊ መብት፣ የዜጎች ግድያ እና እንግልት ይልቅ ከአገሪቷ ለሚያገኙት የኢኮኖሚ ጥቅም ቅድሚያውን ይሰጣሉ፡፡ በዚህ አቋማቸው ለሚሰነዘርባቸው ወቀሳ የሚያቀርቡት ምላሽ ‹‹በአገራት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ መግባት አያስፈልግም›› የሚል ነው፡፡

የሶሪያ መንግስት ብዙ ዜጎቹን እየገደለ ባለበት በአሁኑ ወቅት የቻይናው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስለሁኔታው አስተያየት እንዲሰጡ ሲጠየቁ የሰጡት ምላሽ የአገራቸውን አቋም በደንብ ያንፀባርቃል፡፡ ‹‹ከሶሪያ መንግስት ጋር ያለን ግንኙነት ላለፉት ሃምሳ አመታት የዘለቀ እና በየጊዜው እየተሻሻለ የመጣ ነው፡፡ ወደፊትም ይቀጥላል›› ያሉ ሲሆን አያይዘውም ‹‹ሶሪያ በጎላን ተራሮች ላይ ያላትን አቋም እንደግፋለን›› ማለታቸው ተገልጿል፡፡ የቻይናን መግለጫ የፖለቲካ ተንታኞች እከክልኝ ልከክልህ (tit for tat) የሚባለው አይነት ነው ይሉታል፡፡ ቻይና በሰፊው ከምትወገዝባቸውን የታይዋን፣ የቲቤት እና የሰብዓዊ መብት ረገጣ አስመልክቶ የተለያዩ አገራት ውግዘት ቢያደርሱባትም ሶርያ በያዘችው አቋም ግን ደስተኛ ናት፡፡ ሶርያ ቻይና ሉዓላዊ ግዛቶቼ ናቸው በምትላቸው እነዚህ አገሮች ላይ ሶሪያ ባላት አቋም ሙሉ ድጋፏን ለቻይና ሰጥታለች፡፡ ቻይና በዚህ የሶሪያ አቋም ደስተኛ ከመሆኗ በተጨማሪ በሶሪያ የመንግስት ለውጥ እንዲመጣ ፍላጎት እንደሌላት በይፋ አስታውቃለች፡፡ በተ.መ.ድ የቻይና ቋሚ ተወካይ የሆኑት ግለሰብ የሰጡት መግለጫ ለዚህ አንድ ማሳያ ነው፡፡ በሶሪያ እየተደረገ ያለው የሰላማዊ ሰዎች ግድያ የግድ ሊያቆም ይገባል በሚለው ላይ አገራቸው የምትስማማ ቢሆንም ይህንን ለማስቆም ሲባል ግን በኃይል የመንግስት ለውጥ መምጣት አለበት የሚባለውን አገራቸው እንደማትደግፍ አረጋግጠዋል፡፡

የሩሲያ መንግስትም ቢሆን ከዚህ የተለየ አቋም እንደሌለው ተናግሯል፡፡ የሩሲያ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን ከበሽር አላሳድ ጋር በደማስቆ ተገናኝተው በመከሩበት ወቅት የሩስያን መንግስት አቋም ግልፅ አድርገውላቸዋል፡፡ የሩስያው ልዑክ መንግስታቸው ብጥብጡን ለማስቆም እያደረገ ያለውን ጥረት እንደሚደግፍ ያስታወቁ ሲሆን የማናቸውም የውጭ ኃይል ጣልቃ ገብነትን በእጅጉ እንደሚያወግዙ ይፋ አድርገዋል፡፡

የቻይና እና ሩስያ በሶርያ ላይ ያላቸውን አቋም ንፁህን ለማስጨፍጨፍ ፍቃድ እንዲያገኙ ህጋዊ ሽፋን ሰጥቷቸዋል የሚሉት የተለያዩ አገራት ዲፕሎማቶች መዘዙ በቀጣይም ከዚህም የከፋ ነው ይላሉ፡፡

### ኢራን እና ሳውዲ……

የሶርያን መንግስት በእጅጉ ይረዳል የሚባለው ሌላኛው የቀጠናው አገር ኢራን ለቀውሱ መባባስ የራሷን ድርሻ በመወጣት ላይ ትገኛለች ይላሉ፡፡ ለዚህ በማስረጃነት የሚያቀርቡት ሁለት የኢራን ባህር ኃይል ቡድን መርከቦች ተጨማሪ ወታደራዊ ስልጠና ለሶሪያ መንግስት ወታደሮች ለመስጠት ማቀዳቸው ሲሆን ለዚህም ድርጊቷ ሩስያ እና ቻይና የሽፋን ድጋፍ እየሰጡ መሆናቸውን የእስራኤል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ገልፀዋል፡፡

እነዚህ ሁሉ አለመግባባቶች ተደማምረው በቀጣይ የሶርያ እጣ ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል በሚለው ዙሪያ ፖለቲካ ተንታኞቹ የተለያዩ መላምቶችን አስቀምጠዋል፡፡ ምዕራባውያን ሙሉ ለሙሉ ተቃዋሚዎችን ወደ መርዳቱ የሚያዘነብሉ ከሆነ ሩስያ እና ቻይናም የበሽር አላሳድ መንግስትን መደገፋቸው ስለማይቀር አገሪቷ ወደ ለየለት የእርስ በርስ ጦርነት ልታመራ ትችላለች የሚለው ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ሶርያን በቅርብ የሚያዋስኗት ሳዑዲ አረቢያ እና ኢራን በሶሪያ ላይ የያዙት አቋም የተለያየ መሆኑ ቀጠናውን ወደለየለት ብጥብጥ እንዳይከተው ትልቅ ስጋት ፈጥሯል፡፡ ኢራን የሶርያ መንግስትን መርዳት መጀመሯ ያበሳጫቸው የሳዑዲ ልኡላኖች በቀጥታ የጦር መሳሪያ ለተቋዋሚዎች በማቀበል ቀውሱን እያባባሱ ይገኛሉ፡፡ በቀጣይ እስራኤል በኢራን የኒውክለር ፕሮግራም ላይ ልትወስድ ትችላለች የሚባለው የጥቃት እርምጃ ከእርስ በርስ ጦርነቱ በተጨማሪ የሶርያን አለመረጋጋት ወደለየለት አዘቅጥ ውስጥ ይከተዋል የሚል ፍራቻ አለ፡፡

# የአባይ ግድብ ቀያሽ የት እንደገቡ ሳይታወቅ 25 ቀን አለፈው

## - ‹‹በጣም ተረብሸናል›› ቤተሰቦቻቸው

በኤልያስ ገብሩ

ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ወደ ሆለታ ሊዘረጋ ለታሰበው የከፍተኛ ኤሌክትሪክ ኃይል መስመር የቅየሳ ስራ ተሰማርተው ከነበሩት ሰራተኞች መካከል አቶ አጥናፉሰገደ ተስፋዬ ከመጋቢት 10ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 8 ሰዓት ጀምሮ በስራ ላይ እያሉ በጫካ ውስጥ ጠፍተው እስከአሁን ድረስ የገቡበት አለመታወቁ ተገለፀ፡፡

ግለሰቡ ከ2000 ዓ.ም. ጀምሮ ሜክሲኮ አደባባይ በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን የኢንጂነሪንግ ክፍል ውስጥ ተቀጥረው በሰርቬየር የስራ ቦታ ይሰሩ እንደነበር ባለቤታቸው ወ/ሮ ወይንሸት ኃ/ሚካኤልና ወንድማቸው አቶ ዮሴፍ ተስፋዬ ለፍትሕ አስረድተዋል፡፡ ‹‹ወንድሜ በአሶሳ ክልል ለስራ ተመድቦ ወደሕዳሴው ግድብ ከሄደ አንድ አመት ሆኖታል፡፡ በየዓመት በዓላቱ ቤተሰቦቹ ጋር መጥቶ ያሳልፋል፡፡ በቅርቡ ለገና በዓል መጥቶ ተመልሶ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ በስልክ ብንገናኝም በድምፅ ከጠፋብን አንድ ወር አልፎታል›› ያሉን ወንድማቸው አቶ ዮሴፍ ናቸው፡፡

‹‹ባለቤቴ ከጠፋብኝና ድምፁን ካጧሁት ከወር በላይ ሆነ›› የሚሉት ወ/ሮ ወይንሸት፣ ሁኔታው ሲጨንቃቸው ከአቶ ዮሴፍ ጋር በመሆን ሜክሲኮ ዋና መ/ቤቱ ድረስ በመሄድ የክፍል ኃላፊው ናቸው የተባሉት አቶ ሰለሞንን አነጋገረዋቸው እንደነበረ ይናገራሉ፡፡ አቶ ሰለሞንም ‹‹እዛ ያሉ ሰራተኞችን በኔትወርክ ችግር ምክንያት ለስራ ልናገኛቸው አልቻልንም፡፡ ስራ ለምን እንዳቋረጡ ለማወቅ በስፍራው ከሚሰሩት ልጆች ጋር ለመነጋገር ትኬት አስቆርጬ ሊሄዱ ነው፡፡› የሚል ምላሽ በወቅቱ እንደሰጧቸው አቶ ዮሴፍ ለፍትህ ተናግረዋል፡፡

ሆኖም ወ/ሮ ወይንሸት ከሚያውቁት የባለቤታቸው ጓደኛ፣ ‹‹ጠፍቷል እየተባለ ነው›› የሚል መረጃ ይደርሳቸዋል፡፡ አቶ ዮሴፍም መጋቢት 18/2004 ዓ.ም. ቀጥታ ዋናው መ/ቤት ድረስ በመሄድ በድጋሚ አቶ ሰለሞንን ‹‹ጠፍቷል እየተባለ ለምን በግልፅ አልነገራችሁንም›› ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡

አቶ ሰለሞንም ‹‹ያልነገርኳችሁ ቤተሰብን ለማረጋጋት ብዬ ነው፡፡ ምክንያቱም ሁኔታው ምን እንደሆነ በግልፅ አላወኩኝም፡፡ ሌሎች አብረውት የሚሰሩ ልጆችም አቅጣጫ ስተው ጠፍተው ነበር›› የሚል መልስ እንደሰጧቸው የሚገልፁት አቶ ዮሴፍ፣ በ20/07/2004 ዓ.ም. ከአጐታቸውና ከጓደኛቸው ጋር በመሆን ወደ ቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንጌ ወረዳ በመሄድ ጉዳዩን ለማወቅ ጥረት አድርገው ነበር፡፡



ሰርቬየር አጥናፍሰገድ ተስፋዬ

አቶ ዮሴፍ በዚያም ያሉ ሰዎችን ሲጠይቁ ሰራተኞች በግሩፕ ሆነው ጠዋት ተነስተው ለስራ እንደሚሰማሩ፣ ስራውንም ከወረዳው 20 ኪሎ ሜትር ወደ ውስጥ ገብተው እንደሚሰሩ፣ ከስራ መልስም ከቀኑ 8:00 ሰዓት ላይ ሁሉም ተገናኝተው በተመደበላቸው መኪና ወደ ካምፕ እንደሚመለሱ፣ ነገር ግን አቶ አጥናፉ መጋቢት 10/2004 ዓ.ም. ከቀኑ 8 ሰዓት ላይ ከሶስት ረዳቶቻቸው ጋር አለመመለሳቸውን ለማወቅ ችለዋል፡፡ እንዲሁም ከወንድማቸው ጋር ሲሰሩ ከነበሩት መካከል ሁለቱ በእለቱ ከምሽቱ 4 ሰዓት ላይ ወደ ካምፕ ተመልሰው የስራ ባልደረባቸው እንደጠፉ መናገራቸውንና አንደኛው ሰራተኛ ደግሞ በነጋታው ቀን 8:00 ሰዓት ላይ ተመልሶ መምጣቱን ሰምተዋል፡፡

የአከባቢው ፖሊሲም በወቅቱ ከተወሰኑ የህብረተሰቡ ክፍሎች ጋር በመሆን በጫካው ውስጥ ተሰማርቶ ፍለጋ እንዳደረገ ከፖሊስ እንደተነገራቸው የሚገልፁት የቀያሳ ባለሙያው ወንድም ወንድማቸው ለስራ ይጠቀምበት የነበረውን ጂ.ፒ.ኤስና የሬዲዮ መገናኛ ይዞ እንደተሰወረ ለፍትህ ተናግረዋል፡፡ ‹‹ወንድሜ በስራ የረዥም ጊዜ ልምድ ኖሮት፣ መሳሪያ አጠቃቀም በደንብ እያወቀ፣ በፕሮጀክቱ ለአንድ ዓመት ያህል እየሰራ እያለ ሶስቱ ከእርሱ ጋር የሚሰሩት ሰራተኞች ተመልሰው ከመጡ የእሱን መሰወር ጭንቅላቴ ሊቀበለው አልቻለም፡፡ ምናልባት የተቀነባበረ ሴራ ያለ ይመስለኛል›› የሚሉት አቶ ዮሴፍ ሶስቱም ሰራተኞች ጉዳዩ እንዲጣራ ተብሎ በአሶሳ እስር ቤት እንደሚገኙ መረጃው እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

ፖሊስ አንዴ ፍለጋ ካደረገ በኋላ በተደጋጋሚ የፍለጋ ስራ አለመስራቱንና ጉዳዩ በቸልታ መታየቱን በአዘኔታ በመጥቀስ፣ ‹‹ወንድሜ በስራ አጋጣሚ ችግር ደርሶበት ህይወቱ አልፎ ከሆነም ይነገረን፡፡ በህይወት ካለም ያለበትን ሁኔታ መንግስት ተከታትሎ ሊያሳውቀን ይገባል… እሱ እንደ አንድ ዜጋ ሙያውንና እውቀቱን ለስራ ሊሰዋ ነው የሄደው፡፡ በስራ አጋጣሚ አደጋ ሊደርስበት ይችላል፡፡ ይሄንን እናምናለን›› ብለዋል -የቀያሹ ወንድም፡፡

‹‹ባለቤቴ ትዳሩንና የሁለት አመት ህፃን ልጁን ያክል ነገር ትቶ በረሃ ሄዶ ሲቀር በጣም ያሳዝናል፡፡ ሞተ ወይም አለ ማለት አንድ ነገር ነው፡፡ መ/ቤቱ ይሄንን ያህል ቀን ሲጠፋ እንኳን ለቤተሰብ አላሳወቀም፡፡ እሱ የሄደው ለመንግስትና ለሀገር ትልቅ ነገር ሊገነባ ነው፡፡ ልጃችን እኔ ሳለቅስ የሚሰማት ስሜት በጣም ያሳዝናል፡፡ እንዲሁ ጠፋ ሲባል እጅግ ይከብዳል፡፡ የመጨረሻውን ማወቅ ይገባናል፡፡›› በማለት ወ/ሮ ወይንሸት እንባ እየተናነቃት ለፍትህ ተናግራለች፡፡ ጉዳዩን አስመልክቶ የአቶ አጥናፉ ሰገደ የክፍል አለቃው ናቸው ወደተባሉት አቶ ሰለሞን ተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ ደውለን ስንጠይቃቸው ‹‹‹ምን ፈለክ?›› ካሉ በኋላ ‹‹አይ… አይ እኔ አይመለከተኝም፡፡ ድርጅቱ… አቶ አጥናፍ ሰገድ የሚባል ሰው አላውቅም፡፡ የማውቀው ነገር የለም›› በማለት ስልኩን ዘግተውታል፡፡

መንግስት ስለጉዳዩ የሚያውቀው ነገር ካለ በማለትም የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ደኤታ ለሆኑት አቶ ሽመልስ ከማል ተንቀሳቃሽ ስልካቸው ላይ ብንደውልም ስልካቸው ሊነሳ ባለመቻሉ የመንግስትን ምላሽ ማካተት አልቻልንም፡፡

# የህይወት አድን ጥሪ



የ7 ዓመት ህፃን ልጃችን የታች አገጩና የላይ አፉ እየጠበበ መጥተው አፉ በመግጠሙ ህፃኑ ምግብ እያማረው ምግብ መብላት ወደማይችልበት ውሃ መጣት እያማረው ውሃ መጣት ወደማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ ለህክምና ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ብንወስደውም በአስቸኳይ ወደ ውጪ አገር ተወስዶ ካልታከመ በአጭር ጊዜ ውስጥ አፉ ሙሉ በሙሉ ገጥሞ ምግብ መብላትና ውሃ መጠጣት ወደማይችልበት ደረጃ ደርሶ ህይወቱ ሊያልፍ እንደሚችል በማስንቀቅ የቦርድ ውሳኔ ሰጥተዋል፡፡

ስለዚህ ወደ ውጪ አገር ወስዶ ለማሳከም ብር 700,000 (ሰባት መቶ ሺህ ብር) የተጠየቅን ስልሆነ ችግሩ ከአቅማችን በላይ ስለሆነብን ህፃን ልጃችንን አይን አይኑን እያየነው የመጨረሻ ህይወቱን የሚያልፍበትን ያን ክፉ ቀን በመጠባበቅ ላይ በመሆናችን እርስዎም አቅምዎን የፈቀደው ርዳታ በማድረግ ህፃን ልጃችንን ከመቀጠፍ እንዲያድኑልን በፈጣሪ ስም እንማፀናለን፡፡

አባቱ አክሊሉ ሙሉጌታ፡- 0912-06 98 57

እናቱ ደስታ ሟርጋ፡- 0912-39 89 05

የባንክ አካውንት 000103 የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጉንችሬ ቅርንጫፍ

# ተምጫ እበረሃው ላይ ብረት ምጣድ ጠፍቶ፤ አመጣው እቤቱ በምንይሽር ቆልቶ::



ከታዴዎስ ታንቱ

ተአምር በተአምር ካልወረደ አያመልጥም! ያለተስፋ በተስፋ አይታሰብም:: አርበኛው ተከብቧል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በከስካሽና ድርግሚት ወንዞች መጋጠሚያ ላይ ተደራጅቷል:: መሽጓል:: ዙሪያው በሙሉ ከጫማው ሥር ወድቋል፡፡ አርበኛው እንዴት ሊያመልጥ ይችላል? ወፍ አይደለም! ወደ ሰማይ አይነሳም! ነፋስ አይደለም! ከዓይነ ስጋ አይሾልክም! በሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሮ የገዘፈ ተክለ አካል ዙሪያውን እንደ ማርያም መቀነት ከከበበው መድፍ፣ መትረየስ፣ ጠብመንጃና ቦምብ እንዴት ሊያመልጥ ይችላል? ይልቁንስ የአካል ቅርፁ እንደ ተጠበቀ ቅሪት በድኑ መገኘቱ ያጠራጥራል:: ግን ማን ያውቃል? ደፋርና ጭስ መውጫ አያጣም:: ከበባውን በጥሶ ይወጣ ይሆናል:: ጦርነቱ ቀጥሏል! መጨረሻው በመጨረሻ ይታያል::

አርበኛ ከተራ ሰው ይለያል:: ጀግና እንደ ቀትር እባብ ይወረወራል:: ተአምር አይጠብቅም:: በሰብዓዊ ኃይሉ ራሱ ተአምር ይፈጥራል! ተኩሱ ቀልጧል! ህልቆ መሳፍርት የሌለው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ተሰልፏል:: መማረክ ግን ፈፅሞ አይታሰብም! አንበሳ በዝንጀሮ አይገደልም! መጥፎ አጋጣሚ ግን የበላይነትን አሳይቷል:: የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጠንክሯል::

ጄኔራል ትራኪያ መንዝንና ተጉለትን ጨርሶ ለማጥፋት ቆርጦ ተነሥቷል:: መድፍ ያጓራል! መትረየስ ይተኩሳል! ቦምብ ይወረወራል! ጠብመንጃ ይንጣጣል! በውጊያው ያለ ጥርጥር ግፈኛው ወራሪ የበላይነትን ይዟል! የእሳት ወረዳ በሐሳብ ተከልሏል! ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል!

በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ ጀግና ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ምሽግ አጠገብ ደርሷል:: ይህ ተአምር ሊመስለን ይችላል:: ግን አይደለም! በጀግንነት የተከፈለ የመስዋዕትነት ውጤት መሆኑ ተመዝግቧል:: ጀግናው አርበኛ ከምሽጉ ተጠግቷል! የመትረየስ ተኩሱን አቋርጧል! ከቦምብ ውርወራም ተገትቷል! ምን ሊያደርግ አስቦ ይሆን? ጀግናው የኢትዮጵያ ህዝብ ልጅ የውጊያ ስልቱን ቀይሯል! አሃ! እንዲህ ነው ለካ! በጎራዴ ገብቷል! የፋሽስት ኢጣሊያ ተዋጊዎች ተርበትብተዋል! ጦርነቱ በጨበጣ ሆኗል:: ድምጽ የሌለው መሳሪያ በግዳጅ ላይ ውሏል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪዎች ጎራዴን በሳንጃ መቋቋም ተስኗቸዋል! ሙንጣዝ አንገቱ ተቀልቷል! በስመ አብ ሳይባል ተባርኳል! ያስተጋባል! የኃይል ሚዛን ተለውጧል! ጀግናው አርበኛ የበላይነትን ይዟል! ጎራዴው ሰርቷል! በተለይም በፋሽስት ኢጣሊያ ዘንድ የተመሰገነውንና የታወቀውን ለማዳ አገልጋይ ቀኝ አዝማች አውላዬ የተባለውን ቀንጥሶ በመጣል ጀግናው አድናቆትን አግኝቷል:: ጀግናው አርበኛ የለማዳ አገልጋዩን ረጅም አልቤንም ማርኮ ወስዷል:: የሬሳ ነዶ በጎራዴ አስሯል:: ተአምር ሰርቷል:: የፋሽስት ኢጣሊያን የተጠናከረ ምሽግ በሩን ሰብሯል! በጣም የሚያስደንቅ ድል አስመዝግቧል! ሬሳው እንኳ ተጨፍልቆ ከአፈር ጋር እንደሚዋሃድ የተተነበየለት ጀግና ከበባውን በጥሷል! እንደ ሲድራቅ፣ ምስራቅና አብዲናጎ እሳት ሳይነካው ወጥቷል! ሙንጣዞች፣ ቡልቅባሾችና ሹምባሾች ግን በወላፈኑ አልቀዋል:: ጀግናው ድል አድርጓል! ዓይኑን ያጎራጠርጣል! እንደ አንበሳ ይንጎማለላል! ታሪክ ይናገራል! ለዘለዓለም ሕያው ሆኗል:: ይህ የከፈለው ወልደ ጻድቅ የገድል ድምፅ ነው! መጋቢት 1 ቀን 1929 ዓ.ም.

ጀግናው የጦር አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ ይህን አንፀባራቂ ድል ያስመዘገበው ሰላሳ አርበኞችን ብቻ አስከትሎ እንደ ነበር በታሪክ ተቀርጿል:: በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት ተፋልሟል! በልቡ አላቅማማም:: በተግባርም አላወላወለም! በጦርነቱ ሂደት ሶስት አርበኞች ብቻ ቆስለዋል:: ታሪክ ይመሰክራል! ባይመስልም ሊታመን ይገባል:: በወቅቱ የነበረው የዓይን እማኝነት አረጋግጧል! ይህ እውነት ነው! እውነትም ይህ ሆኗል! ባንዳ ለሆዱ ሞቷል! አርበኛ ለነፃነቱ ተዋድቋል! ሁለት ጎራ በአንድ ሀገር! ታሪክ ራሱን ደግሟል! ዛሬም ባንዳና አርበኛ ተፋጥጠዋል!

ቆራጡ አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ኢትዮጵያን ለመያዝ ከመምጣቱ በፊት መንዝ ማማ ምድር በግብርና ስራ ኑሮውን ይመራ እንደ ነበር ታውቋል:: ቀደም ሲል አባቱ ስላረፉ ትምህርቱን አቋርጦ የተመለሰው የኢትዮጵያ ብርቅ ልጅ ከፈለው ወልደጻድቅ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የጥፋት እጁን በወገን ላይ ከመጫኑ በፊት መውዜር ጠብመንጃ እንደ ነበረው በአርበኝነት ዝርዝር ታሪኩ ውስጥ ተመልክቷል:: ቆየት ብሎ ደግሞ ከራስ ከበደ እጅ አንድ ቤልጅግ ድግን መትረየስ ተሸልሟል:: አሁን ምን ቀረው? የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ገብቷል:: ደህና ሁኝ ግብርና! ከፈለው ወልደጻድቅ ቆርጦ ተነስቷል! ወደ አርበኝነት አቅንቷል! የማን ቤት ፈርሶ የማን ይቀራል?

አንበሳው ከፈለው ስድስት ሰዎች ብቻ አስከትሎ ወጥቷል:: ግዳይ ለመጣል ቋምጧል:: የአንበሳን ለምድ የለበሰ በሬ ለመስበር ተንደርድሯል:: ከጣርማ በር ደርሷል! በልበሊት ላይ አድፍጧል! ጦርነት ተከፍቷል! ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ቡም! ይህ የምትሰሙት የተኩስና የቦምብ ድምፅ የሚያስተጋባው በቀጥታ ከበልበሊት የጦር ሜዳ ነው! ጀግናው ከፈለው ወልደ ጻድቅ በጦርነቱ የበላይነትን ይዟል! በልበሊት ቀውጢ ሆናለች! በአሁኑ ሰዓት ከፈለው አንድ የፋሽስት ኢጣሊያ መኰንን ገድሎ ሬሳውን ማርኳል! እንዲሁም መትረየስ ተኳሽ የነበረው አንድ የባንዳ አለቃ በዚህ ጦርነት ተገድሏል! ብዙዎች ደግሞ ቆስለዋል:: አርበኞች አጥቅተዋል!! ጳጉሜ 3 ቀን 1928 ዓ.ም.

ልበ ሙሉ የጦር ሰው ከፈለው ወልደጻድቅ ለሀገራችን አንድነትና ሉዓላዊነት በቁርጠኝነት ዘብ ቆሟል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ያጭዳል! በልበሊት እንደገና ሞጥ ይዟታል! ከፈለው ዝግጁ! ጦርነቱ ተከፍቷል! ማን በማን ሀገር ላይ ይፈነጫል? ማን የማንን መሬት ያርሳል? ማን የማንን ሐይማኖት ያረክሳል? ማን የማንን ሚስት ይደፍራታል? ድም! ድም! ድም! ቡም! ቡም! ከጧቱ አንድ ሰዓት ሆኗል! ከፈለው ወልደጻድቅ ሬሳ አምርቷል! በሰው ኃይልም ሆነ በጦር መሳሪያ ብልጫ ያለውን የፋሽስት ወራሪ አጥቅቷል! አሁን ከጧቱ አራት ሰዓት ይነበባል! የፋሽስት ወራሪ ፈርጥጧል! ግን ተስፋውን ቆርጦ አልተቀመጠም! ተጠናክሮ ተመልሷል! ጦርነቱ ቀጥሎ ውሏል! ሲጨልም በሁለቱም በኩል ተኩሱ እንዲቋረጥ የግድ ሆኗል! ከወራሪው እጅ ብዙ ጠብመንጃ ተማርኳል! ሁለት የወራሪው ኃይል መትረየሶች ሌሊት ሳይማረኩ አድረው በነጋታው ከአርበኞች እጅ ገብተዋል:: ይህ የጀግናው አርበኛ የከፈለው ወልደ ጻድቅ የድል ድምጽ ነው! ከበልበሊት! መስከረም 19 ቀን 1929 ዓ.ም.

ቆፍጣናው አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ ጠምሪ በተባለ ሥፍራም ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጋር ከፍተኛ ጦርነት አካሂዷል:: በዚሁ ጦርነት በጣም ብዙ የፋሽስት ኢጣሊያ ተዋጊዎች ተደምስሰዋል:: ብዙ ሬሳ በአርበኞች ተማርኳል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ የአርበኞችን ኃይል ፈፅሞ መቋቋም ተስኖታል! ጀግንነትን ከዓላማ ፅናት ጋር አጣምሮ የያዘው የኢትዮጵያ አርበኛ በጦርነት ተፈትኖ ተቀርፆ ወጥቷል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ተዋጊዎች የእሳት እራት ሆነዋል! የተቀሩት ፈርጥጠዋል:: ይህ ሁነት በታሪክ ተመልክቷል! ጀግናው ከፈለው በጠምሪ የጦር ሜዳ! የካቲት 23 ቀን 1929 ዓ.ም.

አይበገሬው አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ በአርበኝነት ተግባራዊ እንቅስቃሴው ሂደት ሌሎች አርበኞች የላይኛውን የውጊያ ቀጠና ሲይዙት ከፊሉን የፋሽስት ወራሪ ከወደ ሞፈር ውኃ ታቹን ቆርጦ ከፍተኛ ጀብዱ መፈፀሙም በታሪክ በአድናቆት ይነሳል! በእርግጥም ሊደነቅ ይገባል! ከፈለው ስምንት ሰው ብቻ ይዞ ገጥሟል! ከፊሉ የፋሽስት ኢጣሊያ ተዋጊ በጥይት ሲቆላ የተቀረው በናዳ አልቋል! ቀለቡንና ጭነቱን እንኳን ለማንሳት ሳይችል ቀርቷል:: ወደ ሰላ ድንጋይ ፈርጥጧል! ድል የወገን ሆኗል! የከፈለው ወልደ ጻድቅ ጀብዱ በሞፈር ውኃ! ሚያዝያ 26 ቀን 1929 ዓ.ም

የጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅ የአርበኝነት ገድል ተዘርዝሮ ሊያበቃ አይችልም:: በጣም ብዙ ነው:: እንደገና ከጦር ሜዳ ውሏል! ብዙ አልቆየም:: ሶስት ጣሊያኖችን ከአፈር ጋር አዋህዷል! የተወሰኑ ባንዳዎችንም ከምድር ገፅ አስወግዷል:: ጀብዱ ፈፅሟል! ሚያዝያ 29 ቀን 1929 ዓ.ም.

የአንዳንድ ጀግኖችን የጦር ሜዳ ጀብዱ ዝርዝር ተመልክተው በሕሊናቸው ጓዳ ምናብ ወለድ ቅንብር የመሰላቸው እንደማይታጡ አላጣንም:: የጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅ የአርበኝነት ጀብዱ በልል እሳቦት ከተአማኒነት ጥያቄ እንደማያመልጥ ይገባናል:: የምንለው ግን ብዙን ጊዜ ያልነውን ነው! ብናምንም ባናምንም አባቶቻችንና እናቶቻችን ወደር የሌላቸው ጀግኖች ነበሩ! ከፈለው ወልደጻድቅም አንዱ ሆኖ ወደ ታሪክ ገብቷል::

ቆራጡ የኢትዮጵያ አርበኛ ከፈለው ወልደ ጻድቅ ባሁኑ ሰዓት የት ይገኛል? እውነት ነው! በታሪክ ላይ ይገኛል! ግን በትክክል የት ይገኛል? ይህ ጀግና ባሁኑ ሰዓት ጅሩ ሙንጣር ወንዝ ላይ በፋሽስት ኢጣሊያ ኃይል ተከብቦ ይገኛል! እንዲያውም ከተከበበ ሁለተኛውን ቀን ይዟል! ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀለብና የጦር መሳሪያ ሊገባለት የሚችልበት ሁኔታ ፈፅሞ የለም! አሁንም ከፍተኛ ተኩስ ይሰማል! ድም! ቡም! ድም! ቡም! ጥይት! ቦምብ! ጥይት! ቦምብ! ጥይት! ቦምብ! አ! የምስራች! ምስር ብላ! ምንድነው? ከፈለው ከበባውን በጥሶ አርበኞችን አስከትሎ ወጥቷል! ዛሬ ግንቦት 5 ቀን 1929 ዓ.ም. ነው! ድንቅ! ድንቅ! ድንቅ!

ቆፍጣናው አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ አሁን ደግሞ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን የጦር አይሮፕላን መትቶ ለመጣል ተዘጋጅቶ ይጠባበቃል:: አይሮፕላኑ እየመጣ ነው! ትንሽ ዝቅ ብሏል! ከፈለው ዒላማ ውስጥ አስገብቶታል:: አይሮፕላኑ ዝቅ ብሎ ቀርቧል! ቦምብ ለመጣል ያሰበ ይመስላል! ከፈለው አከታትሎ አዘነበበት:: ድም! ድም! ድም! በውስጡ የነበሩ አምስት ሰዎች በሙሉ ሞተዋል! ግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም. ይህ ሁነት ተመዝግቧል! ከፈለው ተደነቀ! በሕዝቡም ተወደሰ!!

ጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅ አሁንም በጦር ሜዳ በከፍተኛ ፍልሚያ ተሰማርቷል:: ጀግና ይወድቃል! ጀግና ይጥላል! ከድል በፊት ስለዕረፍት ማን ያስባል? ለጀግና ሞት ሰርጉ ሆኗል:: ወሳኝ ጦርነት ቀጥሏል! ከፈለው ወልደ ጻድቅ ሦስት አምባ ዋሻ በተባለ ስፍራ ተከብቧል! የሞት ሽረት ፍልሚያ መሆኑ ይመዝግብልን! ከጧት አንስቶ ውጊያው ተፋልሟል! ከፈለው ግን በሂደት ተኩሱን ቀንሷል:: አንድ ብልሃት የዘየደ ይመስላል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሊማርከው ተቃርቧል! ከፈለው ያለ የሌለ ኃይሉን ተጠቅሟል! ብዙ ባንዳ በጥይት ቆልቶ ከትቢያ ጋር አዋህዶታል! ወራሪው ኃይል በዚህ ተናድዶ በቅርቡ የነበረውን የጦር መሳሪያ ሁሉ ለጦርነት አውሎታል:: ጀግናው አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ ግን የሚበገር ሆኖ አልተገኘም:: ሲዋጋ ዋለ:: በአስራ ሁለት ሰዓት ላይ ከበባውን በጥሶ ወጣ! ነገር ግን ጀግናው የጀግና ዘር በጣም ተጎድቶ ይታያል:: አካሉ ተበሳስቷል:: በአስራ አራት ቦታ ላይ በጥይት ቆስሏል:: ይህ ለሀገር ነፃነት የተከፈለ ዋጋ ነው:: ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ሀገርን ከመውደድ ይመነጫል! የቀደምት ኢትዮጵያውያን የነፃነት ተጋድሎ ይህን ይመስላል!

በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት የተካነው ጀግናው አርበኛ ከፈለው ወልደ ጻድቅ ቁስሉ ጠገግ እስኪል ድረስ እንኳ አልቆየም:: በደስታውም በሐዘኑም ከጎኑ የማትለየው ውድ ባለቤቱ አስገደች አይዞህ በል በፋሽስቶች ጥይት ቆስላ ስለተማረከች እሷን ለማስለቀቅ ተነሳ:: ጀግና ያሰበውን ከፍጻሜ ሳያደርስ መች ይመለሳል? በተማረከች በአስራ አምስተኛው ቀን በፋሽስቶች ሰፈር አደጋ በመጣል በክብር መልሶ አምጥቷታል:: ጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅ ለፋሽስቶች በባንዳነት ያደሩ ለማዳ አገልጋዮችንም በመምከርና በማስተማር ወደ ወገን መመለሱ ታውቋል!

በሀገር ፍቅር የተቃጠለው አርበኛው ከፈለው ወልደጻድቅ ጥቅምት 12ቀን 1930 ዓ.ም. ላሎ ምድር ወይን አምባ በተባለ ስፍራ ደግሞ ከፍተኛ ቁጥር ከነበረው የፋሽስት ተዋጊ ጋር ጦርነት ገጥሞ በርካታ መኰንኖችን ፈጅቷል:: ባንዳዎችንም ገድሏል:: የጦር መሳሪያም ማርኳል::

በተመሳሳይ መልኩ ጀግናው ከፈለው በህዳር ወር 1930 ዓ.ም. አጠረት በተባለው ቦታ ከወራሪው ኃይል ጋር ከፍተኛ ጦርነት አካሒዶ ድል ነስቷል:: በዚህም ብቻ አላበቃም:: በዚሁ በሕዳር ወር በ1930 ዓ.ም. ደንገዛ ወረሚ ላይ ተዋግቷል:: በዚህ ጦርነት ጀግናው ከፈለው በብርቱ ቆስሏል:: በዕለቱ ማን ድል እንደሚያደርግ ሳይረጋገጥ ከቀኑ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ፋሽስቶች ወደ ሰፈራቸው ገቡ:: አርበኞችም እንዲሁ ወደ ምሽጋቸው ተመልሰዋል:: የጥቂት ቀናት እረፍት ተደርጓል! ጀግናው ከፈለው ግን የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሀገራችንን ለቅቆ እስካልወጣ ድረስ እረፍት የሚፈልግ ሰው አልነበረም:: ስለዚህ ታህሳስ 16 ቀን 1930 ዓ.ም. ላሎ ምድር ቆላ አገረ መርፊያ በተባለ ቀበሌ ላይ

## ከቀረርቶ የተወሰደ

ከወራሪው ኃይል ጋር ከፍተኛ ጦርነት አካሂዷል:: በዚሁ ዕለት ሁለት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ሹማምንትን ገድሏል:: እንዲሁም ለማዳ አገልጋይ ባንዳዎችን በመትረየስ አጭዷል! የታወቀ ነገር ነው! ስጋ መሬት ወድቆ አፈር ሳይነካው አይነሳም! ጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅም በዕለቱ በመትረየስ ትከሻው ላይ በብርቱ ተመትቷል! አልተሰዋም:: ከፈለው ገና ብዙ ይሰራል! ጀግናው ሞት አይፈራም! ፈሪ በቁሙ ሞቷል! ጀግና ግን ሞቶ በህይወት ይኖራል! ከፈለው ይህን አሳምሮ ያውቃል!

የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ የሆነው አርበኛው ከፈለው በየካቲት ወር 1930 ዓ.ም. ጀማ ላይ ታየ:: ለማዳ አገልጋይ ሁላ ተንጸረጸረ! የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል! ጦርነት ተከፈተ! ባንዳዎችን ከአፈር ጋር አዋሐደ:: ማን መሰላችሁ? ከፈለው ወልደጻድቅ እኮ ነው! አንድ ቸኮዝሎባክ መትረየስ ማርኳል! በተጨማሪም ሃያ አምስት ጠብመንጃዎችንና አንድ ባለቀለህ ሽጉጥ ማርኮ ከእጁ አስገብቷል!

ኢትዮጵያ ሀገራችን በከፍተኛ መከራ ላይ በነበረችበት ሰዓት ከመቅፀበት የደረሰላት አርበኛው ከፈለው ወልደ ጻድቅ ከየካቲት 23 ቀን 1931 ዓ.ም. አንስቶ ዘማቶ በተባለው ቦታ ላይ ከፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ጋር ለሁለት ቀንና ሌሊት ተዋግቷል! በዚሁ ጦርነት የአዳባይ ጅረት እስከ መርሓ-ቤቴ ድረስ በደም እንደተበከለ ታውቋል:: በተዛመደ መልኩ ሚያዝያ 5 ቀን 1931 ዓ.ም. ማማ ምድር እመዋይታ አቦ ጉር በተባለ ቦታ ላይ ጦርነት ገጥሞ ሃያ ጠብመንጃና ከሁለት ሺህ የሚበልጥ የአልቤን ጥይት ማርኳል:: በዚሁ ጦርነት ዘጠና ዘጠኝ የፋሽስት ተዋጊ ረግፏል:: ከመካከላቸው ሶስቱ ጣሊያኖች እንደነበሩ ታውቋል:: ላይታመን ይችላል! ግን እንመን! ከወገን አንድ ሰው ብቻ ቆስሏል!


ቆራጡ አርበኛ ከፈለው ወልደጻድቅ ግንቦት 28 ቀን 1931 ዓ.ም. ዙሪያ ምሁይ ቋች ላይ ከጧቱ 3 ሰዓት አንስቶ እስከ ምሽቱ ሁለት ሰዓት ድረስ ተዋግቷል:: አራት ድግን አልቤን መትረየስ ማርኳል! እንዲሁም ሰላሳ አምስት የምንሽርና አልቤን ጠብመንጃ ማርኮ ወስዷል!

የጀግናው ከፈለው ወልደ ጻድቅ የአርበኝነት ውሎ ተዘርዝሮ የሚያልቅ ባለመሆኑ እዚህ ላይ ጎምደነዋል:: ታሪኩ ለብቻው አንድ መጽሐፍ ይወጣዋል:: ልጆቹ ወይም የልጅ ልጆቹ ይሄዱበት! ለጀግኖች ቀናዒ የሆኑ ታሪክ ተመራማሪዎች ደግሞ በበለጠ ሊጨነቁበት ይገባል! አትጠራጠሩ! ከፈለው ወልደጻድቅ ሰው ነው! በዘጠኝ ወሩ ተወልዶ ሶስት ዓመት ጡት ጠብቷል! በቁርጠኝነት፣ በዓላማ ፅናትና በብሔራዊ ስሜት ልቋል! ጀግናው ከፈለው ወልደጻድቅ ከድል በኋላ የደጃዝማችነት ማዕረግ ተሰጥቶታል! በከፍተኛ ኃላፊነት ለእናት ሀገሩ አገልግሏል! ክብር ለከፈለው ወልደጻድቅ! ክብር በዱር በገደሉ ለወደቁ የኢትዮጵያ ጀግኖች!

ተምጫ እበረሃው ላይ ብረት ምጣድ ጠፍቶ፤
አመጣው እቤቱ በምንይሽር ቆልቶ::

አስደናቂው የፋር ኢንፍራሪድ ጀርመንየም እና ማግኔቲክ ቴራፒ

እንደ ብራስሌት እጅ ላይ በማሰር በሽታን ማዳን እንዲሁም መከላከል ይቻላል




ለአርትራይተስ እና ቁርጥማት
ለጀርባ ህመም ለትከሻ ህመም
ለከባድ ራስምታት ለመተንፈሻ ችግሮች
ለሳልና ለአስም ለሪህ ለማቃጠል ስሜት
ከእንቅልፍ ጋር ለተያያዙ ችግሮች
እና ለሌሎችም በርከታ የጤና ችግሮች መፍትሔ ይሰጣል

HARNESS

ይደውሉልን
0910 035578, 0911 19 62 51
P.O.Box 26982 code 1000 Addis Ababa

# እነእስክንድር ነጋ ለብይን ግንቦት ሶስት ተቀጠሩ

በሽብርተኝነት ወንጀል ተጠርጥረው በማረሚያ ቤት ሆነው የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ በሚገኙት በእነ አንዷለም አራጌ የክስ መዝገብ ተከሳሾች ያቀረቡት የመከላከያ ሁለት የኦዲዮ ቪዲዮ ማስረጃዎች ከትናንት በስቲያ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 3ኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ተደመጡ፡፡

በመጀመሪያ ጥዋት የቀረበው የኦዲዮ ቪዲዮ ማስረጃ 1ኛ ተከሳሽ የሆኑት አቶ አንዷለምን የሚመለከት ነበር፡፡ ‹‹የአረቡ አብዮትና የእኛ መነቃቃት›› “Ethiopian Awakening and the Arab spring” በሚል ርዕስ በግንቦት ወር 2003 መጨረሻ አካባቢ በቪዲዮ የተናገሩት ንግግር ሳይቆራረጥ ሙሉ በሙሉ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡

ሁለተኛው የቪዲዮ ማስረጃ የነበረው ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ነሐሴ 29/2003 ዓ.ም. በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ ጽ/ቤት ውስጥ ‹‹በኢትዮጵያ ሰላማዊ ለውጥ እንዴት?›› በሚል ርዕስ ፅሁፉ ሲያቀርብ የሚያሳይ ነው፡፡ በቪዲዮውም ላይ አንዷለምና እስክንድር ጐን ለጐን መድረክ ላይ ተቀምጠው አንዷለም እስክንድርን ሲያስተዋውቅ፣ እስክንድር ፅሁፉን ሲያቀርብ፣ ከተሰብሳቢዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ሲነሱና እስክንድር ሲመልስ ታይቷል፡፡

የተከላካይ ጠበቆች በመጀመሪያ 5ኛ ተከሳሽ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ እና 7ኛ ተከሳሽ እስክንድር ነጋ ግንቦት 7 አለመሆናቸውን በሚያቀርቡት የኦዲዮ ቪዲዮ ማስረጃ ላይ እንደሚያሳዩ በመናገር ለፍ/ቤቱ ጭብጥ አዝይዘው ነበር፡፡ ሆኖም አቃቤ ሕግ ሙሉው መቅረብ አለበት ሲል ተቃውሞ አቀረበ፡፡ ከዚያም ማስረጃው እየታየ እያለ ተከላካይ ጠበቆች ቪዲዮው ረዥም ሰዓት ስለሚፈጅ ሁለቱ ያደረጉትን ምልልስ ቆርጠን እናሳይ?›› በማለት ለፍ/ቤት ጥያቄ አቀረቡ፡፡ አቃቢያን ሕጎች የቀረበው ማስረጃ በአቃቤ ሕግ ማስረጃነት ከዚህ ቀደም ቀርቦ የነበረ መሆኑን አስታውሰው፣ ‹‹ቪዲዮው የተለየ ነገር የለውም፤ በዚህም ምን አዲስ ነገር ሊያስመሰክሩ ነው? ….ማስረጃው ከቀረበ ሙሉ በሙሉ ሳይቆራረጥ መታየት አለበት›› በማለት ተቃውሞ አቅርበው ነበር፡፡ የችሎቱ ዳኞችም ተመካክረውበት ማስረጃው ሙሉ በሙሉ እንዲታይ ውሳኔ ሰጡ፡፡

በእለቱ ከሰዓት በኋላ ማስረጃው መታየት ጀምሮ የነበረ ቢሆንም የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቃ ክንፈሚካኤልና እስክንድር ያደረጉትን ንግግር ብቻ የሚያሳይ ሌላ ሲዲ ማምጣታቸውን ተናግረው አዲሱ ሲዲ እንዲታይላቸው ለዳኞች ጥያቄ አቅረቡ፡፡ አቃቤያን ሕግም አዲስ ይዘት ያለው ሲዲ እንደአዲስ በማስረጃነት የሚቀርብ ከሆነ በህጉ መሰረት ለፍ/ቤቱ ቀርቦ ፍ/ቤት መረጃውን ካመነበት ብቻ መቅረብ እንደሚኖርበት በመናገር ‹‹መቅረብ አይኖርበትም›› በማለት በድጋሚ ተቃውሞ አቅርበው ነበር፡፡ ፍ/ቤቱ በተደጋጋሚ የቀረቡትን ክርክሮች ካደመጠ በኋላ የቀረበው ማስረጃ እንዲታይ ቢፈቅድም የቀረበው አዲስ መረጃን የያዘው ፍላሽ ዲስክ የተባለውን ቪዲዮ መክፈት አልቻለም፡፡ ሆኖም ጉዳዩን ሲከታተል የነበረው ፍ/ቤት የተከሳሽ ተከላካይ ጠበቆችን ‹‹ተጨማሪ ማስረጃ አላቀረባቸውም፡፡ በዚህ አግባብ መረጃው ሊሰማ አይችልም፡፡ …በመሆኑም ፍ/ቤቱ ማስረጃዎች እንደተጠናቀቁ አድርጎ ወስዷል›› በማለት ውሳኔ ሰጠ፡፡

ከዚያም ፍ/ቤቱ ከዚህ ቀደም በችሎቱ በ1ኛ ተከሳሽ በኩል በማረሚያ ቤት ከደረሰባቸው ድብደባ ጋር በተያያዘ ቀርበው የነበሩ አቤቱታዎችንና የማረሚያ ቤቱ ሃላፊ በችሎት የሰጡትን መልስ መርምሮ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

እንዲሁም በፍትህና ነጋድራስ ጋዜጦች ላይ አቃቤ ሕግ አቅርቦት የነበረው የቅሬታ ጥያቄ ኮፒው ለጋዜጦቹ እንዲደርሷቸውና ለሚያዝያ 11/2004 ዓ.ም. ጠዋት 3፡00 ሰዓት ላይ አዘጋጆቹ በችሎት ቀርበው ምላሽ እንዲሰጡ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ተከሳሾች ባቀረቧቸው የመከላከያ ሰነድና የኦዲዮ ቪዲዮ ማስረጃዎች ላይ አቃቤ ሕግ አስተያየት ካለው በፅሁፍ በመዝገብ ቤት በኩል እንዲያስገባ በመግለፅ በተከሳሾች ላይ የቀረቡትን የግራ ቀኙን ክርክር ፍርድ ለመስጠት ለግንቦት 3/2004 ዓ.ም. ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

# መኢአድ ከቤንች ማጂ ዞን የተፈናቀሉ የአማራ ብሔር ተወላጆችን በተመለከተ መንግስትን ነቀፈ

## - የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ስለጉዳዩ መረጃ የለውም

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በደቡብ ክልል በቤንች ማጂ ዞን በጉራፈርዳ ወረዳ ውስጥ በነዋሪዎች ላይ በመንግስት አካላት እየተፈፀመ ያለውን በአንድ ዘር ላይ ያነጣጠረ ከሀብት ንብረት ማፈናቀልና ከመኖሪያ ቀዬ የማሳደድ እርምጃን አስመልክቶ በመንግስት ላይ ያለውን ነቀፌታ ገለፀ፡፡

መንግስት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ ለመፍትሄ ከመንቀሳቀስ ይልቅ ለርካሽ የፖለቲካ ፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ሲባል ችግሩ እንዳልተፈፀመ ለማድረግና ለማስተባበል እንዲሁም ሁኔታውን ፈፅሞ ለማዳፈን ከፍተኛ ዘመቻ ላይ መሆኑን ፓርቲው በትናንትናው እለት ለፍትሕ በላከው መግለጫ ላይ አስታውቋል፡፡

እንዲሁም፣ ‹‹የኢህአዴግ ባለስልጣናት የህዝቡን ጉዳይ ወደኋላ በመተው እውነታውን ደብቆ ኢህአዴግ በሚታወቅበት በተራ ዶክመንተሪ ፊልም ፕሮፓጋንዳ ዝግጅት ላይ መጠመዳቸው በእጅጉ አሳዝኖናል፡፡ በመሆኑም መኢአድ የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች በተፈናቃዮች ላይ እየፈፀሙት ያለውን ደባ ለህዝብ ለማጋለጥ ተገዷል›› ሲል መግለጫው ጠቅሷል፡፡

በቅርቡ ጉዳዩን ለማጣራት ከአዲስ አበባ ወደ ቤንች ማጂ ዞን ጉራፈርዳ ወረዳ የተንቀሳቀሰ አጣሪ ቡድን በህዝብ ላይ የተፈፀመ አስከፊ ግፍና በደልን ለመሸፋፈን የሚደረግ ርካሽ ተግባር መሆኑን መኢአድ በማውገዝ መንግስት ለእነዚህ በአሳዛኝ ሁኔታ ለተፈናቀሉት ዜጐች በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲሰጥ በድጋሚ ጥሪ ማቅረቡን ገልጿል፡፡ በተጨማሪም ሰው የገደለ፣ በአካል ላይ ጥቃት የፈፀመ፣ በተለያየ ህገ-ወጥ ተግባር ላይ በመሰማራት በህዝቡ ላይ ወንጀል የፈጸሙ የመንግስት ባለስልጣናት በሕግ እንዲጠየቁ መኢአድ ጠይቋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘም የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ጉዳዩን እንዴት እንደተመለከተው ፍትህ ወደ ኮሚሽኑ በአካል በመሄድና በስልክ በመጠይቅ መረጃ ለመጠይቅ ጥረት አድርጋ ነበር፡፡ የኮሚሽኑ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር የሆኑትን አቶ ብርሃኑ አባቴም ‹‹አንድም በተገቢው መንገድ በአዲስ አበባና በአዋሳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የቀረበ አቤቱታ የለም፡፡ ተከታትለን ያገኘነው መረጃም ስለሌለ የምንሰጠው መረጃ የለም›› በማለት ለፍትህ መልስ ሰጥተዋል፡፡

# ኢትዮጵያ የተባበሩ መንግስታት የደህንነት ሰራተኛን በሽብርተኝነት ከሰሰች

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የደህንነት ሰራተኛ የሆኑት ኢትዮጵያዊው አቶ አብዱራህማን ሼክ ሀሰን በሽብርተኝነት ከተፈረጀው ከኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር (ኦብነግ) ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በሽብርተኝነት ክስ ፍርድ ቤት መቅረባቸውን የአሜሪካ ድምፅ ሬዲዮ (ቪኦኤ) ከትላንት በስትያ ዘገበ፡፡

አቶ አብዱራህማን ባለፈው ሐምሌ በፀረ-ሽብርተኝነት ህጉ መሰረት ታስረው ባለፈው ሰኞ ፍርድ ቤት የቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ለግንቦት 7 ቀን ቀጠሮ ሰጥቷቸዋል፡፡

የክስ ቻርጃቸው እንደሚያስረዳው በኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ አውጪ ግንባር መሪነት የኢትዮጵያን መንግስት በኃይል ከስልጣን ለማውረድ ሙከራ አድርገዋል የሚል ነው፡፡

አቶ አብዱራህማን ከመታሰራቸው ከሳምንታት በፊት በኦጋዴን ክልል ለእስር የተዳረጉትን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሁለት ሰራተኞችን ለማስፈታት ድርድር እያደረጉ እንደነበር ተገልጿል፡፡ ቪኦኤ በዘገባው ሁለቱ ሰዎች ባልታወቁ ታጣቂዎች ታግተው ከ6 ሳምንታት በላይ መሰወራቸው የታወቀ ሲሆን በወቅቱ አንድ የዓለም ምግብ ፕሮግራም ባልደረባ የተገደለ ሲሆን ሌላኛውም ክፉኛ ቆስሎ ነበር ብሏል፡፡ መንግስት የታገቱትን ሰዎች ለማስፈታት ከአማፂያኑ ጋር የተደረገውን የስልክ ልውውጥ ለክሱ እንደማስረጃ አቅርቧል፡፡

የተባበሩት መንግስታት የኢትዮጵያ ተወካይ አቶ ኡግን አውሱ የአቶ አብዱራህማን መብት መጠበቁን ለማረጋገጥ ከኢትዮጵያ መንግስት ጋር በቅርበት እየተነጋገሩ እንደሆነ የገለፁ ሲሆን የመንግስት ቃለ አቃባይ የሆኑት አቶ ሽመልስ ከማል የተመድ ሰራተኛ ስለመታሰሩ እንደማያውቁ መናገራቸውን ቪኦኤ ዘግቧል፡፡

# የአራዳ ክ/ከተማ ባለስልጣን ከግድያ ለማምለጥ ከሁለተኛ ፎቅ ላይ ዘለሉ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በተለምዶ የእረከበ ሱቅ (የኮንቴነር ሱቅ) በመስራት ላይ ያለ እንዲሁም ከ6 ኪሎ ፈረንሳይ ባለው የታክሲ ቀጠና ተራ አስከባሪ የሆነው ወጣት ‹‹የታክሲ ተራ አስከባሪም፣ ባለሱቅም ሆነህ መስራት አትችልም›› አለኝ ያለውን የወረዳ 6 ስራ አስፈፃሚ አቶ ሻረው ዘለቀ ላይ በክላሽንኮቭ መሳሪያ ያደረገው የግድያ ሙከራ ከሸፎበት በቁጥጥር ስር መዋሉን ምንጮቻችን ገለፁ፡፡

እንደምንጮቻችን ገላፃ ከአመት በፊት መንገድ ትራንስፖርት ‹‹በአነስተኛና ጥቃቅን የተደራጀ በታክሲ ተራ ማስከበር ስራ አይሰመራም›› በሚለው መመሪያ ሱቁ እንዳይነጠቅ በወደሙ ስም ለማዞር በወቅቱ የአነስተኛና ጥቃቅን ፅ/ቤት ኋላፊ ወደነበሩት አቶ ሻረው ዘለቀ ቢያመለክትም ጉደዩ ተቀበይነት ሳያገኝ ይቀራል፡፡ ይሁንና ተደጋጋሚ ጥያቄ እያቀረበ ሳለ ሳይመለስለት ቅሬታውን ለወና ስራ አስፈፃሚው እንዲያቀርብ ይነገረዋል፡፡ ወጣቱም ወደዋና ስራአስፈፃሚው ቢሮ ሲሄድ አቶ ሻረው ዘለቀን በእድገት ዋና ስራአስፈፃሚ ሆኖ ያገኛቸዋል፡፡

‹‹ከዚህ በኋላ›› አሉ ምንጮቻችን መፍትሄ አላገኝም ሲል ያሰበው ተጠርጣሪ ‹‹ሰኞ ሚያዝያ 1/2004 ዓ.ም. ከጠዋት 3፡30 ላይ በቀጥታ ወደ ወረዳው ፅ/ቤት ይሄድና ከጊቢው ጠባቂ አንድ ክላሽንኮቭ መሳሪያ በኃይል በመቀማት የህዝብ አደረጃጀት ኃላፊ የሆኑት አቶ ሳሙኤል ወልዴ ላይ መሳሪያውን በመደቀን ዋና ስራአስፈፃሚው ወደሚገኙበት 4ኛ ፎቅ እንዲመሩ ያስገድዳቸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ ማራኪውና ተማራኪው 2ኛ ፎቅ ላይ ሲደርሱ ድንገት ለስራ ጉዳይ ከቢሮአቸው ወጥተው ወደታች እየወረዱ ከነበሩት ዋና ስራ አስፈፃሚው ጋር ፊት ለፊት ይገናኛሉ፤ በዋናነት የሚፈልገውን ኃላፊ ያገኘው ተጠርጣሪም በያዘው መሳሪያ ለመተኮስ ሙከራ ሲያደርግ መሳሪያው ነከሰበት፡፡ ይህን ጊዜም ዋና ስራ አስፈፃሚው ከጥይት ለማምለጥ ከ2ኛ ፎቅ ላይ ቁልቁል ራሳቸውን ወረወሩ፤ ከዚህ በኋላም ተጠርጣሪው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሲውል ዋና ስራ አስፈፃሚውም እግራቸው ተሰብሮ ወደ ሆስፒታል ሄዱ ›› ሲሉ ምንጮቻችን በተለይ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

# የፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ›› መጽሐፍ ታተመ

‹‹…ሽብርተኛነት ለኢትዮጵያ ባህልና ጨዋነት ባዕድ ነው…››

ፕ/ር መስፍን ወልደማርያም ‹‹አደጋ ያንዣበበበት የአፍሪካ ቀንድ›› በሚል ርዕስ የአፍሪካ ቀንድ የፖለቲካ እና የታሪክ አውዶችን የሚተነትን መፅሐፍ አሳተሙ፡፡ መፅሁፉ የአፍሪካ ቀንድ አቀማመጥና ጉርብትና፣ ሽብርና ሽብርተኝነት፣ የአረቦች ሕዝባዊ አብዮት፣ የሶማሊያ ትርምስና መዘዙ እንዲሁም የአፍሪካ ቀንድ ግጭትና ጦርነት የሚሉ እና ሌሎች ተዛማጅ ርዕሶችን ይዟል፡፡ አስራ አንድ ምዕራፎች ሲኖሩት ሁለት አባሪዎችንም አካትቷል፡፡

የመጀመሪያው አባሪ በ1951 ዓ.ም. ፕ/ሩ ወደ ኦጋዴን ለወሰን ጥናት የተላከው ሚሲዮን አባል በነበሩት ወቅት በወቅቱ ለነበሩት የሚኒስትር መስሪያ ቤቶች ያቀረቡት ማስታወሻ ሲሆን፣ ሌላኛው አባሪ “Ethiopia and the Indian ocean” በሚል ርዕስ እ.ኤ.አ. በ1917 ዓ.ም. በጆርጅ ታውን ዩኒቨርስቲ አለም ዓቀፍ የጥናት ጉባኤ ያቀረቡት ጥናታዊ ፅሁፍ ነው፡፡ ‹‹አደጋ ያንዣበበት የአፍሪካ ቀንድ›› ስድስት ካርታዎችን ያካተተ ባለ237 ገፅ መድብል ሲሆን በ45 የኢትዮጵያ ብር ከሚቀጥለው ማክሰኞ ጀምሮ በገበያ ላይ ይውላል፡፡

# በሊባኖስ ራሷን ላጠፋችው አለም ደቻሳ የገቢ ማሰባሰቢያ ይደረጋል

ቀደም ሲል ደረሶባት በነበረው አሰቃቂ ሰቆቃና ስቃይ ሳቢያ መጋቢት 05/2004 ዓ.ም. ከምሽቱ 12 ሰዓት በሊባኖስ ራሷን አንቃ ለገደለችውና የሶስት ልጆች እናት ለሆነችው ወ/ሮ አለም ደቻሳ በቀጣዩ ሀሙስ እለት በዋቢ ሸበሌ ሆቴል ለልጆቿ የሚሆን የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም ሊደረግ ነው፡፡

ራሳቸውን ‹‹ዴት ኢትዮጵያ ግሩፕ›› በሚል መጠሪያ የሚጠሩት 16 ወጣቶች¬ ከአሲምባ ኮሙኒኬሽን ጋር በመተባበር ስለሚያቀርቡት ፕሮግራም የፕሮግራሙ አስተባባሪዎች ወ/ት ማህሌት ሰለሞንና ወ/ት መሰረት ለማ በዕለቱ የሚቿን ህይወት የሚያሳይ የ10 ደቂቃ ዶክመንተሪ ፊልም መዘጋጀቱን፣ ለልጆቿ የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም እንደሚደረግና ስለ ‹‹ዴት ኢትዮጵያ ግሩፕ›› አላማ እንደሚገለፅ ለፍትሕ ተናግረዋል፡፡ ፕሩፑም በቀጣይ ወደ አረብ አገራት ለስራ የሚሄዱ ዜጐች በዚያ የሚደርስባቸውን ችግር ከመቀነስ አኳያ ጥሩ ግንዛቤ እንዲያገኙና መረጃ መለዋወጥ እንዲችሉ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንደሚሰራ ተገልጿል፡፡

በአረብ አገራት ኢትዮጵያዊ ዜጐች የሚደርስባቸውን ችግርና አሳዛኝ ሁኔታ ለመቀነስ የሁሉም ዜጎች ተሳታፊነት እንደሚጠይቅ የጠቀሱት ወ/ት ማህሌትና ወ/ት መሰረት፣ በሂደት ተደማጭነት ያለው ሕብረተሰብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

# ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብና ንብረት በማፍራት የተከሰሱ ለፍርድ ተቀጠሩ

የፌዴራል የስነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ‹‹ምንጩ ያልታወቀን ገንዘብና ንብረት በማፍራታቸው፣ የመንግስትን ስራ በማያመች መንገድ በመምራታቸውና የማይገባ ጥቅም በመቀበላቸው›› በሚል ክስ በመሰረተባቸው ሶስት ግለሰቦች ላይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 15ኛ ወንጀል ችሎት መጋቢት 19/2004 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የጥፋተኝነት ውሳኔ አስተላለፈ፡፡

የኮሚሽኑ ዓቃቤ ሕግ የክስ መዝገብ እንደሚያመለክተው፣ 1ኛ ተከሳሽ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊ ዳኛቸው ካሳ፣ 2ኛ ተከሳሽ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቤተ-መጽሐፍት ባለሙያና የ1ኛ ተከሳሽ ባለቤት አምሳለ መኮንን፣ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የእሌኒ ማተሚያ ቤት ባለቤት እና ስራ አስኪያጅ ታደሰ ትእዛዙ ናቸው፡፡

በአንደኛው ክስ መሰረት በ1997 ዓ.ም በጀት ዓመት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፋይል ፎልደሮችን ለመግዛት ባወጣው ጨረታ አውጥቶ የእሌኒ ማተሚያ ቤት በማgነፉ ግዥ ይፈፅማል፡፡ ከግዢው በኋላ ፍርድ ቤቱ በድጋሚ ሌላ ጨረታ ሳያወጣ 1ኛ ተከሳሽ ከመንግስት ፋይናንስ አዋጅና ከግዥ መመሪያ ውጭ 3ኛ ተከሳሽን ለመጥቀም በማሰብ ከጨረታ ውጪ ተጨማሪ የፋይል ፎልደሮች ግዥ እንዲፈፀም ያደርጋል፡፡ በክሱ መሰረት 3ኛ ተከሳሽም በበኩሉ ከሕግ፣ ከደንብና ከመመሪያ ውጭ ከ1ኛ ተከሳሽ ጋር በመመሳጠር የዕቃ ማቅረቢያ ውል ተዋውሎ ዕቃውን በማቅረብ እና ክፍያ ተቀብሎ ነበር -

በተያያዘም 3ኛ ተከሳሽ በ1998 ዓ.ም. ለጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የህትመት አገልግሎት በመስጠት ከተቀበለው ክፍያ ውስጥ 730,000 ብር በ2ኛ ተከሳሽ በኩል ወደ 1ኛ ተከሳሽ የባንክ ሂሳብ እንዲገባለት በማድረጉ ሶስቱም ተከሳሾች በሕገ-ወጥ መንገድ ለራሳቸው ተጠቃሚ በመሆናቸው በግብረ አበርነት የሙስና ወንጀል መፈፀማቸውን የክስ መዝገቡ ያስረዳል፡፡

በሁለተኛ ክስ ደግሞ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች ህጋዊና ትክክለኛው የገቢ ምንጫቸው ከሆነውና እስከ 2002 ዓ.ም. ድረስ ያገኙ የነበረው የመንግስት ደመወዛቸው በድምሩ ብር 291,445 ነበር፡፡ ሆኖም በልጆቻቸውና በራሳቸው ስም ምንጫቸው ያልታወቀ በባንክ የሚገኝ 1,076,153 ብር፣ የዋጋ ግምቱ 610,000 ብር የሆነ አንድ የጋራ መኖሪያ ቤትና ባለ አራት ፎቅ (G+4) ህንፃ ይዘው ተገኝተዋል፡፡

በመሆኑም ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክሶች መከላከል ባለመቻላቸው ፍርድ ቤቱ ከላይ በተጠቀሰው ቀን በዋለው ችሎት የጥፋተኝነት ውሳኔ ያስተላለፈ ሲሆን የቅጣት ውሳኔውንም ለመስማት ፍ/ቤቱ ለሚያዝያ 9/2004 ዓ.ም. ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

# የአራት ኪሎ ነዋሪዎች እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ገለፁ

በአራት ኪሎ ልዩ ስሙ ‹‹ባሻ ወልዴ ችሎት ሰፈር›› ተብሎ ለሚጠራው አካባቢ በቀበሌ ቤት ውስጥ የሚኖሩ የወረዳ 8 ቀበሌ 7 ነዋሪዎች ‹‹ለፓርላማ ፕሮጀክት ማስፋፊያ›› በሚል በመስተዳድሩ ‹‹ከፋሲካ ማግስት በኋላ ተነሱ›› በመባላቸው እጅግ አደገኛ እና አሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ለፍትሕ ገለፁ፡፡

እንደነዋሪዎቹ ገለፃ ከሆነ ልማቱን በደስታ ቢደግፉትም ልጆች ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁ በመስተዳደሩ አባላት ከአውደ ዓመት በኋላ ‹‹ትነሳላችሁ›› መባላቸው ትልቅ ስጋትና ድንጋጤ ውስጥ እንደከተታቸው በሀዘኔታ ተናግረዋል፡፡ የአብዛኛው ነዋሪዎች ውሳኔና አስተያየት ተመሳሳይ እንደሆነ ለፍትህ የገለፁት ቅሬታ አቅራቢዎች፣ ለሁለት ወር ያህል በሚኖሩበት ቦታ ሆነው የልጆቻቸው ትምህርት እስኪጠናቀቅ ይፈልጋሉ፡፡

ጉዳዩን አስመልክቶ የአራዳ ክ/ከተማ የወረዳ 8 ጽ/ቤት ዋና ስራ አስፈፃሚ የሆኑትን አቶ ደሳለኝ ደበሌን በስልክ ስናነጋግራቸው በመጀመሪያ ‹‹ቅሬታ ስላቀረቡት ነዋሪዎች በቂ መረጃ ይዛችሁ ኑ›› የሚል ምላሽ ሰጥተውን ነበር፡፡ ከዚያም ኃላፊው ቢሮ በአካል በመሄድ ምላሻቸውን እንዲሰጡን ብንሞክርም ከቢሮ ለአስቸኳይ ስራ መውጣታቸውን በመግለፅ በስልክ መልስ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

# እጅግ የተከበሩ የዓለም ሎሬት … ከገፅ 1 የዞረ

በመባል የተሸለሙ ሲሆን በህይወት ዘመናቸውም ሌሎች በርካታ ሽልማቶችንም አግኝተዋል፡፡

ሽልማት ማግኘት የጀመሩት ገና በተማሪነት ዘመናቸው ሲሆን በዚህ ወቅትም ከአስር በላይ ሽልማቶችን ከማግኘታቸው በተጨማሪ በቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ ዘመን ከአቶ ከበደ ሚካኤል ጋር የመጀመሪያ የሥነ-ጥበብ ተሸላሚ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

ሎሬት በጣም የተከበሩ ሰው ነበሩ የሚሉት በቅርብ የሚያውቋቸው የማስታወቂያ ባለሙያው አቶ ውብሸት ወርቃለማሁ ‹‹ከተለያዩ ሀገራት ከሚመጡ የሀገር መሪዎች ጋር በአፄ ኃይለ ስላሴ እራት ይጋበዙ የነበሩ ክቡር ሰው ነበሩ›› ሲሉ ለፍትህ ገልፀዋል፡፡

የሰዓሊው የቀብር ስነ-ስርዓት የፊታችን ቅዳሜ ሚያዝያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም. ከቀኑ 9፡00 ሰዓት በቅድስት ስላሴ ካቴድራል ቤተክርስቲያን እንደሚፈፀም እና የቀብሩን ስነ-ስርዓት የሚያስፈፅመው የባህል ማዕከል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡

# በጀግናው በላይ ዘለቀ ህይወት ዙሪያ ፊልም ሊሰራ ነው

‹‹ትልቅ ሰውዬ››በሚል ርዕስ በላይ ዘለቀ ከለጋ የልጅነት እድሜው ህይወቱን በስቅላት እስከተነጠቀበት ቅፅበት ድረስ የተጓዘውን የህይወት ውጣ ውረድ የሚያሳይ ፊልም በእያሱ በካፋ የኔነህ ተደርሶ በዋና እና በም/ ዳይሬክተርነት በዮናስ ብርሀነ መዋና ሰለሞን ተፈሪ ሊሰራ እንደሆነ ተገለፀ፡፡ ፊልሙን እናርጅ እናውጋ የልማት ማህበር ስፖንሰር ማድረጉን ዕረቡ ሚያዚያ 3/2004 በተሠጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተገልጿል፡፡

በበላይ ዘለቀ ህይወት ታሪክ ዙሪያ የሚያጠነጥነው ‹‹ትልቅ ሰው››ከ6-7 ሚልዮን ብር ወጪ እንደሚደረግበትናፊልሙ አለም አቀፍ ተቀባይነትና ደረጃ እንዲኖረው ለማድረግ እንዲሁም በጀግናው ላይ የሚደረገውን የታሪክ ማበላሸት እንዲገታ ተደርጎ እንደሚሰራና ፊልሙን ሰርቶ ለማጠናቀቅ አንድ አመት ከ6ወር እንደሚፈጅ አዘጋጆቹ ገልፀዋል፡፡

# “በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል”

ማቴ ም.5 ቁ.21-26

‹‹ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፡፡ እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፡፡ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፡፡ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሣት ፍርድ ይገባዋል፡፡ እንግዲህ መባህን በመሰዊያው ላይ ብታቀርብ በዚያም ወንድምህ አንዳች ባንተ ላይ እንዳለው ብታስብ በዚያ በመሰዊያ ፊት መባህን ትተህ ሂድ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፤ ከዛም መጥተህ መባህን አቅርብ፡፡

አብረው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራ ጋር ፈጥነህ ተስማማ ባላጋራህ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሌላው ወደ ወህኒም ትጣላለህ እውነት እልሃለሁ የመጨረሻውን ሳንቲም እስክትከፍል ከቶ ከዚህ አትወጣም፡፡›› ማቴ ም.5 ቁ.21-26

እነሆ ዛሬ የስቅለት በአል ነው፡፡ የስቅለትን የመታሰቢያ ዋጋ ደግሞ በሁለት ከፍለን ብናየው የተሻለ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም በዕለቱ በቀራንዮ የተሰቀለው ሁለት ነገር ነውና፡፡ የመጀመሪያው ራሱ የእየሱስ ክርስቶስ አካል ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ክርስቶስ ያየዘው እውነት ነው፡፡ አዎን በዛሬው ቀን የተሰቀለው ‹‹እውነት›› ነው፡፡ እናም ከዚህን ጊዜ አንስቶ ከብዙዎች እውነት የራቀች ይመስለኛል፡፡

የሆነ ሆኖ የክርስትና መሰረትና አባት የሆነው እየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቶቹና ለተከታዮች በእየሩሳሌም ጎዳና ሲመላለስ ካስተላለፈው አስተምህሮተ ውስጥ በሰው ልጅ ላይ ቂም መያዝን አውግዞ፣ የይቅርታን አስፈላጊነት ያስተማረበትን በጉልህ እናገኛለን፡፡ ይህ ሁኔታ በተለይም ከኢትዮጵያውያኖች መሀል በአሁኑ ጊዜ እየራቀ ነው፡፡

መንግስት በተለያዩ ጊዜያት የሚወስዳቸው እርምጃዎች ከህግ እና ከሞራል የራቁ በመሆኑ ህዝቡ ሆ ብሎ ሊነሳብኝ ይችላል ሲል በብርቱ ይጠረጥራል፡፡ ህዝብም እንዲሁ መንግስት ደጋግሞ መዋሸትን ስራዩ ብሎ ስለያዘው ምንም ያህል እውነትም ቢናገር አስቀድሞ ትዝ የሚለው የውሸታሙ እረኛ ታሪክ ነው፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ይህ ሁኔታ በህዝብ መካከልም መተማመን እንዳይኖር ማድረጉ ነው፡፡ አረ በዚህ ብቻ አይቆምም፡፡ አልፎ ተርፎም በትዳር ጓደኞች፣ በአባትና ልጅ፣ በእህትና ወንድም መካከልም እንዲሁ መተማመን እየጠፋ ነው፡፡

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ መልኩንና አላማውን ከዚሁ የመካካድ ባህል ጋር እራሱን እያፈጠመ ነው፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ቀደም ተቃዋሚዎች የውስጥ ለውስጥ ሽኩቻ ቢኖርባቸውም ቅድሚ የሚሰጡት የትግል አጀንዳ ነበራቸው፡፡ አሁን አሁን ይህ ሁኔታ ተቀይሮአል፡፡ እንደ ስትራቴጂ አድርገው የያዙት በትግል ውስጥ እንደወንድም ሊታይ የሚገባውን የትግል አጋራቸውን ማውገዝ እና መንቀፍ ብሎም በህብረተሰቡ ውስጥ ፈፀማቸው የተባሉትን ህፀፆች በማውጣት ማሰጣት ላይ ነውና፡፡ በተለይ በተለይ ከምርጫ 97 ወዲህ ሁኔታው እጅግ በጣም ብሶበታል፡፡ በአንድ ፓርቲ ውስጥ በጋራ መታገል የምህዳር በፖለቲካው መጥበብን ያህል ፈታኝ የሆነበት ዘመን ላይ ደርሰናል፡፡ ወንድም በወንድሙ ላይ የሚቆጣበት፣ የሚያቄምበት፣ ይቅር የማይልበት…

በፓርቲ ውስጥ ሰላማዊ ተቃውሞና ድጋፍ ያለና የነበረ የሚኖርም ነው፡፡ እንዲያውም እንደ ፖለቲካ ተንታኞች አረዳድ የፓርቲ ሽኩቻ /ፉክክር/ ለፓርቲው የዴሞክራሲን ባህል ለማስረፅ ወሳኝ ነው፡፡ በዴሞክራሲ ማደግ እንደምሳሌ በምትጠቀሰው አሜሪካ እንኳን ምርጫ በመጣ ቁጥር ከፊታቸው ለሚጠብቃቸው የአገሪቱ ፕሬዚዳንታዊ መንበር በዴሞክራቶቹ እና በሪፐብሊካኖቹ ሁል ጊዜም የሚደረግ ፉክክር ይልቃል እንጂ አያንስም፡፡ ይሄ ጤናማና ተፈላጊው ፉክክር ነው፡፡ ጤናማ ያልሆነው አሁን አሁን በሀገራችን እየተለመደ የመጣው የፉክክር አይነት ነው፡፡ የሰው ልጅ የሚማረው አንድም ከቃል አንድም ከመከራ ነው ይባላል፣ ሆኖም የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎቻችን ከየትኛው ሊማሩ እንደተዘጋጁ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ዛሬ ኢትዮጵያውያኖች በሞራልም በኢኮኖሚም ወደፊት የሚያራምዳቸው እና ነፃ የሚያወጣቸውን ሙሴ ይሻሉ፡፡ መብቶቻቸውን የሚያስከብርላቸው፣ ትግሉ ሊያስከፍል የሚችለውን መስዋትነት የሚከፍል ጠንካራና አላማ ያለው የጋንዲ አይነት መሪና የፖለቲካ ፓርቲ ይፈልጋሉ፡፡ ነገር ግን ይህን አይነት ጥንካሬ ለማምጣት ዩኒቨርስቲ ገብቶ ዶክተርና ኢንጂነር መባል ብቻ ዋጋ የለውም፡፡ ከሁሉም በፊት ሆደ ሰፊና ይቅር ባይነትን ይጠይቃልና፡፡

እናም ለሰዎች ሀጢያታቸውን ይቅር ብትሉ የሰማዩ አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና ለሰዎች ግን ኃጢያታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ሀጢያታቸውን ይቅር አይላቸውም በሚለው የመጽሀፉ ቃል መሰረት ይቅር መባባል ከምንም በላይ ወሳኝ ነው፡፡ ይቅር ባይነት ለሁሉም ነገር መሰረት ነው፡፡ በኢትዮጵያውያንና በአለም አቀፍ ማህበረሰብ በምርጫ 97 ማግስት አምባገነን ተብሎ የተፈረጀው ገዢው ፓርቲ /ኢህአዴግ/ እንኳን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ሕገ-መንግስቱን በሃይል ሊንዱ ተንቀሳቅሰዋል፣ የጎዳና ላይ ነውጥ አካሂደዋል ሲል ከሶ እድሜ ልክ የፈረደባቸውን የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አመራሮችን ይቅር ለእግዚአብሔር ብያቸዋለሁ ማለቱ እንደ አንድ መልካም ነገር ሊወሰድ ይገባዋል፡፡

ሌላው ቀርቶ ባላጋራህን ይቅር ብለህ ተስማማ ከተባለ ለተመሳሳይ አላማ ከጎን የተሰለፈውን ወንድም ይቅር አለማለቱ በሰማዩም በምድሩም ማስጠየቁ አይቀርም፡፡ ሆደ ሰፊነትን ከገዥውም ከተቃዋሚዎችም እንፈልጋለን፡፡ ደርግ ለሽማግሌው ንጉሰ ነገስትና ለስልሳዎቹ ሹማምንት ይቅርታን ነፈገ፡፡ እናም ደርግ ጀንበሩ በጠለቀችበት ጊዜ በተራው ይቅርታን ተነፈገ፣ በወህኒ ተወርውሮ ተዘጋበት፡፡ እዚህም ጋ ልብ ሊባል የሚገባው ነጥብ አሁንም ገዥው ፓርቲ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ለደርግ ባለስልጣናት ያደረገውን ምህርት ነው፡፡

ስለዚህም ሚሊዮናት የተቀናቃኝ ፓርቲዎችን አንድነትና የጋራ ትግል ተስፋ ያደረጉ የምንጊዜም ፀሎታቸው ለአንድነታችሁ እና ለትብብራችሁ ለመሆኑ ከማንም የተሰወረ አይደለም፡፡ ትግሉን ለማሳካት አስቸጋሪ ሁኔታ ቢፈጠር እንኳን ከወንድማቸው ቀርቶ ከባላጋራችሁ ጋር እንድትሰሩ ይጠበቃል፡፡ ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ›› የሚለውን ቅዱስ ቃል መርህ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ይቅር ባይነት ለፖለቲካ ፓርቲዎቻችን አስፈላጊ ፀጋ ነው፡፡ ከይቅር ባይነት አዋቂነት እንጂ ኪሳራ የለውም፡፡ ብትተባበሩ ትጠነክራላችሁ፣ ብትበታተኑ ትፍረከረካላችሁ /ትዳከማላችሁ/፡፡

እ ኛ ኢትዮጵያውያኖች ካለብን ዘርፈ ብዙ ችግር አንፃር መሽቶ ሲነጋ አዲስና ብሩህ ቀን እንደሚናፈቀው ሁሉ ተስፋን ሰንቀናል፡፡ ብዙ ተስፋዎችን እንናፍቃለን፡፡ መንጋውን ሊበትን የማይችል እረኛን እንጠብቃለን፡፡ ዛሬም ተስፋ አልቆረጥንም፣ የይቅር ባይነትን ጠቀሜታ እናውቃለንና፡፡

በ1997 የምርጫ ወቅት አንደበተ ርቱእ ፖለቲከኞችን ይዞ፣ አማራጭ የፖለቲካ ፕሮግራም በማቅረብ ጠንካራና በአጭር ጊዜ ተወዳጅ የነበረው፣ ሚያዝያ 30 በሚሊዮን የሚቆጠሩ ደጋፊዎቻን ያሰለፈው ቅንጅት አሁን የት እንዳለ ማስተዋሉ መልካም ነው፡፡ በዚህ ተዋህዱ፣ ተቀናጁ ለሚቀጥለው ምርጫ በጥንካሬ ለመስራት እየተዘጋጁ ነው የሚለው መልካም ዜና እንደሰማይ በራቀበት ዘመን ከመተባበር ባሻገር ያለ አማራጭ ወንዝ አያሻግርም፡፡ ‹‹እርስ በእርሷ የምትለያይ መንግስት ሁሉ ትጠፋለች እርስ በእርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም›› በተፎካካሪያችሁ ላይ ድልን ለመቀዳጀት ህብረታችሁ ወሳኝ ነው፡፡ አለበለዚያ በመለያየታችሁ የሚመጣውን ድክመት ተጠቅሞ ተቀናቃኛችሁ ገዢው ፓርቲ በቀላሉ ሊያሸንፋችሁ ይችላል፣ ደግሞም ያሸንፋችኋል፡፡ እናም በትግል ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በውይይት ፈቶ እና ተስማምቶ ወይም በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ተቻችሎ ወደፊት መጓዙ ወሳኝ ነው፡፡

ለተመሳሳይ አላማ በአንድ ድርጅት ውስጥ ሲታገሉ አልፎ አልፎ ችግሮች ሊያጋጥም ይችላል፡፡ ያጋጥማልም፡፡ ቁም ነገሩ ችግሩ በምን ተፈታ? እንዴት ይፈታል? የሚሉት ናቸው፡፡ ልታስተውሉት የሚገባ ነገር ቢኖር ጥቂት ቅያሜ ወይም ልዩነት ሲመጣ ተሽቀዳድሞ በሚዲያ ከማሳጣትና ከማሳቀል ይልቅ ቅያሜውን ለባለጉዳዩ ነግሮ መወቃቀስና መስማማት ነው፡፡ ‹‹ወንድምህ ቢበድልህ ሂድና አንተንና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው›› ማቴ ም.18 ቁ.15፡፡ መወቃቀስ በራሱ ይቅርታ መደራረግ ነው፡፡ ለመውቀስና ይቅርታ ለማድረግ ምንም ምክንያት አያስፈልገውም፡፡ ‹‹በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ ጌታ ሆይ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እስከሰባት ጊዜ አለው፡፡ እየሱስም እንዲህ አለው እስከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እስከ ሰባት አልልህም›› ማቴ ም.18 ቁ.21-22፡፡ ምን ያህል ጊዜ ይቅር እንደተባባላችሁ ለማስታወስ ሞክር፡፡ እንግዲህ ከሰባት ጊዜ ሰባ በታች ከሆነ ይቅርታ ያደረጋችሁት አሁንም ጊዜ አላችሁ ይቅር ተባባሉ፡፡

ለትግላችሁ ስኬት የአምላካችሁና የአምላካችን ድጋፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የሚሰጥም እግዚአብሔር፣ የሚነሳም እግዚአብሔር የምትሹትን ለማግኘት እናንተም የምትከፍሉት ዋጋ አለ፡፡ ያ የምትከፍሉት ዋጋ፣ ዋጋ የሚኖረው አጠገባችሁ ለአለው፣ ለበደላችሁ ይቅርታን በማድረግ ነው፡፡ እናንተ ይቅር ካላችሁ የጠየቃችሁትን ታገኛላችሁ፡፡ ‹‹መንግስተ ሰማያት ባሮቹን ሊቆጣጠር የወደደን ንጉስ ትመስላለች፣ መቆጣጠርም በጀመረ ጊዜ እልፍ መክሊት እዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ፡፡ የሚከፍለውም ቢያጣ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውን ሁሉ እንዲሸጡና እዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ፡፡ ባርያውም ጌታ ሆይ ታገሰኝ ሁሉንም እከፍልሀለሁ አለው፡፡ የዚያም ባርያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው እዳውንም ተወለት፡፡ ነገር ግን ያ ባርያ ወጥቶ ከባልደረቦቹ መቶ ዲናር ያለበትን አንዱን አገኘና እዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው፡፡ ስለዚህ ባልንጀራው ባርያ ወድቆ ታገሰኝ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው፡፡ እርሱም አልወደደም ግን ሄዶ እዳውን እስኪከፍለው ድረስ ወህኒ አኖረው፡፡ ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ መጥተውም ለጌታቸው ነገሩት፡፡ ጌታውም አንተ ክፉ ባርያህ ስለለመንከኝ ያን ሁሉ እዳ ተውኩልህ፡፡ እኔ እንደማርሁ ባልንጀራህ /ጓደኛህ/ የሆነውን ባርያ ልትምረው ለአንተስ አይገባምን አለው፤ ጌታውም ተቆጣና እዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚያሰቃዩት አሳልፎ ሰጠው፡፡ ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ እንዲሁም ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል ማቴ ም.8 ቁ.23-35፡፡ እንደዚያ ስግብግብ ባርያ እናንተም ይቅርታ ተደርጎላችኋል፡፡ እዳችሁም /ክሳችሁም/ ተሰርዞላችኋል፡፡ መንገዳችሁ ሁሉ ቀናና ቀጥተኛ እንዲሆን መጀመሪያ ሠላም፣ ፍቅርና ይቅር ባይነትን ይስጣችሁ፡፡ አሜን ይስጠን፡፡

